
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር 7ኛ ዓመት ቁጥር 4 ነሐሴ/መስከረም 1992 ዓ.ም



# እንኳን አደረሳችሁ

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ቢያስቡ መልካም ነው

በሰንበት ቀን በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኘ ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የሚያስቀድስበት፣ እናም የሚቀደስበት ቀን ነው:: ነገር ግን አንዳንድ አባቶች /ምእመናን/ በሰንበት ወደ ቤተክርስቲያን ከመሄድ ይልቅ ሌላ ቀጠሮ እየያዙ እዚያ ሸንጎ ላይ ሲውሉ ይታያሉ:: እንዲህ ዓይነቱ ሸንጎ ጌታችንን ከሰቀሉት ከአይሁዳውያን ሸንጎ ተለይቶ አይታይምና የሰንበት ቀን ቀጠሮአቸውን በሌላ ቀን አድርገው ሰንበትን ይቀድሱአት ዘንድ ቢያስቡ መልካም ነው::

*ፍሬ ሰንበት ኃ/ማርያም*
*(ሆሳዕና*

## ተጠቃሚዎች ያድርገን

የአብነት ትምህርት ቤቶች ለኢትዮጵያ ያበረከቱት አስተዋጽኦ በቃላት የሚገለጽ አይደለም:: ይሁንና የእነዚህን የሕይወት ትምህርት ቤቶች ህልውና የሚፈታተኑ ነገሮች ከዘመን ዘመን እየተበራከቱ መጥተዋል:: ድሮ ድሮ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ማለትም ጐጃም፣ ጐንደር፣ ትግራይ፣ ወሎና ከፊል ሸዋ የቆሎ ተማሪ የሚማረው ወንዝ ሸንተረሩን አቋርጦ ተጉዞ «በእንተ ማርያም ስለ እመ አምላክ ብለው» ብሎ ቁራሽ ለምኖ ነበር:: አሁን አሁን ግን በተለይ በከተማ አካባቢዎች ያ ትውፊት እየጠፋ የመጣ ይመስለኛል:: በከተማ እንኳንስ ትውፊቱ የትውፊቱ ተረካቢ የሆኑ የአብነት ተማሪዎችም የሉም:: እንደምንስ ማው ተማሪ ቤት ሄድን ብለው ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው አዲስ አበባ ካለምንም ሥራ የሚዞሩ የባላገር ወጣቶች ተበራክተዋል:: የአብነት ትምህርት ቤቶች ጠፉ ማለት'ኮ ቤተክርስቲያን ተረካቢ አገልጋይ አጣች ማለት ነው:: ስለዚህ የዚች ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ልጅ የሆነ ሁሉ እየጠፋ ላለው ለዚህ ትውፊት ተቆርቋሪ በመሆን የእምነታችን የትውፊታችን ተጠቃሚዎች ያድርገን::

*ከንድነህ ወ/ሰንበት*
*ከማሺ*

## እየተከታተልን

የቤተክርስቲያንን ፍትፍት በልተውና ትምህርቷን ተምረው ካደጉ በኋላ መልሰው የሚ ክዷት የእናት ጡት ነካሾች እየተ በራከቱ መጥተዋል:: ይህ ሊሆን የግድ ነውና አይደንቀንም:: የሆነው ሆኖ እነዚህ መናፍቃን ዕለት ዕለት አመጣጣቸውን እየቀያየሩ እንደመምጣታቸው እኛም አካሄዳቸውን እየተከታተልን ልንቋቋማቸው ይገባል:: እነዚህ እኔ ባለሁበት አካባቢ አንድ መሪጌታ ነኝ ባይ በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች በተለይ በሰሜን ባሉ እየተዘዋወረ አንድ ጊዜ መሪጌታ እንባቆም፣ ሌላ ጊዜ መሪጌታ እንቁ ባሕርይ ሌላ ጊዜ ደግሞ መሪጌታ ድልበድል እያለ ወደ አባቶች በመቅረብ የዕውቀት ምንጭ የሆኑ ልዩ ልዩ መጻሕፍት በመቀበል ብራናውን እየፋቀ የኑፋቄ ትምህርቱን የሚጽፍ መናፍቅ እንዳለ ደርሰንበታል :: ስለዚህ ፍቁረ ጥበብ ሰሎሞን «ወይናችን አብቦ አልና የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮዎች አጥምዱችሁ ያዙልን» እንዳለው በተለሳለሰ አንደበትና ማንነታቸውን ሰውረው በያዙት የዲቁና መአርግ እየተጠቀሙ ብዙ የጥፋት ሥራ እየሠሩ ነውና ሕዝበ ክርስቲያን በያለንበት ሆነን ልንከታተላቸውና ልንመነጥራቸው ይገባል እንላለን::

*የደባርቅ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም*
*ሰንበት ት/ቤት*
*ሰ.ጐንደር/ደባርቅ/*

## ከማን ወገን ይሆን?

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስር በሚተዳደረውና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኘው የዮሴፍ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ተከሰተ የተባለውን አሳፋሪ ድርጊት በሰኔ ወር አጋማሽ ላይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በፖሊስ ፕሮግራም ሲተላለፍ ተመለከትኩ:: በፕሮግራሙ በቤተክርስቲያኑ የሚገኙ ሰዎች የድሃውን ትኩስ ሬሣ በማውጣት ሳጥኑንና ጉድጓዱን ለሀብታሞች እንደሚሸጡ በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፈ ዘገባ በተከታታይ ቀርቧል:: የተለያዩ ሰዎችም ወደ ቴሌቪዥን ጣቢያው በመቅረብ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል:: በእውነቱ እጅግ አዝኛለሁ:: ለመሆኑ ድርጊቱ ከእኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጸመ ነው ወይስ በመናፍቃን የተቀነባበረ ሴራ? እንደእኔ እንደእኔ የቤተክርስቲያን ሰዎች ይህንን አይፈጽሙም:: በእውነት ይህ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን የሌላትን ስም የሚያሰጣት ነውና የሚመለከታቸው ሁሉ ተከታትለው እውነቱን እንዲያወጡ እላለሁ::

*አቶ ዳንኤል*
*ከሊሙ ሻይ*

## ገጠመኝ

ድካሜንና ትንሽነቴን ሳይመለከት እግዚአብሔር በሰጠኝ ፀጋ እዚህ አዲስ አበባ በተለያዩ ጉባኤያት እየተዘዋወርኩ ቃለ እግዚአብሔርን እሰማለሁ:: እስተምራለሁ:: ታዲያ ምንም እንኳን በእንደዚያ ዓይነቱ ጉባኤ ተገኝቼ ባላውቅም አንድ ቀን ሀብታሞች የሚባሉ ሰዎች ከተሰበሰቡበት የጽዋ ማኅበር ተገኝቼ ሳስተምር የጉባኤው ታዳሚዎች እልፎ እልፎ ምንጥቅ ብሎ ወጥቶ ቆይቶ መግባት ሀሳቤን እየሰረቀው መጣ:: ምናልባት አራት አምስቱ ካልሆኑ በስተቀር ሁሉም እንዳውም ሁለት ሦስቴ ደጋግመው ወጡ፤ ገቡ:: የሁሉንም በልሰማ ወደ ፊት የተቀመጡት ጉባኤተኞቹን የሚያስነሣቸው አንዳች ቅጭልጭል የሚል ድምፅ ነው:: ቅጭልጭል ሲል ኪሳቸውን እየደባበሱ ወደ በር ይሮጣሉ:: በዚያ ሁኔታ እንዳለሁ በነገሩ መረበሼን ከፊቴና ከአነጋገሬ የተረዳው አንድ ወንድሜ ቀስ ብሎ መጣና በጆሮዬ «እይዞህ ሰዎቹ የሚወጡት በያዙት ሞባይል የስልክ ጥሪ ስለሚደርሳቸው ነው» አለኝ :: ነገሩ ገባኝና የጀመርኩትን ጨርሼ ተቀመጥኩ::

*ያሬድ*
*ከአዲስ አበባ*

/የሽፋን ፎቶ መታፈሪያ/

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ቢያስቡ መልካም ነው

በሰንበት ቀን በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኘ ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የሚያስቀድስበት፣ እናም የሚቀደስበት ቀን ነው:: ነገር ግን አንዳንድ አባቶች /ምእመናን/ በሰንበት ወደ ቤተክርስቲያን ከመሄድ ይልቅ ሌላ ቀጠሮ እየያዙ እዚያ ሸንጐ ላይ ሲውሉ ይታያሉ:: እንዲህ ዓይነቱ ሸንጐ ጌታችንን ከሰቀሉት ከአይሁዳውያን ሸንጐ ተለይቶ አይታይምና የሰንበት ቀን ቀጠሮአቸውን በሌላ ቀን አድርገው ሰንበትን ይቀድሱአት ዘንድ ቢያስቡ መልካም ነው::

*ፍሬ ሰንበት ኃ/ማርያም*
*(ሆሳዕና*

## ተጠቃሚዎች ያድርገን

የአብነት ትምህርት ቤቶች ለኢትዮጵያ ያበረከቱት አስተዋጽኦ በቃላት የሚገለጽ አይደለም:: ይሁንና የእነዚህን የሕይወት ትምህርት ቤቶች ህልውና የሚፈታተኑ ነገሮች ከዘመን ዘመን እየተበራከቱ መጥተዋል:: ድሮ ድሮ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ማለትም ጐጃም፣ ጐንደር፣ ትግራይ፣ ወሎና ከፊል ሸዋ የቆሎ ተማሪ የሚማረው ወንዝ ሸንተረሩን አቋርጦ ተጉዞ «በእንተ ማርያም ስለ እመ አምላክ ብለው» ብሎ ቁራሽ ለምኖ ነበር:: አሁን አሁን ግን በተለይ በከተማ አካባቢዎች ያ ትውፊት እየጠፋ የመጣ ይመስለኛል:: በከተማ እንኳንስ ትውፊቱ የትውፊቱ ተረካቢ የሆኑ የአብነት ተማሪዎችም የሉም:: እንደምንስ ማው ተማሪ ቤት ሄድን ብለው ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው አዲስ አበባ ካለምንም ሥራ የሚዞሩ የባላገር ወጣቶች ተበራክተዋል:: የአብነት ትምህርት ቤቶች ጠፉ ማለት'ኮ ቤተክርስቲያን ተረካቢ አገልጋይ አጣች ማለት ነው:: ስለዚህ የዚች ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ልጅ የሆነ ሁሉ እየጠፋ ላለው ለዚህ ትውፊት ተቆርቋሪ በመሆን የእምነታችን የትውፊታችን ተጠቃሚዎች ያድርገን::

*ከንድነህ ወ/ሰንበት*
*ከማሺ*

## እየተከታተልን

የቤተክርስቲያንን ፍትፍት በልተውና ትምህርቷን ተምረው ካደጉ በኋላ መልሰው የሚ ክዷት የእናት ጡት ነካሾች እየተ በራከቱ መጥተዋል:: ይህ ሊሆን የግድ ነውና አይደንቀንም:: የሆነው ሆኖ እነዚህ መናፍቃን ዕለት ዕለት አመጣጣቸውን እየቀያየሩ እንደመምጣታቸው እኛም አካሄዳቸውን እየተከታተልን ልንቋቋማቸው ይገባል:: እነዚህ እኔ ባለሁበት አካባቢ አንድ መሪጌታ ነኝ ባይ በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች በተለይ በሰሜን ባሉ እየተዘዋወረ አንድ ጊዜ መሪጌታ እንባቆም፣ ሌላ ጊዜ መሪጌታ እንቁ ባሕርይ ሌላ ጊዜ ደግሞ መሪጌታ ድልበድል እያለ ወደ አባቶች በመቅረብ የዕውቀት ምንጭ የሆኑ ልዩ ልዩ መጻሕፍት በመቀበል ብራናውን እየፋቀ የኑፋቄ ትምህርቱን የሚጽፍ መናፍቅ እንዳለ ደርሰንበታል :: ስለዚህ ፍቁረ ጥበብ ሰሎሞን «ወይናችን አብቦ አልና የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮዎች አጥምዱችሁ ያዙልን» እንዳለው በተለሳለሰ አንደበትና ማንነታቸውን ሰውረው በያዙት የዲቁና መአርግ እየተጠቀሙ ብዙ የጥፋት ሥራ እየሠሩ ነውና ሕዝበ ክርስቲያን በያለንበት ሆነን ልንከታተላቸውና ልንመነጥራቸው ይገባል እንላለን::

*የደባርቅ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም*
*ሰንበት ት/ቤት*
*ሰ.ጐንደር/ደባርቅ/*

## ከማን ወገን ይሆን?

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስር በሚተዳደረውና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኘው የዮሴፍ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ተከሰተ የተባለውን አሳፋሪ ድርጊት በሰኔ ወር አጋማሽ ላይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በፖሊስ ፕሮግራም ሲተላለፍ ተመለከትኩ:: በፕሮግራሙ በቤተክርስቲያኑ የሚገኙ ሰዎች የድሃውን ትኩስ ሬሣ በማውጣት ሳጥኑንና ጉድጓዱን ለሀብታሞች እንደሚሸጡ በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፈ ዘገባ በተከታታይ ቀርቧል:: የተለያዩ ሰዎችም ወደ ቴሌቪዥን ጣቢያው በመቅረብ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል:: በእውነቱ እጅግ አዝኛለሁ:: ለመሆኑ ድርጊቱ ከእኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጸመ ነው ወይስ በመናፍቃን የተቀነባበረ ሴራ? እንደእኔ እንደእኔ የቤተክርስቲያን ሰዎች ይህንን አይፈጽሙም:: በእውነት ይህ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን የሌላትን ስም የሚያሰጣት ነውና የሚመለከታቸው ሁሉ ተከታትለው እውነቱን እንዲያወጡ እላለሁ::

*አቶ ዳንኤል*
*ከሊሙ ሻይ*

## ገጠመኜ

*ድካሜንና ትንሽነቴን ሳይመለከት እግዚአብሔር በሰጠኝ ፀጋ እዚህ አዲስ አበባ በተለያዩ ጉባኤያት እየተዘዋወርኩ ቃለ እግዚአብሔርን እሰማለሁ:: እስተምራለሁ:: ታዲያ ምንም እንኳን በእንደዚያ ዓይነቱ ጉባኤ ተገኝቼ ባላውቅም አንድ ቀን ሀብታሞች የሚባሉ ሰዎች ከተሰባሰቡበት የጽዋ ማኅበር ተገኝቼ ሳስተምር የጉባኤው ታዳሚዎች አልፎ አልፎ ምንጥቅ ብሎ ወጥቶ ቆይቶ መግባት ሀሳቤን እየሰረቀው መጣ:: ምናልባት አራት አምስቱ ካልሆኑ በስተቀር ሁሉም እንዳውም ሁለት ሦስቴ ደጋግመው ወጡ፤ ገቡ:: የሁሉንም ባለሰማ ወደ ፊት የተቀመጡት ጉባኤተኞቹን የሚያስነሣቸው እንዳች ቅጭልጭል የሚል ድምፅ ነው:: ቅጭልጭል ሲል ኪሳቸውን እየደባበሱ ወደ በር ይሮጣሉ:: በዚያ ሁኔታ እንዳለሁ በነገሩ መረበሼን ከፊቴና ከአነጋገሬ የተረዳው አንድ ወንድሜ ቀስ ብሎ መጣና በጆሮዬ «እይዞህ ሰዎቹ የሚወጡት በያዙት ሞባይል የስልክ ጥሪ ስለሚደርሳቸው ነው» አለኝ :: ነገሩ ገባኝና የጀመርኩትን ጨርሼ ተቀመጥኩ::*

*ያሬድ*
*ከአዲስ አበባ*

/የሽፋን ፎቶ መታፈሪያ/

*ሴት ከወንድ እኩል ናትን? ብለን ከምንነሣ ሴት ከወንድ በምን ታንሳለች? ብለን ብንጠይቅ የተሻለ የሆናል፡፡*

*ትምህርተ ሃይማኖት*

---

*እና ሰዎች ተሳስተን ገሃነም ብንገባ ምን ትጠቀማለህ? ለምን አትተወንም?*

*ኪነ ጥበብ*

---

አንድ ጊዜ አንድ የአካባቢው «ጉልበታም» ሰው ገድሎ ከበዓል አክባሪዎች ጋር ተቀላቀለ፡፡ ሰላማዊ ለመምሰል፡፡ ምእመናኑ ወደ አጣብቂኙ በዕልልታ በዝማሬ ሲመጡ ተከትሎ መጣ፡፡ «ሰው መሳይ በሸንጎ» ሆነና አጣብቂኝ ውስጥ ገባ፡፡ የድፍረቱ ድፍረት ከነመሣሪያው፡፡

እናስተዋውቃችሁ

አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ለጽድቅም ለኃጢአትም «ባሪያ» ሲሆን አይችልም፡፡ ለሁለቱም ሳይሆኑ መኖር የሚባል ነገርም የለም፡፡ ምርጫው ሁለት ነው፡፡ ከኃጢአት ባርያ፡፡ ሆኖ ራስን ከጽድቅ ባርነት አርነት ማውጣት ወይም ለጽድቅ ባርያ ሆኖ ራስን ከኃጢአት ባርነት ነፃ ማውጣት

ዓምደ ወ ራዙት

---

*ቦታዎ ምንድን ነው /የት ነው? በት/ቤት፣በሥራ ቦታ፣በጓደኞችዎና በኅብረተሰቡ ዘንድ ቦታዎ የት ነው? በቤተክርስቲያንስ ያለዎት ቦታ ምንድ ነው?*

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

---


**ዋና አዘጋጅ ግርማ ወ/ሩፋኤል**
**ም/ዋና አዘጋጅ – መርሻ አለኸኝ**
**ስልክ** 556328
**ፖስታ** 80078
**አዲስ አበባ**

E-mail-EOC -M- kidusan @ tel .com.net.et.



# ሐመር

7ኛ ዓመት ቁጥር 4

ነሐሴ/ መስከረም 1992 ዓ.ም.


## ይዘት


**የማኅበሩ መልእክት**

ክርስቲያኖች አገራቸውን ከድህነት የማላቀቅ ኃላፊነት አለባቸው.......................2

**ደብዳቤዎች**...................................................5

**በረከተ ወንጌል**

- ወደ ሰማይ ተመልከት.........................7

**ትምህርተ ሃይማኖት**

- ነገረ ድኅነት....................... ..........9
- እኩል ናችሁ ሲል ከጐኑ ፈጠራት........12

**ምዕራፍ** ............................................ 15

**የጥያቄዎች መልስ** .................................16

**እናስተዋውቃችሁ**

- አባ ዮሐንስ ............ ....................18
- ከደብረ ብርሃን እስከ. .. ..............19

**ኪነ ጥበብ**

- ከሰይጣን ቃል የተደረገ ቃለ መጠይቅ ...........................21

**ዓምደ ወራዙት**

- መንፈሳዊነት ነፃ ለመሆን ከመፈለግ ጋር ሲከራከር ....... ...................23

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**

- ቦታህ የት ነው?...........................25
- ራሴን ባጠፋ እኮነናለሁ................28
- ስለ ሁለት ነገሮች ተጨንቄአለሁ ........................ .......29

**ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ**

- የቅኔ መንገድ........................ ......30



*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ፡፡*

## የማኅበሩ መልእክት

# ክርስቲያኖች አገራቸውን ከድህነት የማላቀቅ ኃላፊነት አለባቸው

በተለያዩ ዘመናት ለሥራ ከነበራቸው ከፍተኛ ፍቅር የተነሣ የተወሰኑ ሀገሮች የበላይነት ያሳዩ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ:: ሀገራችን ኢትዮጵያም ከእነዚህ ሀገሮች መካከል አንዷ እንደነበረች ሕያው ሆነው የቆሙት፣ እንደ ዕንቁ ፈርጥ የሚያበሩት የሥራ ውጤቶቿ ዛሬም ይመሰክራሉ:: ያኔ እንደዛሬው በረሃብና በችግር ሳይሆን በተራቀቀ ሥልጣኔዋ ነበር የምትታወቀው:: ጥንት የሥልጣኔ በር ከፋች የነበረችው ሀገራችን ዛሬ የት ናት? ለምን?

እውነት ለመናገር ከሆነ ዛሬ ሀገራችን ዓለም የደረሰበትን ሥልጣኔ በርቀት ከሚታዘቡት ሀገሮች መካከል አንዷ ናት:: በሥልጣኔ ወደ ኋላ መቅረት ብቻ ሳይሆን በረሃብና በበሽታ አለንጋ ከሚገረፉት የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች ዋነኛዋ ሆናለች:: እነዚህ ሀገሮች ከምዕራባውያን የሚሰጣቸውን ርዳታ እንደ መብት እየቆጠሩት መጥተዋል:: በየዓመቱ በጀት ሲመድቡም የሚያገኙትን ብድር ወይም ዕርዳታ በመተማመን ነው:: መክፈል ካቃተን የዕዳ ስረዛ ይደረግልናል ብለው የሚያስቡም አይጠፉም::

ርዳታ ከተለመደ ሠርቶ ማደር ይዘነጋል:: ሥራ ከተዘነጋ ደግሞ ሌላ መዘዝ ይመጣል:: ሥራ የፈታ አእምሮ ከበጐ ይልቅ የሚታየው ክፉ መሥራት ነው:: «ሥራ ከምፈታ ልጄን ላፉታ» የሚለው ብሂል ይህንን ያጐላልናል:: ለዚህም የሥራ ባሕል ባልዳበረባቸው ሀገሮች ውስጥ በጦርነት መቆራቆስ የበዛ ነው::

የዛሬውን አያድርገውና የኢትዮጵያ ሕዝብ በዓለም የሚታወቀው በርትዕት ሃይማኖቱ፣ በጀግንነቱና በሠራተኛነቱ ነበር:: ሥራን ፈጥሮ መሥራት ለኢትዮጵያውያን እንግዳ አይደለም:: በምሕንድስናው ዓለም ምሥጢራቸው ያልተደረሰበት የላሊበላ አብያተ መቅደስ እና የአክሱም ሐውልቶች ለዚህ አባባላችን ቀጥተኛ ዋቢ ናቸው::

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቅኝ አልተገዛችም:: ስለሆነም በከርሰ ምድሯ ያለውን ሀብቷን ማንም አልወሰደባትም:: «የአሥራ ሦስት ወር የተፈጥሮ ጸጋ» ያላት ለምለም ሀገር ናት:: ወንዞቿ ከራሷ አልፈው ለጐረቤቶቿ የኑሮ መሠረት ናቸው:: እንዲያውም አጥኚዎች የምሥራቅ አፍሪካ የውኃ ምንጭ «The water tower of East Africa» ብለው ይጠሯታል:: በቀንድ ከብት ብዛት ከዓለም አሥረኛ ከአፍሪካ ደግሞ አንደኛ መሆኗ ይነገራል::

እነዚህና ሌሎችም በርካታ ሀብቶች ያሏት ሀገር ብትሆንም ድህነት በተነሣ ቁጥር ኢትዮጵያ የማትታሰብበት ጊዜ የለም:: የዛሬው ዓለም ኢትዮጵያን የሚያውቃት በረሃብ እየሆነ መጥቷል:: ፈረንጆች በመዝገበ ቃላታቸው «ረሃብ» (famine) ለሚለው ቃል የሚሰጡት ትርጉም ኢትዮጵያን ምሳሌ ያደረገ ነው::

ሀገራችን በተፈጥሮ ጸጋ ሀብታም ከሆነች ለምን ትራባለች? ድህነቱንስ ምን አመጣው? ምናልባት አንዳንድ ሰዎች እንደሚያስቡት «የእግዚአብሔር ቁጣ» ነውን? አይደለም:: በእርግጥ ሕገ እግዚአብሔርን ስንተላለፍ እግዚአብሔር አይቀጣንም ማለታችን አይደለም:: በየጊዜው በረሃብ አለንጋ ለመገረፋችን ግን ዋነኛው ምክንያት እግዚአብሔር ስለፈረደብን አይደለም:: እንዲያውም ዛሬም ቢሆን ከሌላው ዓለም በተሻለ እግዚአብሔር የሚመሰገንባት ሀገር ኢትዮጵያ መሆኗ አያጠራጥርም:: የችግሮቻችን መንስኤዎች በርካታ ናቸው:: ዋና ዋናዎቹ ግን ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው::

1. <u>የሥራ ባሕል መጥፋት</u>:- ከፍ ብለን እንደተናገርነው ኢትዮጵያውያን ጥንት ራሳቸውን ከመመገብ አልፈው በጥበብ ሥራዎቻቸው የታወቁ ነበሩ: እንደዚህ ያለው የሥራ ባሕል ዛሬ እየከሰመ መጥቷል:: በአዲስ አበባ ጎዳናዎች በየጥቂት እርምጃዎች ርቀት የሚታዩት እርዳታ ጠያቂዎች ለዚህ ማስረጃዎች ናቸው:: በተማረው ኅብረተሰብም በኩል ሥራ ለመሥራት የግድ የተቋም ሰርተፊኬት እንደሚያስፈልግ የተወሰነ ይመስላል:: ወረቀት ካልጨበጠ፣ በዚህ ሙያ የተመረቀ ካልተባለ ሥራ ያለ የማይመስለው የኅብረተሰባችን አካል እየተበራከተ ነው:: ይህንን ዕድል የሚያገኙት ደግሞ እጅግ በጣም ውስኖች ናቸው:: በየዓመቱ አሥራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከሚፈተኑት ወደ 200 ሺህ ከሚሆኑ ተማሪዎች ውስጥ ለቀጣይ የትምህርት ደረጃ የሚያልፉት ጥቂቶች ናቸው:: በዚህም የተነሣ አብዛኛው ወጣት በሥራ አጥነት ሲጉላላ ይታያል::

እነ ቅዱስ ላሊበላ የምሕንድስና ትምህርት ምሩቃን ስለነበሩ አይደለም እነዚያን የመሣሠሉ የሚያስደንቁ ሥራዎች የሠሩት! ዛሬ ግን ወረቀቱ የእርሱን ሥራ የሚሠራለት ይመስል ያለው እርሱን ይዞ የሌለው ደግሞ ሐሰተኛ መረጃ (forged) አሠርቶ ከወዲያ ወዲህ ሲመላለስ ጊዜውን በከንቱ ያባክናል:: «የዕድሌን አላጣ» እያሉ የዕድሜን ግማሽ መግፋትም ተለምዷል::

➡

በእያንዳንዱ ሰው ግቢ ያለው ባዶ መሬት የሥራ ያለህ የሚል መሆኑን መገንዘብ የቻለ ያለ አይመስልም:: በመጀመሪያ መሬት በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በድካም ከእርሷ ይበላ ዘንድ ለአዳም የተሰጠችው መሆኗን በመዘንጋት የግድ የደመወዝ መቀበያ ቅጽ ላይ ካልተፈረመ ሥራ የለም ብሎ መቀመጥ አይገባም:: ሌሊቱ በነጋ ቁጥር «ጊዜዬን በምን ላሳልፈው?» ከማለት «ምን ስሠራ ልዋል?» ወደ ማለት መምጣት ያስፈልጋል::

አንዳንዶች እንደሚናገሩት «ካናዳ ይዝነብ እንጂ...» እነርሱ እጅና እግራቸውን አጣጥፈው ይቀመጣሉ:: ሌሎች ደግሞ አንድ ሰው አዲስ ሥራ ፈጥሮ መሥራት ሲጀምር ያንኑ ሰው ተከትለው ያንኑ ሥራ መሥራት ይመርጣሉ:: ይህም የሥራ ፈጣሪውንም ሆነ የእነርሱን ኑሮ ያዳክማል:: አንዱ ሆቴል ሲከፍት ሌሎች ተከትለው ያንኑ የሚከፍቱ ከሆነ፣ አንዱ ሱቅ ሲከፍት ሌሎችም ተከታትለው አጥራቸውን የሚቀድዱ ከሆነ ምኑን ሥራ ተሠራ? ይኸ ሁሉ ችግር የሥራ ባሕል ባለመኖሩ የሚከሠት ነው::

2. <u>ሥራ መናቅ</u>:- «ትለብሰው የላት ትከናነበው አማራት» እንዲሉ ዛሬ ከሚወደደው የሥራ መስክ ይልቅ የሚጠላው እና/ወይም የሚነቀፈው የሥራ ዘርፍ ይበዛል:: «የእገሌን ዓይነት ሥራ ከምሠራስ ለምኜ ባድር ይሻለኛል» የሚለው «አህያ የሌለው በቅሎ ይን ቋል» ዓይነት አስተሳሰብ በብዙዎች ዘንድ ይንጸባረ ቋል:: በዚህም የተነሣ በሀገሩ ምድር ያገኘውን ሠርቶ ከመክበር ይልቅ በሰው ሀገር ሄዶ ባሪያ መሆንን ይመርጣል:: የኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤትን አጣብቦ የሚታየው እንደዚህ ያለው ወገናችን ነው:: «ኢትዮጵያ ውስጥ ሰው ሆኖ ከመፈጠር ውጭ አገር እንስሳ ሆኖ መፈጠር ይሻላል» ባዩ በዝቷል:: ሥራ ጠፍቶ ሳይሆን ሥራ ፈርቶ ወይም ንቆ ማለቱ ይቀላል::

3. <u>አስተዳደር</u>:- በሀገራችን ያለው የመሥሪያ ቤቶች የአስተዳደር ሥርዓት መበላሸት ለሀገሪቱ ድህነት ዋነኛ ተጠቃሽ ነው:: አንድ ሰው ሥራ እየሠራ ነው የሚባለው በሰዓት መቆጣጠሪያ ሠንጠረዥ ላይ ፊርማውን ስላስቀመጠ አይደለም:: በሰዓቱ ገብቶ ራሱም ሳይሠራ የሚሠሩትንም ጥቂቶች ሰዎች ስሜት ሲጐዳ እየዋለ በሰዓቱ የሚወጣውን ማን ተመለከተ? በመደበኛው የሥራ ሰዓት መሥራት የሚጠበቅበትን ባለመሥራት የትርፍ ሰዓት ሥራ ሠርቶ ገንዘብ ለማግኘት የሚሯሯጠውስ? ይህ ሰው ሠርቶ አገኘ ሳይሆን «በሕጋዊ መንገድ ሰረቀ» ቢባል ይመረጣል::

አንዳንድ ሀገር ወዳዶች በእውነተኛ ፍቅር ሀገራቸውንና ወገናቸውን ለማገልገል የተቻላቸውን ለማድረግ ሲሞክሩ ከበላይም ከበታችም «ጦር ይሰበቅባቸዋል»:: ለዚያውም መንግሥት የሚከፍላቸው ክፍያ አናሳ በመሆኑ እያንዳንዱ መሥሪያ ቤት ባዶ እየሆነ መጥቷል:: የሥራ መመዘኛው ወረቀት ብቻ መሆኑም በዘመድም በሀሰተኛ መረጃም ተሯሩጠው የሥራ መድረኮችን የሚያንቁ ሰዎችን አብዝቷል:: ሥራውን እንዳይሠሩ ለቦታው አይመጥኑም ተቀምጠው የደመወዝ ቀን ለመቁጠር ግን አያንሱም:: ሠራተኞች ሳይሆን ተመልካቾች ይመስላሉ:: ሥራ የመሥራት ችሎታ ወይም ባሕል ስለሌላቸው ከወዲያ ወዲህ ወሬ በማቀባበልና «በማጣፊጥ» የብዙዎችን ሕይወት ያበላሻሉ::

በሌላም በኩል በየመሥሪያ ቤቱ የፈጣሪ ያህል የሚፈሩ አለቆች በመኖራቸው ተወያይቶ ሥራን ከመሥራት ይልቅ እነርሱ ያሉትን ብቻ ለመፈጸም መራወጡ በራሱ ጉዳት አለው:: «አለቃ አይሳሳትም» ወይም «ከእርሱ በላይ ጥሩ ሐሳብ ማመንጨት አይቻልም» የተባለ ይመስል በበርካታ ቦታዎች የባሪያና የጌታ ዓይነት ግንኙነት ተስፋፍቷል::

መሥሪያ ቤቱ የጣለበትን ኃላፊነት ወደጐን በማለት ታማኝነቱን የሚያጐድፍ፣ ባለጉዳይን ካላጉላላ አለቅነቱ የማይታወቅለት የሚመስለው÷ወፍጮ ከምትፈጨው፣ ቆሎ ከምትሸጠው እንኳን ሳይቀር ጉቦ ካልተቀበለ ኃላፊነቱን የተወጣ የማይመስለው፣ ለትንሹም ለትልቁም ስብሰባ በመጥራት የራሱንም የሠራተኛውንም የሥራ ጊዜ የሚያባክን፣ ባለጉዳይ በሄደ ቁጥር «የለም» የሚባልለት፣ በመንግሥት ቢሮ ውስጥና የሥራ ሰዓት የግል ሥራውን «የሚሠራው» ቁጥሩ ቀላል አይደለም::::

4. <u>ባለሀብቶች</u>:- ባላቸው ገንዘብ ራሳቸውንም ሀገራቸውንም ለመጥቀም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ የሚገኙ ባለሀብቶች አሉ:: በተቃራኒው ደግሞ ካላታለሉ መክበር የማይቻል የሚመስላቸው፣ ስማቸው በሀብታቸው ብዛት የገነነ ጥቂት አይደሉም:: የታይዋኑን ዕቃ የእንግሊዝ ነው ካላሉ እንደማይሸጥላቸው በማመን ኅብረተሰቡን የሚያታልሉ፣ በአግባቡ የሚሠራውን ሰው ጉቦኛነት የሚያስተምሩ፣ ሁሌ ካልቀደሙ እንደተበደሉ የሚቆጥሩ.. በርካታ ናቸው:: አንዳንድ ድርጅቶችንም ቢከፍቱ መቅጠር የሚፈልጉት በዘመድ አዝማድ የመጣውን ብቻ በመሆኑ ለራሳቸውም ለወገኖቻቸውም የጉዳት መንስኤዎች ይሆናሉ:: እንደዚህ ያለ አስተሳሰብ ይዞ ለሀገር ዕድገት ማሰብ ይከብዳል::

5. <u>የሀገር ፍቅር</u>:- አንድ ጊዜ ከራሱ ጣሪያ አልፎ ስለወገኑ ስለሀገሩ ማሰብ ካልቻለ ከራስ ወዳድነት አረንቋ ሊወጣ አይችልም:: የቀደሙ አባቶችን ጠላት ቢመጣባቸው በውስጣቸው የሚቀጣጠለው የሀገር ፍቅር ስሜት አንድ አድርጓቸው ሕይወታቸውን ሰውተው፣ አጥንታቸውን አጥር ቅጥር አድርገው ለእኛ አስረከቡን:: ዛሬም ይህ ስሜት ሊጐለብት ይገባል::

እያንዳንዱ ሰው በከንቱ የሚያሳልፈው ጊዜ ራሱን ብቻ ሳይሆን ሀገሩን እንደሚጐዳ ማሰብ አለበት:: ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ ሥራ ሳይሠራ ደመወዝ የሚበላው የራሱን የላብ ዋጋ ሳይሆን፣ የወሰደው በችግር አለንጋ እየተገረፈ ቀንና ሌሊት እየለፋ ለሀገሩ ግብር የሚገብረውን የገበሬውን ደም ነው የጠጣው:: ከየቤቱና መሥሪያ ቤቱ ጥሩ ሰው ካልወጣ ለሀገር ማሰብ ከየት ሊመጣ?

➡

የሀገሩ በድህነት መውደቅ፣ የወገኑ መራብ፣… የማይታየው ሰው የሀገር ፍቅር የለውም:: ይህንን ማየት ከቻለ ግን ሀገሩን ለመታደግ በታማኝነትና በታታሪነት ወደ ሥራ ዓለም ይሠማራል:: አንዱ ሲሰርቅ የሀገር ንብረት እንደሰረቀ ስለሚያውቅ በሽፍንፍን አያልፈውም ወይም ከርሱ ጋር አይተባበርም::

ከላይ ከተዘረዘሩት ችግሮች በተጨማሪ ሌሎችም ተደማምረው ሀገራችንን ወደ ድህነት አዘቅት ከትተዋታል:: ይህንን ሥር የሰደደ ችግር ከሥረ መሠረቱ መንግሎ ለመጣል ከአሁን የተሻለ ጊዜ እንደሚኖር መጠበቅ የለብንም:: ከትናንት ብንዘገይ ከነገ ለመቅደም መነሣሣት ይጠበቅብናል::

ሀገራችንን ከድህነት ለማውጣት ቤተክርስቲያን እንደጥንቱ ሁሉ ዛሬም ቀዳሚዋ ተሰላፊ ልትሆን ይገባል:: ልጆቿ ሠራተኞች ናቸው:: በተለያየ የሥራ መስክ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ከልጆቿ የተሻለ ይገኛል ለማለት አንደፍርም:: ሥራ ፈትነት፣ ጉቦኝነት፣ አድሏዊነት፣ ንዝህላልነት፣ ግዴለሽነት፣ ምዝበራና ሌሎችም የሥራ እንቅፋቶች ውጉዝ ናቸው:: ስለዚህም በትምህርቷ አካትታ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ስለ ሥራ ማስተማር የቤተክርስቲያን ድርሻ ነው:: ዛሬም በየመሥሪያ ቤቱ ኃላፊነታቸውን በአገባቡ የሚወጡ ሠራተኞችን በማፍራት ላይ መሆኗ ይበል ያሰኛል::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን «ሥራ ፈትታችሁ ቀኑን ሙሉ ስለምን ቆማችኋል?» ሲል እንደወቀሳቸው ሥራ መፍታት በክርስቲያኖች ዘንድ ቦታ የለውም:: የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት የተሳነው ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ይጠየቅበታል:: መብላት ያለበት ሁሉ መሥራት ይገባዋል:: ለዚህም ነው ሐዋርያው «ሊሠራ የማይወድድ አይብላ» ሲል የተናገረው:: ሥራ ሳይሠሩ «እግዚአብሔር ያው ቋል» እያሉ በማሳበብ እጅና እግርን አጣጥፎ በመቀመጥ የሚገኝ ነገር የለም:: ሥራን በአግባቡ መሥራት በራሱ ወደ ጽድቅ የሚመራ ጎዳና ነው:: ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ «ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፣ መልካም ሥራን ከመሥራት አትታክቱ» በማለት የሚመክረን:: እያንዳንዱ መንፈሳዊ ሰው ከማንኛውም አካል የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ መወጣት አለበት:: ለመጽደቅ እንደሚጾም እንደሚጸልይ፣ እንደሚመጸውትና እንደሚሰግድ ሁሉ ሥራውንም በብቃትና በጥራት መሥራት ይጠበቅበታል:: ክርስቲያን ባለሀብቶችም በቤተክርስቲያን አካባቢ ያለውን ጥሬ ሀብት (resource) ተጠቅመው ቢሠሩ የተሻለ ውጤት ያገኛሉ::

ቤተክርስቲያን ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል አላት:: ታማኝነት ያለው ሰው ማግኘት በሚያዳግትበት ወቅት ለዚህ የሚበቁ ሰዎች ባለቤት ናት:: ከእነዚህ ጋር መሥራት ለራስ፣ ለሀገር ለወገን የሚያበረክተው ጠቀሜታ ቀላል አይደለም:: በምግባረ ሃይማኖት ከተኮተኮተ፣ በሀገርና በወገን ጽኑዕ ፍቅር ከተጠመደ ሠራተኛ ኃይል ደግሞ ብዙ ነገር ይጠበ ቃል:: በተለይም ሀገራችንን ከድህነት አረንቋ መንጥቆ ለማውጣት ኃይሉ፣ ጉልበቱ፣ ፈቃዱ አቅሙ አለው ና::

ወገናችን ከተራብ በኋላ ለመመጽወት እጃችንን ከምንዘረጋ ከመራቡ በፊት ሠርቶ እንዲበላ ወይም ከምንፈራው አደጋ እንዲድን ማድረግ ይጠበቅብናል:: ይህም የቤተክርስቲያን አደራ ነው:: ዓመት በዓል በመጣ ቁጥር ነዳያንን ለመመገብ እጅግ ከፍተኛ ወጪ ከማውጣት ያንኑ ገንዘብ ራሳቸውን የሚችሉበትን ፕሮጀክት ነድፎ መጠቀም ቅድሚያ የሚሰጠው ቢሆን ይመረጣል:: ሁልጊዜ ማብላት ብቻ ከሆነ ግን በተ ቋሚነው የተመጽዋቹን ቁጥር ከፍ ማድረግ ይሆናል:: ቤተክርስቲያን ስለ ሥራ እያስተማረች ደግሞም የሥራ መስክ እየፈጠረች ብትሄድ እጅግ ያማረ ይሆናል::

መንግሥትም በበኩሉ እውነተኛ ሠራተኞችን ሊያበረታታበት የሚችልበትን መንገድ መቀየስ ያስፈልገዋል:: ለምሳሌ ተማሪዎች ስለ ሥራ ክቡርነት እና ስለሀገራቸው ፍቅር እየተማሩ እንዲያድጉ በሥርዓተ ትምህርት ቢካተት መልካም ይሆናል:: ኅብረተሰቡም ሀገሩን ተባብሮ ማሳደግ እንዲችል የተለያዩ መድረኮች ሊከፈቱለት ይገባል:: ለምሳሌ ከውጭ ሀገር ለሚመጡ ሸቀጣ ሸቀጦች ቅድሚያ ከመስጠት ይልቅ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃዎች ደረጃቸውን እንዲጠብቁ ማገዝ እና ተጠቃሚው ኅብረተሰብም ወገኑ የሆኑ አምራቾችን መጥቀም እንዲችል ራሱም በቀላል ወጪ የሚፈልገውን እንዲያገኝ ማድረግ ተገቢ ነው::

ወላጆችም ልጆቻቸውን በሚገባ ኰትኩተው የማሳደግ ኃላፊነት አለባቸው:: «እገሌን ምታ እገሌን ስደብ» እያሉ ከማሳደግ ይልቅ ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲኖራቸው ቢያደርጉ ስለ ሥራ ክቡርነት፣ ስለ ሀገር ፍቅር እያስተማሩ ቢያሳድጓቸው ነገ ለራሳቸውም ለሀገራቸውም የሚጠቅሙ ብቁ ዜጋዎችን ማፍራት ይችላሉ::

እነዚህንና ሌሎችንም መፍትሔዎች በመያዝ ሀገራችንን ከገባችበት የድህነት ማጥ ለማውጣት ጊዜው አሁን ነው:: እያንዳንዱ ክርስቲያን ሥራ ሳይንቅ ከሠራ እግዚአብሔር በረከቱን ይሰጣል:: በማንኛውም የሰው ልጅ ጉዞ ውስጥ የእግዚአብሔርና የራሱ የሰው ልጅ ድርሻ አለ:: ሰው የዐቅሙን ያህል ከሠራ እግዚአብሔር ይባርክለታል:: ሰው አርሶ ቆፍሮ ዘርቶ እንደሆነ እግዚአብሔር ጠለ ምሕረቱን፣ እክለ በረከቱን ይሰጣል:: ቁጭ ብሎ እግዚአብሔርን በማማረር እና «የአርባ ቀን ዕድልን» በመርገም የሚገኝ አንዳች ነገር የለም::

ሌላው ሀገር በረሃውን እያለማ እኛ በለምለሟ ሀገራችን ሠርተን ረሃብንና ድህነትን ማስወገድ ካልቻልን ምን ይባላል? ይህ ደግሞ ምንጭ አጠገብ ቆሞ ውኃ ጠማኝ እንደማለት ነው:: መጽሐፍ «ታምነህ ተሠማራ» እንዳለ ለፈጣሪና ለሀገራችን ታምነን ከተሠማራን ከምንጠላው ድህነት እግዚአብሔር መንጥቆ ያወጣናል:: ሁልጊዜ ድህነትን ማውገዛችን በራሱ የሚያመጣው ለውጥ የለምና::

*ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን::*

# ደብዳቤዎቻችሁ

## ... መባሉ ቅዱስ አያደርገውም

ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል፣ እነዚህ ጊምቢ ያሉ የማኅበራችሁ አባላት ድርጊት እጅግ ቢያሳዝነኝ ይህን ደብዳቤ ጻፍኩላችሁ:: ነገሩ እንዲህ ነው፣ እዚህ ያሉ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ደንብና ሥርዓት እየታተመ የሚወጣውን መለከት መጽሔት እንዳይሸጥ እያደረጉ ይገኛሉ:: በተመሳሳይ ሁኔታ የሚታተመው ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣም እየተቋረጠ ይገኛል:: ይህን የሚያደርጉት ለምን እንደሆነ ስንጠይቃቸው ሐመር መጽሔት እንደሚበልጥና የሚዘጋጀ ውም ዲግሪ በጫኑና በምሁራን እንደ ሆነ ይሰብኩንና አፋችንን ያስይዙናል:: በዚህም ከእነሱ አልፈን እናንተን ከመጠራጠር ደረጃ ደርሰናል:: አንድ ሰው ዮሴፍ ወይም ኤፍሬም የሚባል ስም ቢወጣለት የእነሱን ምግባር ቅድስና ካልተከተለ ዮሴፍ ወይም ኤፍሬም መባሉ ቅዱስ አያደርገውም:: በተረፈ መልእክቴን በቅን ልቡና እንድትረዱት እግዚአብሔር ይርዳችሁ::

*ኃይሉ ኢየሱ*
*(ጊምቢ–ወለጋ)*

<u>ከአዘጋጁ:-</u> አቶ ኃይሉ በመጀመሪያ ረጅሙ ደብዳቤዎትን በማሳጠራችንና የጠነከረውን በማለዘባችን ይቅርታ እንጠይቃለን:: ከዚህም ጋር የእርስዎ ዓይነት ይዘት ያለው ደብዳቤ ሲደርሰን ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑን ልንገልጽልዎት እንፈልጋለን:: በርካታ አንባብያን እንደሚያውቁት እኛና የመለከት መጽሔት ዝግጅት ክፍል ዓላማችን አሠራራችንና ውሉአችን አንድ ነውና:: የሆነው ሆኖ በየትም ቦታ ያሉ የማኅበራችን አባላትም እስከአሁን በዚህ ሲወቀሱ አልሰማንም:: ነገር ግን ምናልባት በጊምቢ ያሉ የማኅበሩ አባላት ያንን አድርገው ከሆነ ሊመከሩ ይገባል:: ነገር ግን ዉድ ወንድማችን ይህንን የመሰለ አስተያየት ሲሰጡ አስበውበት አይመስለኝም:: ይህም «ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣም እየተቋረጠ ይገኛል» በሚለው ዓረፍተ ነገር ይከሰታል:: ለመሆኑ ስምዐ ጽድቅ የምትታተመው በማኅበረ ቅዱሳን እንደሆነ ያውቃሉ? ለማንኛውም እግዚአብሔር ይስጥልን::

## ተምሬበታለሁ

በተከታታይ በሁለት እትሞች «የኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች የተቃራኒ ፆታ ግንኙነት» በሚል ርዕስ ከወጣው ጽሑፍ ብዙ ትምህርትን አግኝቼበታለሁ:: እንደእኔ ሁሉ ሌሎችም በተለይ በሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ወጣቶች ከፍተኛ ዕውቀት እንዳገኙበት ተረድቻለሁ:: ስለዚህ ወደፊትም በተቃራኒ ፆታዎች መካከል መኖር ስላለበት ግንኙነት የተለያዩ ጽሑፎችን ከመስጠት አትንፈጉን::

*ተስፋ አለኝ ጀምበ*
*(ከድሬዳዋ)*

## ዳግማዊት መምህሬ

ሐመሮች የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ሐመር መጽሔትን ስትጀምሩ ስለ ሥላሴ ሦስትነትና አንድነት የምታስተምረው ቁጥር ሁለት መጽሔት እጄ ገባች:: አነበብኳት:: ከዚያም በውስጧ የያዘችውን ምሥጢር ስመለከት የመጽሔቷ ደንበኛ ብሆን የበለጠውን ምሥጢር ማግኘት እንደምችል ገመትኩና የዓመቱን ክፍያ ፈጽሜ በፖስታ ቤት በኩል ያለሁበት ቦታ ድረስ እየተላከልኝ መጠቀም ጀምሬ ነበር:: በመሆኑም ሐመር ለቅኔ ትምህርት በጐጃም ክ/ሀገር በዞርኩበትና በታላቁ አባት በአለቃ ጥበቡ ገሜ ቅኔ ቤት እያለሁኝ ያገኘሁትን የቅኔ አገባብን፣ የውዳሴና ቅዳሴ ማርያምን ትርጓሜ ዕውቀት እንዳወጣው የመክስተ ስብከት ዘዴ ዕውቀትን አጐናፅፋኛለች:: በዚህ የተነሣ «ዳግማዊት መምህሬ» የሚል ስምን አውጥቼላታለሁ:: እናንተም ስንቅ ትጥቋን በማቀበል ትጉ እያልኩ ሥራችሁ ሁሉ የተቃና እንዲሆን ዘወትር እጸልያለሁ::

*አለቃ መዘምር ዳምጤ*
*(ገርበጉራቻ)*

<u>ከአዘጋጁ:-</u> እናመሰግናለን::ጥያቄዎትን ወደሚመለከተው ክፍል መርተናል::

## በጽሙና አነበብኳት

ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል፣ 7ኛ ዓመት ቁጥር 3 መጽሔትን በጽሙና አነበብኩት:: በመጀመሪያ በማኅበሩ መልእክት የቀረበው ጽሑፍ በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣችሁ የወጣና ድጋሚ ቢሆንም ሰሚና አስተዋይ ካለ እጅግ ጠቃሚ መልእክት ነው:: የማኅበሩን ማንነት የበለጠ እንድናውቀው ያላወቁትም እንዲያውቁትና ጥንቃቄ እንድናደርግ አድርጓል:: በበረከተ ወንጌል ዓምድም «ክርስቲያንነት» በሚል ርዕስ በጣም ጠቃሚ የሆነ ትምህርት ተላልፏል:: የወቅቱ የቤተ ክርስቲያን ችግር ነውና:: ከዚህ ሌላ በደብዳቤዎች ዓምድ ሥር በዲ.ተፈራ አበራ የተሰጠውን አስተያየት እጅግ አጥብቄ እደግፈዋለሁ:: አባቶች በሚጠየቁበት ጊዜ ጥያቄዎቹ ሀገረ ስብከታቸውን መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ በቅድሚያ ጥያቄዎችን ብትሰበስቡ ጥሩ ነው:: በተረፈ በሥራችሁ ሁሉ የአምላክ ርዳታ አይለያችሁ እላለሁ::

*መስፍን ሥራህብዙ*
*(አዲስ አበባ)*

## ነገረ ማርያም...

በ7ኛ ዓመት ቁጥር 2 እና 3 በተከታታይ ያቀረባችሁልን «ነገረ ማርያም በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ» በሚል ርዕስ የቀረበው ጽሑፍ በጣም ጠቃሚ ጽሑፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: የእመቤታችን ታሪክ ተጽፎ አያልቅም:: ከዚህም ተጽፎ ከማያልቀው ምስጋናዋ ጥቂቱን እንድናውቅ ስላደረገልን እግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ሰፋ ያለ ትንታኔ ግእዝን ከአማርኛ ጋር እያቀነባበሩ ላቀረቡልን ለመሪጌታ ዓምደ ወርቅ ስጢፋኖስ ምሥጋናዬን አቀርባለሁኝ:: ሌሎች ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም የመሪጌታ ዓምደ ወርቅን አርአያነት ሊከተሉ ይገባል:: ሌላው «ነገረ ድኅነት» በሚለው ርዕስም ያቀረባችሁልን ጽሑፍ እጅግ በጣም አስደሳች ነው:: አቅራቢውን አመስግኑልኝ:: በተረፈ ፍቅረ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን::

*ሥዩም ደስታ*
*(ደብረ ብርሃን)*

## ዕድሜ ይስጥልን

በ7ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትም ከብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ጋር ያደረጋች

ሁት ቃለመጠይቅ ልብ ይነካል። ብፁዕነታቸው ስለልማትና የወቅቱ የቤተክርስቲያን ሁኔታ የሚሰጡት አስተያየት አደራ አስረካቢ ትጉህ አባት መሆናቸውን ፍንትው አድርጎ አሳይቶናል። ከዚህ ሌላ ግን በሥጋ ከተለዩን አባቶች ተለይተው እንዴት ሊተርፉ እንደቻሉና በአባቶቻችንን ላይ የደረሰውን አደጋ ሁኔታ አስመልክተው የተናገሩት ንግግር እንደእኔ ሁሉ ሕዝበ ክርስቲያንን እንደሚያስለቅስ እርግጠኛ ነኝ። እውነትም እርሳቸው እንዳሉት የመትረፋቸው ሁኔታ ከእግዚአብሔር በቀር የሚያውቀው የለምና አሁንም አምላክ አበው ለእሳቸውም ሆነ ለቀሩት አባቶች ረጅም ዕድሜ የስጥልን።

*ትንቢተ ኢሳይያስ*
*ደብረብርሃን*

## ማንነታቸውን ያስረዳ

ሐመሮች፤ መጽሔታችሁን መከታተል ከጀመርኩኝ ሰነባበትኩ። ሐመር ትምህርታዊ እንደመሆኗ መከታተል ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ በሕይወቴ ላይ ታላቅ ለውጥ እንዲኖረኝ ረድታኛለች። ዛሬ ለመጻፍ ያነሣሣኝ በሰባተኛ ዓመት ቁጥር ሦስት እትማችሁ «የማኅበሩ መልእክት» ትምህርታዊና የተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችንን ታሪኳ፣ ባሕሏ፣ ቅርሷና ሃይማኖታዊ ሥርዓቷ ተጠብቆ እንዲኖር የሚያደርግ፣ በተጨማሪም ምእመናንን የመናፍ ቃንን ምንነት እንዲረዱ የሚያነሣሣ ጽሑፍ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ልጅ የሆነ ሁሉ ይህንን ሰይጣን የሸመቀውን ሴራ ለመከላከል ጭራሹንም ለማክሸፍ መትጋት አለበት እላለሁ። እናንተም ትምህርታችሁን ለወደፊቱ ከዚህ በበለጠ ለማስተማር በርቱ። ለዚህም ልዑል እግዚአብሔር ይርዳችሁ። አሜን።

*እሸቱ ወ/ማርያም*
*(አዲስ አበባ)*

## ሀዘኔ የበለጠ ከብዷል

ባለፈው እትም ከብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ጋር ያደረጋችሁትን ቃለ ምልልስ በሚገባ አነበብኩት። እኔ አደጋው በደረሰበት አካባቢ በመሆኔ ዕረፍታቸውን በትኩሱ ከሰሙትና አስከሬናቸውን ወደ አዲስ አበባ ከላኩት አንዱ ነኝ። ታዲያ የአባቶች ሁኔታ እስከዛሬ ቢያሳዝነኝም ቃለ መጠይቁን ሳነብ ኀዘኔ የበለጠ ከብዷል። ነገር ግን በቃለ መጠይቁ አንቀጽ 29 ላይ እኔን «በአሰላ ከተማ ወደሚገኘው ቅዱስ ገብርኤል አደረሱኝ» የሚለው ዓረፍተ ነገር በስህተት ስለሆነ በአሰላ ሳይሆን «አሣሣ ቅዱስ ገብርኤል» ተብሎ ይስተካከል። ሌላው ከመጀመሪያው ጀምሮ ያረፉትን ብፁዓን አባቶችና ሁለቱን ሊቃውንት (መልአከ ሰላም ዳኛቸውንና ሊቀ ጉባኤ አበራን) ከአሣሣ ክሊኒክ ዶዶላ ጤና ጣቢያ፣ ኩየራና ይርጋለም ሆስፒታል በማጓጓዝ ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከቱት የአሣሣ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲ ያን መሪጌታና ዲያቆናት መመስገን ይገባቸዋል።

*ሸዋንግዛው ማሙዬ*
*(አሣሣ)*

## ትውልድን ከጥፋት ታደጉ

ሐመሮች ይህንን ደብዳቤ ለመጻፍ የተነሣሁት በአሁኑ ወቅት የዓለምን ሕዝብ በማስጨነቅ ላይ ስለሚገኘውና መድኃኒት ያልተገኘለት ተብሎ እየተነገረለት ያለውን ቀሳፊ በሽታ በሚመለከት የሚጠበቅባቸውን ያደረጉትን ሁለት አባቶች ለማመስገን ነው። በሃምሳኛ ዓመት ቁጥር 183 ዜና ቤተክርስቲያን ጋዜጣ ላይ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና ዶ/ር ብፁዕ አቡነ ገሪማ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ የበሽታው መድኃኒት በእጃችን እንደሆነ ገልጠው «እንዴት?» ለሚለው ጥያቄ ሰፊና ጠቃሚ ትምህርት ሰጥተዋል። በእውነቱ እነዚህ አባቶች ምንም እንኳን ያንን ማድረግ የሚገባቸው ቢሆንም በልጅበነቴ ላመሰግናቸው እወዳለሁ። ሌሎች አባቶችና ሰባክያነ ወንጌልም እንደእነሱ ትውልድን የመታደግ ሥራ እንዲሠሩ አደራ እላለሁ። ከዚሁ ጋር የእናንተ ማኅበር አባላቱ ወጣቶች በብዛት እንደመሆናቸውና በእግዚአብሔር እርዳታ ብዙ ሥራ መሥራት የሚችሉ በመሆናቸው ከመንፈሳዊ ሥራዎቻችሁ ትልቁ መሆኑን ተገንዝባችሁ ትውልድ የማዳን ሥራችሁን እንድትጀምሩ አደራ እላለሁ።

*አቶ ጉተማ ለገሠ*
*(አዋሳ)*

<u>ከአዘጋጁ፡</u>–ወንድማችን ይህንን ሰው የሆነ ሁሉ ሊያስብበት ሊጨነቅ በትም የሚገባውን ጉዳይ አስመልክ ተው ረጅም አስተያየትዎን ስለሰጡን እናመሰግናለን። እንዳሉት ዕድሜ ሳይመርጥ የዓለምን ሕዝብ እየፈጀ ያለውን ይህንን ቀሳፊ በሽታ በሚመለከት የዓለም ሕዝቦች በሚችሉትና እግዚአብሔር በሚወደው መንገድ ሁሉ ሊተጉ ይገባል። እኛም ከሚቀጥለው እትም ጀምሮ ኤድስን በሚመለከት እኛም ሆን አንባብያን ትምህርት የሚሰጡበት ዐምድ እንከፍታለን። እርስዎም ሆኑ ሌሎች አንባብያን በበሽታው ዙሪያ የምትሉትና የምትጠይ ቁት ቢኖር ላኩልን። እናስተናግዳለን ።

## ተኩላዎች ወደ በጐች

በሰባተኛ ዓመት ቁጥር ሁለት እትም ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ጋር ያደረጋችሁትን ቃለምልልስ በጥሞና አንብቤዋለሁ። እናም በተለይ ልጆች (ሕፃናት) ከመጀመሪያው ጀምሮ ማለትም ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ አንደኛ ደረጃ የትምህርት ጊዜያቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁኔታዎችን እያመቻቹ ወደ ቅጽራቸው እንዲያሰባስቡ ቢደረግ የሚለው ሀሳብ እጅግ በጣም የተደሰትኩበትና ዘወትር በአእምሮዬ የሚጉላላ ጥያቄ ነበር። ታዲያ ይህ ጉዳይ ዛሬ ነገ ሳይባል ተግባራዊ ቢሆን እላለሁ። ቅዱስነታቸውም ኅብረተሰቡንና የቤተክርስቲያን አባቶችን በይበልጥ ቢቀሰቅሱት ተኩላዎች ወደ በጐች መካከል የሚገቡ አይመስለኝም።

*ተንሣይ ባረጋ*
*(መተሃራ)*

## መርዝ ውጠን ላለመሞት

ሐመሮች በ7ኛ ዓመት ቁጥር 2 እትማችሁ ላይ በማኅበሩ መልእክት የወጣውን ጽሑፍ ሳነበው እጅግ በጣሙን ደንቆኛል። እኒህ የጥፋት ልጆች በዚህ በጂንካ ከተማ በብዙ መልኩ ጉባኤያችንን ሲፈታተኑ ከር መዋል። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ቸርነት በእናታችን በድንግል ማርያም አማላጅነት እስከዛሬ ድረስ የተዋሕዶ ልጆች ተጠብቀን አለን። እንኖራለንም። ታዲያ ይህ አልበቃ ብሎአቸው ዛሬ ዛሬ ደብዳቤ በመጻፍ ለእኅቶቻችን ጌታን ተቀበይ የሚል መልእክት ከተወነባበደ ጥቅሳቸው ጋር እየጠቀሱ መስጠት ጀምረዋል። ስለዚህ ይህ እኩይ ተግባራቸው በዚህ አካባቢ ብቻ የተወሰነ ስለማይሆን የተዋሕዶ ልጆች ከትናንቱ ይልቅ ዛሬ ይበልጥ ልንጠነቀቅ የሚገባን ጊዜ መሆኑን ዐውቀን በማር የተለወሰ መርዝ ውጠን ላለመሞት በሃይማኖታችን እንፅና። እግዚአብሔር አምላክ ከፈተና ይጠብቀን።

*ተኮላ ከተማ*
*(ጂንካ)*

# ወደሰማይ ተመልከት

ዘፍጥ.15÷5

*ከቀሲስ ስንታየሁ አባተ*

ልዑል እግዚአብሔር በሕግ በአምልኮ በፍቅር ሁሉን ትተው ወደ እርሱ የቀረቡ ልጆቹ ሃዘን፣መከራ ስደት ሲያገኛቸው ዝም ብሎ አይመለከታቸውም:: የወደደውን ሊያደርግላቸው ድምፁን ያሰማቸዋል:: የረድኤት እጁንም ይዘረጋላቸዋል::

አብርሃም የሥነ ፍጥረትን ሂደት ተመልክቶ ፈጣሪውን ለማወቅ በንጹሕ ልቡና በመሻቱ ለወደዱት ቅርብ የሆነ እግዚአብሔር ድምፁን አሰማው:: እርሱ ወደሚያሳየው ምድር እንዲወጣም አዘዘው:: አያይዞም ዘሩን እንደሚያበዛለትና እንደሚባርክለት ቃል ኪዳን ገባለት::

አብርሃም እግዚአብሔርን አምኖ ተስፋም አድርጎ በታዘዘው መሠረት ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ:: ፈጣሪው ባመለከተው ምድር ይኖርም ጀመር:: እርሱ ለእግዚአብሔር ፈጥኖ ቢታዘዝም «ዘርህን አበዛልሃለሁ፤» ያለው እግዚአብሔር የተስፋው መፈጸሚያ የሚሆን ልጅ እንደሰው አቆጣጠር ቶሎ አልሰጠውም:: አብርሃም ዕድሜው ገፋ፣ ጉልበቱ ዛለ:: ልጅ ባለመውለዱም አዘነ:: በዚህ የተነሣ ኀዘኑን ዕለት ዕለት በእግዚአብሔር ፊት ያስታውቅ ጀመር::

እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ቆርጦ አያሳፍርም:: በውድቅት ሌሊት በኀዘን በትካዜ የተያዘውን አብርሃምን ቀስቅሶ «አብራም ሆይ አትፍራ፤ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ:: ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው:: ... ወደሰማይ ተመልከት ከዋክብትንም ልትቆጥራቸው ትችል እንደሆነ ቁጠር:: ዘርህም እንደዚህ ይሆናል::» አለው:: /ዘፍ.15÷5/ አብርሃም ዓይኑን አቅንቶ ተስፋውን በሰማይ አየ::

ፍርሃት ራቀለት:: በሰማይ ሆድ ላይ አሸብርቀው እንደሚታዩት ከዋክብት ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ለሰማያዊ ርስት ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ ሥራ የሚሠሩ፣ ፈቃደ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ብሩህ አእምሮን ገንዘብ የሚያደርጉ ልጆች እንደሚሰጠው አመነ:: ይህም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት::

አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር እንደ አብርሃም በእምነት የሚታዘዙለትን ፣በሙሉ ልባቸው ተስፋ የሚያደርጉትን ሲቸገሩ፣ ሲያዝኑ በረድኤት ይቀርባቸዋል:: መልካሙን ፈቃዳቸውን ይፈጽምላቸዋል:: ወደ ሰማይ ተመልከቱ እያለ ተስፋቸውን በማን ላይ መጣል እንዳለባቸው ያመለክታቸዋል:: ዛሬም ቢሆን በሃይማኖት ጸንተን፣ ፈቃደ እግዚአብሔርን በመፈጸም የጸናን አንዳች ነገር በኑሮአችን ውስጥ ሲያገኘን ዓይናችንን እንደ አብርሃም ወደ ሰማይ ልናቀና ይገባል:: ለመሆኑ ዓይንን ወደ ሰማይ ማንሣት /ወደ ሰማይ መመልከት/ ወደማን መመልከት ነው?

## 1. ወደ እግዚአብሔር መመልከት ነው

ሰማይ የእግዚአብሔር የክብሩ ዙፋን መገለጫ ነው:: የኀዘን ደመና ያንዣበበበት ከእግረ አጋንንት ወድቆ ኃጢአት የሰለጠነበት አይዞህ ባይ ረዳት የሌለው መጻተኛ ከዚህ ሁሉ ችግር ሊያወጣው ወደሚቻለው ወደ እግዚአብሔር ያንጋጥጣል:: ቅዱስ ዳዊት «የሰው ሁሉ ሰውነት አንተን ተስፋ ያደርጋል» እንዳለው ወደተስፋው ይመለከታል::

ወደ ሰማይ ስንመለከት ለአባቶቻችን ተስፋን የሰጠ፣የተናገረውንም የፈጸመ እግዚአብሔርን በዓይነ – ልቡናችን እናያለን:: በሰማይ የምትኖር ሆይ ዓይኖቼን ወደ አንተ አነሣሁ» በማለት እንለምነዋለን:: /መዝ.123÷1/ በሰማይ የሚኖር አምላካችንን ስናስበው ቃሉ፣ ትእዛዙ፣ቸርነቱ፣ ቅድስናው፣ ፍርዱ፣ ጥበቃው፣ ፍቅሩ ይታሰበናል::

አብርሃም ከሀገሩ የተለየው እግዚአብሔርን ብሎ ነው:: በችግሩ ጊዜም ተስፋ ሳይቆርጥ የለመነው እግዚአብሔርን ነው:: በመሆኑም የወደደውን አገኘ:: ዛሬም እምነታቸውንና ተስፋቸውን በእግዚአብሔር ላይ የጣሉ ሰዎች የወደዱትን ነገር ከእርሱ ያገኛሉ::

በቅዳሴያችንም ዲያቆኑ «በሰማይ የሀሉ ልብክሙ፤ ልቡናችሁ ሰማያዊ ነገር በማሰብ በአንክሮ፣ በተዘክሮ ጸንቶ ይኑር፤» በማለት ያውጃል:: ይህም ከሰማያዊው አምላክ ክብር የሚያሰጠንን ሥራ ለመሥራት ራሳችንን እንድናዘጋጅ ነው:: ነህምያ የፈረሰውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመሥራት ሲነሣ ብዙዎች ተዘባብተውበት ነበር:: እርሱ ግን ዓይነ ልቡናውን ወደሰማይ ያነሣ ተስፋውን በእግዚአብሔር ያደረገ በመሆኑ «የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል:: እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን» በማለት ተናገረ:: እንደተናገረው ያመነውና ተስፋ ያደረገው እግዚአብሔር ረዳው:: /ነህ. 2÷20/ ሠለስቱ ደቂቅ ለጣዖት እንዲሰግዱ ሲገደዱ ዓይናቸው የናቡከደነፆርን ግርማ፣የእሳቱን ግለት አልተመለከተም:: በሰማይ ወዳለው ወደ ልዑል እግዚአብሔር ተመለከቱ:: ተስፋም አደረጉት:: በአስጨናቂያቸውም ፊት አንደበታቸውን መልተው «...የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል:: ከእጅህም ያድነናል» አሉ:: እርሱም አዳናቸው:: /ዳን. 3÷17/

እንደ አብርሃም በእግዚአብሔር አምነው የሚታዘዙለት፣ ወደ ሰማይ የሚመለከቱ /በተስፋ የሚጠባበቁት/ ታምነው ይሠማራሉ:: እንደ ቅዱስ ገብርኤልም አንደበታቸውንና ልባቸውን አንድ አድርገው «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም» በማለት እምነታቸውን ይገልጣሉ::

## 2.ወደ እመቤታችን መመልከት ነው

ሰማይ ዙፋኑ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ፣ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ስለከተመባት ሰማይ ትባላለች:: ሊቁ.ቅዱስ ኤፍሬም «አምላክን ያለርኩሰት የወለድሽ ሆይ የምድር ሁለተኛ ሰማይን ሆንሽ እውነተኛ ፀሐይ ካንቺ ወጥቷልና» ሲል ያመሰገናት አማናዊት ሰማይ መሆንዋን በመረዳቱ ነው:: በሰማይ መላእክት፣ ቅዱሳን እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ በእመቤታችን ማኅጸን ሣለ፣ በዕቅፍዋ ታቅፋውም ሣለ የሰማይ መላእክት የምድር ሠራዊት አመሰግነውታል::

ከሰማይ ፀሐይ ትወጣለች:: ጨለማን ታርቃች:: በብርድ ለታሠረ ሁሉ ሙቀትዋን ትለግሣለች:: «ዳግማዊ ሰማይ» የተባለችው እመቤታችን ያለዘርዐ ብእሲ በፍጹም ድንግልና ያስገኘችው /የወለደችው/ ፀሐየ–ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢ

አትን ጨለማ፣ አራቀልን:: በኃጢአት ሠንሰለት ታሥረው መንጸፈ ደይን የወረዱትን በሞቱና በትንሣኤው ከእሥራታቸው ፈታቸው:: በዚህም እመቤታችን ለሰው ልጆች ሁሉ ምክንያተ ድኂን ሆነችን::

በአሪቱ የነበሩ ሁሉ ከነበረባቸው መከራ ለመዳን ወደዚህች እናት ያንጋጥጡ ነበር:: ድኅነተ ዓለም በእርሷ በኩል እንደሚፈጸም ተረድተው «ሙሽራዬ ሆይ ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነይ፣ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነይ» እያሉ ይጮሁ ነበር:: /መኃል.4÷8/ በርሷም መወለድ ዓለሙ ከጥፋት መዳኑን «የሠራዊት ጌታ ዘር /እመቤታችንን/ ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደገሞራም በመሰልን» ብለው መስክረዋል:: /ኢሳ.1÷9/

እኛም ዛሬ በነፍስ በሥጋ መከራ ሲመጣብን ዓይናችንን ወደ እመቤታችን እናነሣለን:: የአዳም ተስፋ የተፈጸመው በእርሷ እንደሆነ ሁሉ እኛም ኃጥአን ርኅርኅተ ኅሊና የዋህ ልቡና መሆንዋን ዐውቀን ምልዕተ ክብር ምልዕተ ጸጋ፣ እግዚአብሔር የማይለያት መሆኗን አምነን «ሰአሊ ለነ ቅድስት» እያልን ወደ እርስዋ እናንጋጥጣለን:: ሉቃ1÷28/

## 3.ወደ ቅዱሳን መላእክት መመልከት ነው

መላእክት ሰማያውያን ናቸው:: ስለ ዚህም ወደ ሰማይ በተመለከትን ወቅት በእግዚአብሔር መንበር ዙሪያ በፍርሃት በመንቀጥቀጥ ቆመው የሚያመሰግኑትን ቅዱሳን መላእክት በዓይነ ልቡናችን እናያለን:: እነዚህ መላእክት ሳያርፉ ያመሰግናሉ:; የሰውን ልጆችም ይጠብቃሉ:: መልካም ሥራን ለመሥራት ስንነሣም ይደግፉናል፣ይራዱናል:: ቅዱስ ጳውሎስ «አኮኑ ኲሎሙ መላእክት መንፈስ እሙንቱ ወይትፌነው ለመላእክት በእንተ ሀለዎሙ ወረሱ ሕይወተ ዘላለም፤ የዘላለም ድኅነትን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ሰዎች የሚወጡ የሚወርዱ መላእክት አይደሉምን?» ያለውም በድኅነታችን ውስጥ የመላእክት አገልግሎት ሰፊ መሆኑን ያመለክታል:: /ዕብ.1÷14፣ መዝ.33÷7/

በዚህ መሠረት ከአጋንንት ዘንድ ፈተና ሲበዛብን፣የሥጋ ፈቃድ ሲያይልብን ስተን ከድኅነት ጎዳና እንዳንወጣ ይረዱን ዘንድ ወደ ሰማያውያን መላእክት እናንጋጥጣለን:: እንደሚረዱን ተስፋ አድርገን ስንለምናቸው «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለአንተ ያዝዛቸዋልና፣ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል» በተባለው መሠረት ይረዱናል፣ይጠብቁናል:: /መዝ.90÷11–12/

እነዚህ ቅዱሳን የሰማይ መላእክት ዘወትር ስለኛ የሚቆሙ ፣ በእግዚአብሔር ዘንድም ክብር ያላቸው በመሆኑ ሊከበሩ ይገባቸዋል:: በተስፋ ወደ ነርሱ ስንመለከት ይህን ክብራቸውንም ጭምር መገንዘብ ተገቢ ነው:: ልዑል እግዚአብሔር ከወደቅንበት የኃጢአት አዘቅት አንዲያወጡን መላእክቱን ሲልክልን እኛ ደግሞ በትኅትና፣ በፍቅር በአክብሮት ልንቀበላቸው ይገባል:: «በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ሥፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድዳለሁ:: በፊቱ ተጠንቀቁ:: ቃሉንም አድምጡ:: ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት:: አንተ ግን ቃሉን ብትሰማ ያልሁህንም ሁሉ ብታደርግ ጠላቶችህን እጣላችዋለሁ:: የሚያስጨንቁህንም አስጨንቃቸዋለሁ:: መልአኬ በፊትህ ይሄዳልና» ተብሎ አንደተጻፈው ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል:: /ዘጸ. 23÷20–23/

## 4. ወደ ቅዱሳን አበው መመልከት ነው

ቅዱሳን አበው እኛ የለበስነውን ሥጋ የለበሱ፣የሚሰማን ስሜት የሚሰማቸው ሲሆኑ የዚህችን ዓለም ጣዕም ንቀው ተስፋ ስለሚያደርጓት መንግሥት ጽኑ የሆኑ መከራዎችን ተቀብለው ለክብር የበቁ ናቸው:: ከዚህ ዓለም በሥጋ ቢለዩም በመንፈስ ከኛ ጋር ናቸው:: ትናንት በኃጢአት ለታሰረው ወገናቸው ያስቡ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም ፍጹም ዕውቀት በሚታደልበት ዓለመ ነፍስ ሆነው ለልጆቻቸው ያስባሉ:: /ሉቃ13÷12–13፣ ራዕይ.6÷9–11/

ልዑል እግዚአብሔርም ስለርሱ ሲሉ መራራ መከራን ተቀብለው በክብር ስላረፉ ወዳጆቹ /ስለ ቅዱሳን/ ሲል እንደሚምረን ስለምናምን ወደ አበው ቅዱሳን እንመለከታለን:: ምልጃቸውን፣ በረከታቸውን ረድኤታቸውን ተስፋ አድርገን አማልዱን እንላቸዋለን:: ኢየሩሳሌምን ስለወዳጁ ስለ ቅዱስ ዳዊት ሲል ከሰናክሬም ጦር የጋረዳት /የጠበቃት/ እግዚአብሔር በደሙ የዋጀን እኛማ የበለጠ የቸርነት ሥራውን እንደሚሠራልን ስለምናምን ወደ ቅዱሳን እንመለከታለን:: /ኢሳ.37÷35/

ከዚህም በተጨማሪ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፤ የኑሮአቸውን ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነት ምሰሉአቸው፤» ባለው መሠረት ዓይነ ልቡናችንን ወደ ቅዱሳን እንመልሳለን:: በመሆኑም ለገነት የበቁት ጽኑዕ እምነትን ይዘው፣መራራ ተጋድሎን ተጋድለው እንደሆነ እንረዳለን:: ለእግዚአብሔር የነበራቸውን ፍቅር፣ ለሃይማኖታቸው ያሳዩትን ጽናት ከሕይወታችን ጋር እናስተያያለን:: ድክመታችንን ተረድተንም እንዲያግዙን እንለምናቸዋለን:: /ዕብ.13÷7/

ሊቀ ነቢያት ሙሴም «አባትህን ጠይቅ ያስታውቅህማል፣ ሽማግሌዎችህን ጠይቅ ይነግሩህማል፤» ያለው በሃይማኖት መንገድ ከኛ የቀደሙ አበው በመከራ፣በኀዘን፣በደስታ ወቅት የነበራቸው ጽናት ለእኛ አርአያ እንዲሆነን የሚጋብዝ ነው:: /ዘዳ.32÷7 የጸናውን አስቡ እንደተባለው ዓይናችንን ወደሰማይ አንሥተን የጸኑትን ስናስባቸው ብርታት ይሰማናል:: /ዕብ.12÷3/

እንግዲህ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ከዓለም የሆነ መከራ ሲያገኘን እንዲረዳን፣ኃይል ምርኩዝ እንዲሆነን ዓይናችንን /ተስፋችንን/ ወደማን ማንሣት እንዳለብን ዕንወቅ:: አብርሃም ልጅ ባጣበት ወቅት ሌላ መፍትሔ አልፈለገም:: ዓይኑን ከእግዚአብሔር መልሶ በዙሪያው ወዳሉ ጣዖት አምላኪዎች ፣ባለዛሮችና ጠንቋዮች አልተመለከተም:: በጽኑ እምነት ሆኖ ልመናውን በእግዚአብሔር ፊት አስታወቀ እንጂ:: እኛም ዛሬ ልዑል እግዚአብሔር የክብሩ ወራሾች እንድንሆን ጠርቶናልና ሀገራችን በሰማይ መሆኗን ተረድተን ወደሰማይ እንመልከት:: ሐዋርያው «ወእመሰ ተንሣእክሙ ምስለ ክርስቶስ ዘላዕሉ ኅሡ ኀበ ሀሎ ክርስቶስ በየማነ እግዚአብሔር ይነብር ዘላዕሉ ሐልዩ ወአኮ ዘበምድር፤ ከክርስቶስ ጋር ለመኖር ትንሣኤ ልቡና ከተነሣችሁ ምድራዊውን ያይ ደለ በአብ ዕሪና የሚኖር ክርስቶስ ካለበት ዘንድ ሰማያዊውን ነገር እሹ» ባለው መሠረት ተስፋችን ሰማያዊ ይሁን:: ቆላ.3÷1–2/

ሰማያዊውን ርስት አስበን፣ሰማያዊ ሥራ ሠርተን መንግሥቱን ለመውረስ ስሙን ለመቀደስ እንዲያበቃን የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን::

# ነገረ ድኅነት

ባስልዮስ ዘቂሣርያ

## እግዚአብሔር ሰው ሆነ ስንል እንዴት ነው?

ባለፉት እትሞቻችን እንደ
ተመለከትነው ነገረ ድኅነት ማለት
የመዳን ነገር ማለት ነው:: በዚህ ምሥ
ጢር ደግሞ ከዚህ ቀጥለን የምናየው
የክርስቶስ ሰው የመሆን ምሥጢር
(ምሥጢረ ሥጋዌ) ትልቅ ቦታ ይሰጠ
ዋል:: አንድ ሰው «አምላክ ሰው ሆነ»
«እንዴት ሰው ሆነ?» የሚለውንም
ሐሳብ መረ ዳት ይኖርበታልና:: እግዚ
አብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ
በሥጋ ማርያም ስለመገለጡ ስንናገር
በዙሪ ያው ማወቅ የሚገባን ብዙ ነገር
አለ::

ቅድመ ዓለም ያለእናት ከባ
ሕርይ አባቱ ከአብ ድኅረ ዓለም ያለ
አባት ከድንግል ማርያም በሥጋ የተወ
ለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ነስቶ
ሰው የመሆኑ ነገር ቅዱስ ጳውሎስ እን
ደተናገረው ነው:: ስለዚህ ይህን በሚ
ገባ መረዳት አለብን:: ይህንን ስል
በራሳችን ተፈላስፈን እንመርምር
ማለት አይደለም:: ነገር ግን ቅዱሳት
መጻሕፍት በገለጡልን ዕውቀት መሠ
ረት እንዴት ሰው እንደሆነ እንረዳ
ማለታችን እንጂ:: ጌታችን ጴጥሮስን
«አንተ ዐለት ነህ በዚህ ዐለት ላይ
ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ» ማቴ.
16÷18 ያለው፣ የሃይማኖት መሠረት
የሆነ እምነት እንዳለው የተናገረለት፣
«አንተ መሲሁ ክርስቶስ የሕያው የእግ
ዚአብሔር ልጅ ነህ» ስላለ ነበር::
ማቴ.16÷16:: በፊቱ የቆመውን ወልደ
አምላክ የአብ የባሕርይ ልጅ ብሎ
በመጥራቱ ብፁዕ ተባለ::

ዛሬም ብዙዎች እንደሚሉት
በተሳሳተ መልኩ ኢየሱስ ክርስቶስን
የማይገባ ስም ሰጥተን ከመጥራት ተቆ
ጥበን /ከስህተት ድነን/፣ መለኮት
ከሥጋ ፍፁም መዋሐዱን አምነን፣ ኢየ
ሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ ነው፣
የአብ የባሕርይ ልጁ ነው ብለን ከአመ
ንን ሊያድነን ይችላል:: ስለዚህ እግዚ
አብሔር ወልድ ሰው ሆነ ስንል በምን
መልኩ? እንዴት? የሚለውንም ማወቅ
አለብን:: ከዚህ ቀጥለን ይህን ሐሳብ
መረዳት እንዲያስችለን አምላክ ሰው
የሆነው እንዴት እንደሆነ በቅዱሳት
መጻሕፍት በተጻፈውና አባቶች በነ
ገሩን መሠረት እንመለከታለን::

<u>በመለወጥ /ውላጤ/ ነውን</u>? አይደለም፤

ለምን? ቢሉ መለወጥ ማለት ሥጋ
ወደ መለኮትነት ወይም መለኮት ወደ
ሥጋነት ተለውጧል፣ አንዱ በአንዱ
ጠፍቷል ማለት ነው:: <u>ምሳሌ</u> የሙሴ
በትር ወደ እባብነት፣ የሎጥ ሚስት
ወደ ጨው ዓምድነት እንደተለወጡ::
አንድ ነገር ተለወጠ ስንል የቀደመ
ባሕርይውን ለቆ ሌላ ይሆናል የሚል
ትርጉም ይሰጠናል:: የአምላክ ሰው
የመሆን ምሥጢር ግን በመለወጥ አይ
ደለም:: ምክንያቱም መለኮት ወደ
ሥጋነት ተለወጠ ካልን መለኮት የቀ
ድሞ ማንነቱን ለቆ ሰው ብቻ ሆኗልና
ዓለም አልዳነም ማለት ይሆንብናል::
ይህ ደግሞ መለኮት ከሥጋ ጋር ስላል
ተዋሐደ ሥጋ ብቻውን ከሆነ መከራ
መቀበሉ መሰቀሉ ሁሉ ለከንቱ ነው
ያስብላል:: በሥጋ ብቻ (በፍጡር ደም)
ዓለም አይድንምና::

በሌላ በኩል ሥጋ ተለውጦ
መለኮትን ሆኗል በመለኮት ተውጧል
ልንልም አንችልም:: አምላክ ሰው ሆነ
ካልን ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ
መሆኑንም ከመረዳት ጋር መሆን አለ
በት:: ምክንያቱም ሥጋ ባሕር ይውን
ለቅቆ ወደ መለኮትነት ተለው ጧል
ካልን አሁንም ዓለም አልዳነም ወደ
ሚል ሀሳብ ስለሚወስድ ነው:: ክርስ
ቶስ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ ነው
ብለን ካላመንን ሥጋ ተለውጧል ካልን
መከራ የተቀበለው መለኮት ብቻውን
ነው ያስብለናል:: ይህ ደግሞ ስህተት
ነው፤ መለኮት ሊዳሰስ፣ ሊሰ ቀል፣
ሊቀበር አይችልምና:: የግድ መከራን
ለመቀበል የሥጋን ባሕርይ ባሕርይው
ማድረግ ነበረበት:: ስለዚህ በአጠቃ ይ
ስናየው ሥጋም ወደ መለ ኮትነት
መለኮትም ወደ ሥጋነት አል ተለወ
ጡም በተዐቅቦ (በመጠባበቅ) አንድ
ሆኑ እንጂ:: እግዚአብሔር በባሕር
ይው መለወጥ ስለሌለበት (ሚል.
3÷6) በሥጋ ባሕርይ ተለወጠ ማለት
ስሕተት ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ትና
ንትም ዛሬም እስከ ዘለዓለም ያው
ነው (ዕብ.13÷6)::

<u>በኅድረት ነውን?</u> አይደለም::

ይህ ሃሣብ የመጣው በምንታዌ
(በሁለትነት) ከሚያምኑና በ2ኛው
መቶ ክፍለ ዘመን ከነበሩ መናፍቃን
ነው:: እነርሱም ሁለት አምላክ አለ::
አንዱ ክፉ ሌላው ደግ፤ ክፉው ይህን
ዓለም (ሥጋን) ፈጠረ፤ ደጉ የማይታ
የውን ዓለም (ነፍስን) ፈጠረ:: ስለዚህ
ነፍስ በደጉ፤ ሥጋ በክፉ የተፈጠሩ
በመሆናቸው ሁለቱ አይዋደዱም::
ነፍስ በሥጋ ታስራ ስትሰቃይ ትኖራ
ለች፤ አምላክ እርሷን ነጻ ሊያደርግ
መጣ:: በሥጋ ላይ አድሮ ተመላለሰ፤
ግን ሥጋ አልተዋሐደውም፤ ምክንያ
ቱም ሥጋ የክፉ አምላክ የእጁ ሥራ
የረከሰ ፍጥረት ነውና ይላሉ::

ይህ አስቀድሞ በነበሩ በሁለት
አማልክት በሚያምኑ መናፍቃ የተ
ጀመረ የኅድረት ትምህርት ሥር ለቆ
በስተመጨረሻ «በአንድ አምላክ እናም
ናለን» ወደሚሉ መናፍቃንም ደረሰ::
ስለዚህም ከቤተክርስቲያን የተነሡ እነ
ንስጥሮስም አምላክ ከድንግል ማርያም
በተወለደው በኢየሱስ ላይ አደረበት
እና የፀጋ አምላክ አደረገው እንጂ
ሥጋን አልተዋሐደም አሉ:: /ንስጥሮስ
በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን የተወገዘ መና
ፍቅ ነው::/ ይህ መናፍቅ ዳዊት በማኅ
ደሩ እንደሚያድር በማርያም ልጅ
ኢየሱስ ላይ አምላክ አደረበት:: ድን
ግል ማርያም የወለደችው ሰውን ነው
/ወላዲተ ሰብእ ይላታል/:: ኋላ እርሷ
በወለደችው ላይ ፈጣሪ አደረ ብሎ
በድፍረት ያስተምር ነበር:: ይህንን የክ
ህደት ትምህርት ይዘው ኢየሱስ ክር
ስቶስ ሁለት ባሕርይ ነው:: ሥጋን
አልተዋሐደም የሚሉ መናፍቃ
ዛሬም አሉ:: ይህ ዓይነት አስተሳሰብ
ግን ፍፁም ስህተት ነው:: ምክን
ያቱም::

ሀ. መናፍቃ እንደሚሉት እመ
ቤታችን ሰውን ብቻ ወለደች ኋላ
አምላክ መጥቶ አደረባት ካልን ከፅን
ሰቱ ጀምሮ በልደቱ ጊዜ የተደረገውን
ነገር የተነገረለትን ቃል መሻር ስለሚ
ሆንብን ነው:: ኢሳይያስ «ድንግል
ትፀንሣለች፤ ወንድ ልጅም ትወል
ዳለች፤ ስሙ ንም አማኑኤል ብላ ትጠ
ራዋ ለች::» ኢሣ.7÷14 /አማኑኤል
ትርጓሜውም «እግዚአብሔር ከእኛ
ጋር ነው» ብሎ ተናግሯል::
/ማቴ.1÷23/ የተወለደው ሕጻን አማ
ኑኤል የተባለው ሲወለድም አምላክ
በመሆኑ ሥጋን ነስቶ ፍፁም ሰው
መሆኑን ለመ ግለጥ ነበር:: ከዚህ ሌላ
አሁንም በትንቢት «ሕጻን ተወልዶልና
ልና÷ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለ
ቅነትም በጫን ቃው ላይ ይሆ ናል
ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ÷
የዘለዓለም አባት÷ የሰላም አለቃ
ተብሎ ይጠራል» የሚል ቃል እናገኛ
ለን:: ኢሳ.9÷6 በቤተልሔም ዋሻ
ድንግል ማርያም የወለደችው ሰብአ
ሰገል ወርቅ ዕጣን ከርቤ መባ አድ
ርገው ያቀረ ቡለት ሕጻን ኢየሱስ ክር
ስቶስ አምላክ ስለሆነ ስሙም ኃያል
አምላክ ተብሎ ይጠራል ተባለ ለት::
ይህን ሕጻን ኤልሳቤጥ በማ ሕፀን ሳለ
ገና ጌታዬ ብላ ጠርታዋለች:: ሉ ቃ
.1÷43:: ስለዚህ መናፍቃ

➡

እንደሚሉት ድንግል ማርያም ወላዲተ
ሰብእ /የሰው እናት/ አይደለችም።
የአምላክ እናት እንጂ። ኢየሱስ ክርስ
ቶስም አስቀድሞ ሰው የነበረ በኋላ
በፀጋ የከበረ አይደለም። ከድንግል
ማርያም ሥጋን ነስቶ ሰው የሆነ
አምላክ እንጂ።
ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕ
ርይ ነው፤ መለኮትና ሥጋ አልተዋሐ
ዱም፤ ከተባለ ሰው ገና አልዳነም
ማለት ይሆናል። በተዋሕዶ መለኮት
ና ሥጋ አንድ ካልሆኑ ኢሳይያስ «...
በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕማማ
ችንም ተሸክ ሟል... ስለመተላለፋችን
ቆሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ... ተጨነቀ
ተሰ ቃ አፉን አልከፈተም» (ኢሳ.53)
ብሎ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ባልተና
ገረ ነበር። እርሱስ በተዋሕዶ መለኮ
ትና ሥጋ አንድ መሆናቸውን በመን
ፈስ ተገልጾለት ተናገረ። ለምን ቢሉ
መታ መምና መቸገር የመለኮት ባሕ
ርይ አይደለምና፤ በተዋሐደው ሥጋ
ታመመ፣ ተቸገረ፣ ቆሰለ ለማለት።
ሥጋ ብቻውን ነው ካልን ግን ሰው
የራሱን መከራ ራሱ ተቀብሏልና ገና
አልዳነም ወደሚል ክህደት ይወስዳል።
ሰውም በሰው አይድንምና አዳም
አልዳነም ማለትን ያስከትላል። በተዋ
ሕዶ ምሥጢር ግን መለኮት የሥጋን
ገንዘብ የራሱ በማድረግ ታመመ፣
ሥጋም የመለኮትን ገንዘብ የራሱ በማ
ድረጉ መከራን ችሎ ታገሰና ተቀበለ፤
እንላለን። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ
ሁለት ባሕርይ አይደለም። በመሆኑም
ኅድረት የሚለው ቃል ክህደት ነው።
ሐ. እግዚአብሔር አብ ስለ ባሕ
ርይ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የምወ
ልደው የምወደው ልጄ እርሱ ነው
በማለት መስክሯል። መለኮትና ሥጋ
በተዋሕዶ አንድ ባይ ሆኑ ኖሮ
በንቅዱስ ጴጥሮስ ፊት የቆመውን ኢየ
ሱስ ክርስቶስን ልጄ ብሎ ባልጠራው
በዚህም ፈንታ የልጄ ማደሪያ ባለው
ነበር። ነገር ግን ሥጋ ከመለኮት ጋር
በመዋሐዱ ማደሪያ ሳይሆን ልጄ
ተብሎ ሥጋ የመለኮትን ገንዘብ
ገንዘቡ አድርጎ የአብ የባሕርይ ልጁ
ተባለ። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው
የሆነው በኅድረት ሳይሆን በተዋሕዶ
ነው።

<u>በቱሳሔ ነውን?</u> አይደለም።

ቱሳሔ ቅልቅል ማለት ነው።
ይህም እንደ ማር እና እንደ ውኃ
ነው፤ ውኃና ማር ሲቀላቀሉ ስም ማእ
ከላዊ ይገኝባቸዋል። መልክ ማእከላዊ
እንደ ማር ሳይነጣ እንደ ውኃ ሳይጠ
ቁር መካከለኛ መልክ ይይዛል፤ ጣዕም
ማዕከላዊ እንደ ማር ሳይከብድ እንደ
ውኃም ሳይቀል መካከለኛ ጣዕም ይኖ
ረዋል። ወተትና ቡናም ሲቀላቀሉ እን
ዲሁ ነው፤ ቡናው እንደ ወተት አይ
ነጣም - ወተቱም እንደቡና አይጠ
ቁርም፤ መካከለኛ ቀለም ይኖራቸዋል።
በምሥጢረ ሥጋዌ ግን
ሥጋና መለኮት አንድ የሆኑ ያለመ
ቀላቀል ነው። ሥጋ ወደ መለኮትነት
መለኮት ወደ ሥጋ ባሕርይ መጥቶ
መካከለኛ የሆነ ነገር አልመጣም።
ሥጋም ሥጋዊ ባሕርይውን ሳይለቅ
መለኮትም መለኮታዊ ባሕርይውን ሳይ
ተው በመጠባበቅ ተዋሕደዋል። ያለመ
ቀላቀል ሌላ አዲስ ነገር ሳይፈጥሩ
አንድ ሆነዋል። ሥጋም የመለኮትን
ባሕርይ ገንዘቡ አድርጎ፣ መለኮትም
የሥጋን ባሕርይ ገንዘቡ አድርጎ ተዋ
ሕደዋል።
<u>ምሳሌ:</u>- ሙሴ ባያት ዕፀ ሐመልማሉ
ከነበልባሉ /ቅጠሉ ከእሳቱ/ ጋር ተስ
ማምተው ነበር። አንዱ ሌላውን አላጠ
ፋውም። ቅጠሉ እሳቱን ሳያጠፋ እሳቱ
ቅጠሉን ሳያ ቃጥል ያለመጠፋፋት
አንድ ላይ ታይተዋል። እንደዚሁም
መለኮት የሥጋን ባሕርይ ሳያጠፋ
ሁለቱ ያለመጠፋፋት አንድ ሆኑ።
ከዚህ ውጭ ተቀላቀሉ ካልን ግን
ከባሕርያቸው ለቀዋል፣ ክርስቶስ
ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ አይደለም፣
ሌላ አዲስ ባሕርይ አለው ስለሚያ
ስብለን በሰውነቱ መብላት መጠ
ጣቱን... የሰውን ሥራ መሥራቱን
ምትሐት ነው እንድንል በአምላክነቱ
ሙት ማስነሣቱን፣ ተአምር መሥራ
ቱን፣ እንዳናምን እንድንጠራጠር ያደ
ርገናል። በመቀላቀል ወደ ሌላ ባሕ
ርይ ተቀይሯል ካልን ፍፁም አምላክ
ነው ልንል አንችልምና ነው።

<u>በትድምርት ነውን? አይደለም።</u>

ትድምርት መደረብ መደ
መር ማለት ነው። ይህም እንደ ልብስ
እንደ እንጀራ ማለት ነው። ልብስ
ቢደርቡት ይደረባል፣ ቢነጥሉት ይነጠ
ላል፣ እንጀራም ቢደርቡት ይደረባል፣
ቢነጥሉት ይነጠላል። መለኮት ከሥጋ
ጋር አንድ የሆነው ግን እንዲህ በመ
ደረብ አይደለም፤ በተዋሕዶ እንጂ።
ምክንያቱም በትድምርት ከሆነ ሲፈ
ልጉ መነጠል አለ። ቀድሞውንም
አንዱ በአንዱ ላይ ይደረባል እንጂ
አይዋሐዱም። መለኮትና ሥጋ ግን
በመጀመሪያም በተዋሕዶ አንድ ሆነ
ዋል ኋላም ያለመነጣጠል ኖረዋል።
መለኮትን ከሥጋ ከተዋሐደ በኋላ
መነጠል አይቻልም።

<u>በቡዐዴ ነውን?</u> አይደለም።

ቡዐዴ መለየት መለያየት
ማለት ነው። ሁለት ነገሮች አንድ ላይ
ከሆኑ በኋላ መለየት መነጠል ሲቻል
ቡዐዴ ይባላል። <u>ለምሳሌ:</u>- በቆሎና
ስንዴን (በጥሬአቸው) እነዚህ ሁለት
የእህል ዘሮችን ከቀላቀልናቸው በኋላ
ስንፈልግ መለየት እንችላለን። አብረ
ውም ሳሉ በቆሎውን በቆሎ ስንዴውን
ስንዴ እንላለን። የክርስቶስ ሰው
የመሆን ምሥጢር ግን ከዚህ የተለየ
ነው። ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋና መለኮ
ትን ለያይቶ ለየብቻ ይህ መለኮት
ነው ይህ ሥጋ ነው አይባልም። እንደ
ብረትና እሳት ፍፁም ተዋሕዶ ስለሆነ
መነጣጠል አይቻልም። ስለዚህ ክር
ስቶስ ሰው የሆነው እንበለ ቡዐዴ
ነው።

<u>በተዋሕዶ ነውን?</u> አዎን።

በተዋሕዶ ነው። ተዋሕዶ
ከሚጠት፣ ውላጤ፣ ቱሳሔ፣ ትድም
ርትና ቡፀዴ የተለየና አምላክ ሰው
የሆነበትን ምሥጢር የሚገልጥ ቃል
ነው።
ሁለት አካላት አንዱ አንዱን
ሳያጠፋ ሳይለውጠው፣ ያለመቀላቀል
ያለመደራረብ /በተዐቅቦ/ በመጠባበቅ
አንድ ሲሆኑ ተዋሐዱ ይባላል።
<u>ለምሳሌ:</u>- የብረትና የእሳት ውሕደት
/አንድነት/። ብረትና እሳት ሲዋሐዱ
ብረት የእሳትን ገነዘብ ገንዘቡ ያደር
ጋል። አስቀድሞ የማያ ቃጥል የነበረው
ኋላ ማ ቃጠል መፋጀት ይጀምራል።
የእሳቱን ብርሃን ወርሶ የሚያበራም
ይሆናል። እሳትም የብረትን ባሕርይ
ባሕርይው ያደርጋል። በቀደመ አፏ
ፏፉ ቅርፅ የሌለው ሲሆን ኋላ ከብረት
ሲዋሐድ የብረቱን ቅርፅ ወርሶ ቅርፅ
ያለው ይሆናል። አስቀድሞ የማይ
ጨበጥ፣ የማይዳሰስ፣ የማይመታው
ኋላ ብረቱን በመዋሐዱ መጨበጥ፣
መዳሰስ መመታት ይጀምራል።
እንደዚሁ ሁሉ መለኮት አስ
ቀድሞ በአፏፏፉ ረቂቅ ሲሆን ነገር
ግን እሳት ብረቱን ተዋሕዶ እንደ
ሚታይ እርሱም ሥጋን ተዋሕዶ በግ
ዘፍ ታየ፤ ተገለጠ። እሳት ከብረት
ጋር ሆኖ በመዶሻ እንደሚመታ ነገር
ግን መዶሻው ባሕርይውን እሳትነቱን
እንደማያናውፅበት ሁሉ መለኮትም
ከተዋሐደው ሥጋ ጋር በአንድነት
በመኖሩ አብሮ መከራን ተቀበለ ሞቶ
ተቀበረ። ይህ ግን መለኮታዊ ባሕር
ይውን አላገኘውም /በመለኮት አልሞ
ተም/ በለበሰው ሥጋ እንጂ። በሌላ
በኩል ብረቱም አስቀድሞ የሌለውን
የማ ቃጠል ባሕርይ ከእሳት ወርሶ
እሳት ይሆናል፤ ያ ቃጥላል። በዚህ ዓይ
ነት ደካማ የነበረ ሥጋ ከመለኮት ጋር
በተዋሕዶ ሞትን ድል የሚያደርግ
ተአምራትን የሚሠራ ሆነ። ይህ ቅዱስ
ቄርሎስ ስለ መለኮት የመሰለው
ምሳሌ ነው።
ይኸው አባት በሌላ ሥፍራ
ለተዋሕዶ ምሳሌ እንዲሆን የነፍስና
የሥጋንም ተዋሕዶ ያነሣል። «የሚረ

ዳህስ ከሆነ የትስብዕትና /የሥጋና/ የመለኮትን ተዋሕዶ በእኛ ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ መስለን እንነግር ሃለን:: እኛ በነፍስ በሥጋ የተፈጠርን ነንና አንዱን የሥጋ አንዱን የነፍስ ብለን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ አናደር ገውም:: ሰው ከሁለት አንድ በመሆኑ አንድ ነው እንጂ:: ከሁለቱ ባሕርያት አንድ በመሆኑ ሁለት ሰው አይባልም:: በነፍስ በሥጋ የተፈጠረ ሰው አንድ ነው እንጂ:: ይህንንስ ካወቅን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተዋሕዶ በፊት እርስ በርሳቸው አንድ ካልነበሩ ከተዋሕዶ በኋላም ከማይለያዩ ከሁለት ባሕርያት አንድ እንደሆነ እናውቃለን:: /ሃይ.አበ.ዘቄርሎስ 78÷19/::

በእነዚህ ሁለት ምሳሌዎች እንደተመለከትነው ሁለት የተለያዩ ባሕርያት ያላቸው አካላት ተዋሕደው ያለመለያየት ያለመጠፋፋት አንድ ባሕርይ ስለሆኑ ተዋሐዱ ይባላል:: ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ /ሥግው ቃል/ ሥጋን የተዋሐደ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: ከተዋሕዶ በኋላ መለያየት አንችልም:: ይህ የመለኮት ነው ይህ የሥጋ ነው፣ አይባልም:: ሁለቱ በፍፁም ተዋሕዶ አንድ ሆነዋልና::

<u>ለምሳሌ:-</u> ጌታችን የሠራቸው ተአምራት ለዚህ ማስረጃ ይሆኑናል:: ዓይነ ስውሩን በምራቁ አፈር ለውሶ በመቀባት አዳነው:: ምራቅ የሥጋ ገንዘብ የነበረ ተአምር የመሥራት ኃይል ያልነበረው ሲሆን፣ አሁን ግን ሥጋ ፍፁም ከመለኮት ጋር ተዋሕዷልና ጌታችን በምራቁ ዓይን አበራ:: ይህን ዓይተን ተአምር የሠራው በሥጋው ነው፣ በመለኮት ነው፣ ብሎ መነጣጠል አይቻልም:: ጌታችን ከሐዋርያት ጋር በታንኳ ሲጓዝ አንቀላፋ:: ጌታ ሆይ ጠፋን ብለው ቀሰቀሱት:: ተነሥቶም ነፋሱን ገሠፀው:: እዚህ ላይ ከሥጋ ጋር የተዋሐደ መለኮት ሥጋ ሲያንቀላፋም አለ:: መለያየት የለባቸውም:: ጌታ ተነሥቶ ማዕበሉን ገሠፀ:: ከላይ እንዳየነው ማን ቀላፋት የሥጋ ባሕርይ ነውና ተኛ:: በመቀጠል ተነሥቶ ማዕበሉን ፀጥ አደረገው:: ባሕር መገሠፅ ፍጥረታትን ማዘዝ የመለኮት ባሕርይ በመሆኑ ይህ ይህንን አደረገ እያሉ መለያየት አይቻልም:: የተኛውም ተነሥቶ ማዕበሉን ፀጥ ያደረገውም አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው በመሆኑ ይተኛ፣ ይበላ፣ ይጠጣ፣ ተአምር ይሠራ፣ ሙት ያስነሣ... ነበር::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ነስቶ ሰው የሆነ አምላክ ነው:: ንል ሰው በመሆኑ በባሕርይው ተዋራጅነት የለበትም:: በሰማይ በዙፋኑ እየ ተመሰገነ በምድር ዞሮ አስተማረ መከራን ተቀበለ እንጂ:: ቅዱስ ያሬድ ስለዚህ « ፍጥረቱን ሁሉ የሚመግብ -ጌታቸው በብትሽ /በክንድሽ/ ተቀምጦ እንደ ሕጻን ጡትሽን ሲጠባ ባዩት ጊዜ በአርያም ፈለጉትና በዚህ ዓለም እንደ ቀድሞው ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አገኙት:: /ይህን ያዩ መላእክት ናቸው/ ፀሐይ ባለችበት ሆና ምድርን እንደ ምታሞቅ እርሱም በዙፋኑ ተቀምጦ /አለምን እየገዛ/ በምድር በሥጋ ማርያም ተገለጠ ሥጋን ተዋሕዶ ዞሮ አስተማረ::

በአጠቃላይ ስንመለከት ተዋሕዶ ማለት እንደ አውጣኪ ተጣፍቶ አንድ ባሕርይ ብቻ ሳንል እንደ ንስጥሮስ በመደረብ ሁለት ባሕርይ ነው ሳንል እንደ ሌሎች መናፍቃን በመቀላቀል...የሚል ሀሳብ ሳናስገባ መለኮት ከሥጋ ጋር ፍፁም በመዋሐዱ የኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ መሆኑን የምንመሰክርበት ነው::

ለመሆኑ ጌታችን በተዋሕዶ ሰውን ያዳነው ለምንድን ነው? ቅዱስ አትናቴዎስ እንደተናገረው::

ሀ. ሞት ጋር ከእኛ ጋር ተዋሕዶ ይኖር ነበርና ሞትን ይሽረው ይነቅለው ዘንድ መለኮት ከእኛ ሥጋ ጋር ተዋሐደ::

ለ. ዲያብሎስ በእባብ ሥጋ ተሰውሮ /ተዋሕዶ/ አዳምና ሔዋንን አሳስቷቸው ነበርና:: መለኮትም የሰውን ሥጋ ተሰውሮ /ተዋሕዶ/ ድል ነሳው:: ምሥጢርን በምሥጢር መመለስ የእግዚአብሔር ጥበብ ነውና::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ያስተምር በነበረበት ወቀት ሙት ያስነሣ፣ ድውያንን ይፈውስ፣ ማዕበሉን ይገሥፅ ነበር:: እነዚህ በፍጡር ሊሠሩ የማይችሉ ናቸው:: እርሱ አምላክ ስለሆነ አድረጓቸዋል:: በሌላ በኩል ይራብ፣ ይጠማ፣ መከራ ይቀበል ነበር:: አምላክ የማይራብ የማይጠማ መከራ የማይቀበል ነው:: እሱ ግን ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው ነውና ይህንን በፍቃዱ አድርጎታል:: ይህ ንን ለይተን እዚህ ላይ አምላክ ነበር:: በዚህ ቦታ ሰው ሆነ አንልም:: ይልቅስ ወልደ አብ ወልደ ማርያም /የአብ ልጅ የማርያም ልጅ/ ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው በመሆኑ ይህን አደረገ እንላለን እንጂ:: እሱ በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ በመሆኑ የሥጋንም የመለኮትንም ሥራ ሠራ:: በእርሱ ባሕርይ ተከፍሎ መለያየት የለበትም::

ስለ ጌታችን ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር:: «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ...» ይላል:: ሐዋ.20÷28:: መለኮት በባሕርይው ሥጋና ደም ያለው አይደለም ረቂቅ ነው እንጂ:: ነገር ግን የሥጋን ገንዘብ ገንዘቡ አድርጎ ከሥጋ ጋር ፍፁም ተዋሕዷልና እግዚአብሔር ደሙን አፈሰሰ ተባለ:: ከተዋሕዶ በኋላ መለኮትን ለብቻ ሥጋን ለብቻ መነጠል ስለማይቻል ይህ ተነገረ::

ይቀጥላል

## *<u>ማስተካከያ</u>*

*በሐመር በ7ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትማችን «ነገረ ድንነት» የሚል ጽሑፍ ማስነበባችን ይታወሳል:: በዚህ እትም ገጽ 13 ሁለተኛ ረድፍ ሦስተኛ ነጥብ ላይ ያለው «በሠላሳ ዘመኑ ልጅነቱን ቢያጣ» የሚለው ሐረግ «የሠላሳ ዘመን ጎልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ፣7ዓመት በገነት ኖሮ፣በምክረ ከይሲ ተታሎ ልጅነቱን ቢያጣ» ተብሎ ይነበብ ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን::*

## ነገረ ማርያም ...

/የመጨረሻው ክፍል/

2. መሥዋዕት እናቀርባለን ብለው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ቢሄዱ አይቀበሏቸውም እናንተማ ብዙ ተባዙ ብሎ ለአዳም የነገረውን ያስቀረባችሁ ርጉማን አይደላችሁምን- ቢጠላችሁ ነው እንጂ ቢወዳችሁማ ልጅ ይሰጣችሁ አልነበረምን -ይሏቸዋል:: ስለዚህ መሥዋዕታቸውን ስለ ማይቀበሏቸው በዚህ አዝነዋል::

3.ከአሰሩ-ገ-እሥራኤል -ከእሥራኤል ሽማግሎች-የወለዱ ሰዎች የሚመገቡት ተረፈ መሥዋዕት ነበር:: ያንን ነሥተዋቸው በዚህ ሁሉ አዝነው ሲመለሱ ርግቦች ከልጆቻቸው ጋር ሲጫወቱ ዕፅዋት አብበው አፍርተው አይታ ለሁሉ ልጅ ሰጥተኸዋል፣ ሐናን ጸንጊያ አድርገህ ፈጥረሃታልን- ብላ አልቅሳ ተመልሳለች ሁለቱም ከቤታቸው ገብተው ወንድ ልጅ ብንወልድ ወጥቶ፣ ወርዶ፣ አርሶ፣ ቆፍሮ ይርዳን አንልም፣ ለቤተ እግዚአብሔር አገልጋይ ይሆናል ሴት ልጅም ብንወልድ እንጨት ለቅማ ውኃ ቀድታ ትርዳን አንልም ለቤተ እግዚአብሔር መሶበ ወርቅ ሰፍታ መጋረጃ ፈትላ ትኑር ብለው ብፅዓት ገብተዋል:: ሐምሌ 30 ቀን በሌሊቱ ክፍለ ሰዓት ፀአዳ ርግብ 7ቱ ሰማያትን ሰንጥቃ መጥታ በማኀ ፀንዋ ስታድር፣ ለኢያቄም የፀምር መታጠቂያ ሲያስታ ጥቁት የብርሃን በትር ሲያሲዙት አይታ ነገረችው:: እኔም እንጂ ከደ ጃችን የነበረች ዛፍ አፍርታ ፍጥረት ሁሉ ሲመገባት አየሁ ብሎ ነገራት:: በህገራቸው መተርጉመ ህልም አለና፣ ሄደው ነገሩት ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ አላቸው፡ አንተስ አልፈታኸውም ጊዜ ይፍታው ብለው ነሐሴ 7 ቀን መልአክ ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ ብሏቸው በብሥራተ መልአክ በፈቃደ እግዚአብሔር እመቤታችን ተፀነሰች፡ በተፀነሰችም ጊዜ ገቢረ ተዓምር ተደርጓል፡ ለሐና ቤርሴላ የምትባል አንድ ዐይና እክስት ነበረቻት ሐና እግዚአብሔር በረድኤት ጎበኘሽ መሰለኝ ጡትሽ ጠቁሯል ከንፈርሽ አሯል ብላ ማኀፀኗን ዳሳ ዓይኗን ብትነካው በርቶላታል፣ ይህንንም አብነት አድርገው ህሙማን ሁሉ ማኅፀኗን እየዳሰሱ የሚፈወሱ ሆነዋል::

ዳግመኛም ሮቤልም ቢሉ፣ ሳምናስ የሚባል የአጎቷ ልጅ ሞቶ ትወደው ነበርና የአልጋውን ሸንኮር ይዛ እየዞረች ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት ተነሣ:: ከዚያም ሰማይንና ምድርን ለፈጠረ ለእውነተኛ ፀሐይ ክርስቶስ አያቱ የምትሆኚ ሰላምታ ይገባሻል ብሎ ከመተርጉመ ሕልም ተሰውሮ ረቆ የነበረውን የፀሐይን ምሥጢር ተረጎመው::

ከዚህ በኋላስ አይሁድ ለምቀኝነት አይቦዝኑምና ቀድሞ ከዚህ ወገን የሚሆኑ ዳዊት ሰሎሞን ነግሠው አርባ አርባ ዘመን እንደሰም አቅልጠው እንደገል ቀጥቅጠው ገዙን ደግሞ ከዚህ የሚወለደው እንደምን ያደርገን ይሆን ብለው በጠላትነት ተነሡባቸው፣ መልአክ ኢያቄምን ወደ አድባረ ሊባኖስ ይዘሃት ሂድ ብሎት በዚያው ወልዳታለች::

«ከሊባኖስ ሙሽራ ትወጣለች::» ብለው ጠቢቡ ሰሎሞንና ቅዱስ ያሬድ የተናገሩትም ቅሉ ይህ ነው:: *ተፈጸመ::*

# እኩል ናችሁ ሲል ከጎኑ ፈጠራት

/ከዓባይነህ ካሤ/

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በዓለም ላይ ያሉትን መገናኛ ብዙኃን እና በርካታ ድርጅቶችን ትኩረት እየሳበ የመጣ ዐቢይ ጉዳይ ነው:: አጀንዳው አነጋጋሪ በመሆኑም የተለያዩ ሰዎች እንደየ አመቺነቱ የየግል ሐሳባቸውን ይሰነዝራሉ:: በርካታ መንግሥታትም ብሔራዊ ፖሊሲ እያወጡበት ሲሆን ከዚያም አልፎ በተፈጻሚነቱ ላይም ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ላይ ናቸው:: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም እጅግ በጣም ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ሰፋ ያለ የለውጥ እንቅስቃሴ እያካሄደበት ይገኛል:: ይህም ሴቶች ከወንዶች ጋር ስላላቸው እኩልነት ነው::

ከቤተክርስቲያን ትምህርት አንፃር እንዴት ይታያል? ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸውን? በዚህ ርእሰ ጉዳይ መጠነኛ ግንዛቤ ለመስጠት እንሞክራለን::

ሴት ከወንድ እኩል ናትን? ብለን ከምንነሣ ሴት ከወንድ በምን ታንሳለች? ብለን ብንጠይቅ የተሻለ ይሆናል:: ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን አወዳድሮና መዝኖ ትክክለኛ ፍርድ መስጠት አይቻልም:: ይህ የሚቻለው ለፈጣሪ ብቻ ነውና:: ስለዚህም የተለያዩ ሰዎች የሚሰጧቸውን መመዘኛዎች አስቀድሞ መመልከት ተገቢ አይሆንም::

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት በፊት ሴት ከወንድ ታንሳለች የሚለው ጥያቄ የሚታየው ከምን አንፃር ነው? የሚለውን ማየት ያስፈልጋል:: በዚህ በኩልም በአብዛኛው አነጋጋሪ ሆኖ የሚታየው በስብእና ወይም በሥነ ተፈጥሮ ሚዛን የሚነገረው ነው:: ለመሆኑ የወንድና የሴት ሥነ ተፈጥሮ ምን ይመስላል?

ምንም እንኳን ሄዋን የተፈጠረችው አዳም ከተፈጠረ ከአንድ ሳምንት በኋላ ቢሆንም በሥነ ተፈጥሮ ወንድና ሴት አንድ ጊዜ የተፈጠሩ ናቸው:: አዳም ከሔዋን ሔዋንም ከአዳም የቀደሙበት ወይም ወደኋላ የቀሩበት ሁኔታ የለም:: ሁለቱም የዕለተ ዓርብ ፍጥረቶች ናቸው:: ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው::» በማለት ይገልጠዋል:: ዘፍ.1÷27::

በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ካለ በኋላ «እግዚአብሔር አምላክም አለ:- ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም:: የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» በማለት ስለ ሔዋን ይናገራል:: ዘፍ.2÷18:: በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሥላሴ «እንፍጠርለት» በማለት እንደ ስድስቱ ዕለት ፍጥረታት ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣትን አያመለክትም:: ምክንያቱም ሥላሴ ይህን የተናገሩት ዓለምን መፍጠር ፈጽመው በሰባተኛው ቀን ካረፉ በኋላና ሰውን በዔድን ገነት ወስደው ካኖሩት በኋላ ነው:: እግዚአብሔር ደግሞ ከዚያ በኋላ አዲስ ፍጥረት አልፈጠረም:: ሃያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረታት በስድስቱ ዕለታት ውስጥ ተጠቃለው ተፈጥረዋልና::ለዚህ በሁለተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንፍጠርለት የሚለው ቃል አስቀድመን በአንድ ላይ ከሰውነቱ አዋሕደን የፈጠርንለትን የኑሮ ጓደኛውን በአካል አግዝፈን እና ሳየው ለማለት የገባ ነው:: «ረዳት እንፍጠርለት» ከመባሉ በፊት የተፈጠረው ሰው እንደሆነ እንጂ አዳም ብቻ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም:: ሰው የሚለው ደግሞ የአዳምና የሔዋን የጋራ መጠሪያቸው ነው:: ምክንያቱም ሰው (አዳም እና ሔዋን) ከተፈጠሩ በኋላ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሥልጣን ሲናገር ለአንድ ሰው እንደሚናገር ሳይሆን ለሁለትና ከዚያም በላይ ለሆኑ እንደተናገረ እናያለን:: በጊዜው ደግሞ ከአዳምና ከሔዋን አልፎ ስለሌላ ሦስተኛ ሰው ሊነገር እንደማይቻል ይታመናል:: ቃሉም እንዲህ የሚለው ነው::

«ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው:: እግዚአብሔርም ባረካቸው÷ እንዲህም አላቸው:- ብዙ÷ ተባዙ÷ ምድርንም ሙሏት÷ግዟትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዟቸው::» ዘፍ.1÷28:: ለአዳም ብቻ ተናግሮ ቢሆን ኖሮ በብዙ አንቀጽ ባልተጻፈ ነበር:: ነገር ግን ምንም እንኳን ከአዳም ሰውነት ጋር ተዋሕዳ ብትኖርም ሔዋንም አብራ ስለነበረች እግዚአብሔር በብዙ አንቀጽ ተናገረ:: ስለዚህ አዳም ሔዋንን በሥነ ፍጥረት አይቀድማትም::

ለዚህም አባባላችን የበለጠ ማጠናከሪያ የሚሆነን ሔዋን ከአዳም ጐን ከተወሰደች አጥንት ወደ ባለሙሉ አካልነት መምጣት ነው:: ዘፍ.2÷21 አዳምም ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ ሔዋንን ካጠገቡ ባያት ጊዜ «ይህች አጥንት ከአጥንቴ ሥጋዋም ከሥጋዬ ናት» ሲል ተናግሯል:: ዘፍ.2÷23:: ለአዳም ያለው ሁሉ ለሔዋንም አላት ማለት ነው:: ከራሱ ከአዳም አጥንት የተወሰደች ናትና ከአዳም ታንሳለች ማለት አይቻልም:: የራሱ ሥጋና አጥንት ከራሱ ሰውነት ጋር አንድ ነው እንጂ የሚያንስ የሚብልጥ የለበትምና:: አዳም ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ እና ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ እንደ ተፈጠረ ሁሉ ሔዋንም ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ እና ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ የተፈጠረች ናት:: ከፆታ ልዩነት በስተቀር ለአዳም የተሰጠው አካል ሁሉ ለሔዋንም አላት:: ስለዚህም እግዚአብሔር አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ አድርጎ እንዳልፈጠረ እንረዳለን::

አባቶቻችን እንደዚህ ስላለው ነገር ሲናገሩ «እግዚአብሔር ሔዋንን ከአዳም ሠራት፤ ከፍ ብሎ ከአናቱ አይደለም፤ አለቃ ገዥህ ነኝ እንዳትለው ዝቅ ብሎ ከእግሩም አልሠራትም የበታች ነሽ ባሪያ ነሽ እንዳይላት ብሎ:: ነገር ግን ከጐኑ ሠርቷል እኩል ናችሁ ሲላቸው» ይላሉ:: ይህም ሔዋን በሥነ ተፈጥሮ ከአዳም በምንም እንደማታንስ ያጠይቃል:: እግዚአብሔር ረዳት እንፍጠርለት ማለቱም ባሪያ አገልጋይ ታዛዥ ማለቱ ሳይሆን ጓደኛ፣ አቻ ማለቱ ነው::

አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ከወንዶች እንደሚያንሱ ይናገራል ይላሉ:: ይህ ግን ፈጽሞ ትክክል ያልሆነ አመለካከት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አልተናገረምና:: የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው ሰዎች የሚያነሡት ቅዱስ ጳውሎስ «ሚስቶች ሆይ÷ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና:: ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ::» ሲል የተናገረውን ነው:: ኤፌ.5÷22–24:: ነገር ግን ይህ ምን ማለት እንደሆነ ቀጥለን እንመለከታለን::

አንድ ሰው ሕዝብን እንዲገዛ ቢመረጥ እንዲመረጥ ያደረገው ሥነ ተፈጥሮው ከሌላ ሰው የላቀ ወይም የተለየ ስለሆነ አይደለም:: ነገር ግን የተሰጠው የመምራት ወይም የማስተዳደር ጸጋ ለሥልጣን አብቅቶት ሊሆን ይችላል:: በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከባል ሌላ ሌሎች ወንዶች ልጆችም ሊኖሩ ይችላሉ:: ከእነዚህ መካከል ባል ወይም አባት የቤተሰቡ መሪ ወይም አባወራ ይሆናል:: ይህ ማለት ግን ከወለዳቸው ወንዶች ልጆች በሥነ

➡

ተፈጥሮ በልጧል ማለት አይደለም።
ልጆቹን በዕድሜ ስለሚበልጣቸው፣
ከእነርሱም ይልቅ ብዙ ነገር ቀድሞ
ስለሚያውቅ እነርሱ ሳይወለዱም የተለ
ያየ ኃላፊነት የነበረው በመሆኑ አባ
ወራ ይሆናል። በዚህ ሁኔታ አባት
ቤተሰቡን ቢመራ ወይም ቢያስተዳድር
ኃላፊ ነው እንጂ በተፈጥሮ የተለየ
ወይም የላቀ ነው አይባልም።

የቤተሰብ ኃላፊነት ደግሞ
የግድ ለአንድ ሰው መስጠት አለበት።
ስለዚህ ደግሞ ባል ይመረጣል። አዳም
ሲፈጠር እንደ ሠላሳ ዓመት ጐልማሳ
የነበረ ሲሆን ሔዋንም ደግሞ የአሥራ
አምስት ዓመት ቆንጆ ነበረች። በዘ
ህም መሠረት ከዚያ በኋላ በመጽሐፍ
ቅዱስ የተገለጡት የተቀ ደሱ ጋብቻ
ዎች የወንዱን በዕድሜ መብለጥ የሚ
ያንጸባርቁ ናቸው። ከዚህ በመነሣት
ቅዱስ ጳውሎስ ባል የሚስት ራስ ነው
ብሏል። ለባሎቻቸው ይገዙ ማለቱም
እንደ ባሪያ እንደ አገልጋይ ማለት
ሳይሆን በፈቃደኝነትና በፍቅር ላይ
የተመሠረተ አባወራነቱን ይቀበሉ ለማ
ለት ነው።

ደግሞም ቅዱስ ጳውሎስ ሚስ
ቶች ለባሎቻችሁ ተገዙ ብሎ ያቆመ
አይደለም። ከዚያው ወረድ ብሎ የሚ
ከተለውን ኃይለ ቃል አያይዞ ተናግሯ
ል። «ባሎች ሆይ÷ ክርስቶስ ደግሞ
ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻ
ችሁን ውደዱ... እንዲሁም ባሎች
ደግሞ እንደገዛ ሥጋቸው አድርገው
የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዷቸው ይገባ
ቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን
ይወድዳል፣ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚ
ጠላ ከቶ የለምና» ኤፌ.5÷ 25–30።

ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የወ
ደዳት እስከምን ድረስ ነው? የተባለ
እንደሆነ እስከሞት ራሱን መሥዋዕት
አድርጐ እስከ ማቅረብ። ባልም ሚስ
ቱን እስከሞት ድረስ ማለትም ለእርሷ
መሥዋዕት እስኪሆን ድረስ የመው
ደድ ኃላፊነት አለበት። ባል ሚስቱን
እንዲወድዳት እንጂ ከእኔ ታንሳለች
ብሎ እንዲያስብ አይደለም። ምክንያ
ቱም እርሷ ሥጋው ናትና። የራሱን
ሥጋ ደግሞ ከእኔ ያንሳል ብሎ ሊና
ገር የሚችልበት ምክንያት የለ ውም።
ማንም ወንድ ወይም ባል ሥጋውን
ሊጠላ አይችልም። በሥጋው መከራ፣
ስቃይ፣ ጭንቀት ወይም ሕማም እን
ዲያገኘው አይፈልግም። እንደዚ ሁም
ሁሉ ባል ለሚስቱ ይህን ያኸል የማ
ሰብ ግዴታ ተጥሎበታል።

ምንም እንኳን ሐዋርያው
«ሚስቶች ለባሎቻቸው በሁሉ ይገዙ»
ያለ ቢሆንም ይህ በበላይነትና በበታ
ችነት ስሜት የሚከናወን ሳይሆን በፍ
ቅር የሚፈጸም ነው። ፍቅር ደግሞ
ሁሉን ታቸንፋለች። «ፍቅር ሰሀቦ ለወ
ልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ
ለሞት–ፍቅር ኃያል ወልድን ከመንበሩ
ሳበችው እስከሞትም አደረሰችው።»
እንዲል።

ጌታችን ቢወድደን እርሱ
ፈጣሪያችን ሳለ ከሰማያዊ መንበሩ
መጥቶ የታመምነውን ፈወሰን፣ የጠፉነ
ውን መለሰን፣ ዝቅ ብሎም አገለ
ገለን። በቀራንዮ አደባባይም ፍቅሩን
ገለጸልን። የፍቅር ኃይሏ እስከዚህ
ድረስ ነው። በፍቅር መካከል የበላይ
ነት የበታችነት ስሜት የለም። ፍቅር
ካለ አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ እየተ
ባባሉ ተደጋግፎ መኖር ይመጣል።
እንግዲያውስ ሁለቱም (ባልና ሚስት)
የፍቅር ባርያዎች ናቸው። በተሳሳተ
መንገድ የሚተረጐሙት ይኑሩ እንጂ
ፍሬ ቃሉ እንደዚህ ያለ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም
በቅዱስ ጳውሎስ አባባል ይስማማል።
«በቀድሞ ዘመን በእግዚአብሔር ተስፋ
ያደረጉት ቅዱሳት ሴቶች ደግሞ ለባ
ሎቻቸው ሲገዙ ተሸልመው ነበርና፣
እንዲሁም ሣራ ለአብርሃም፦ ጌታ
ብላ እየጠራችው ታዘዘችለት።» እን
ዲል። 1ጴጥ.3÷5–6። ሐዋርያው «ሣራ
ጌታዬ ብላ ታዘዘችለት» ሲል ሚስት
ለባሏ ልታደርግ የሚገባትን ሁሉ አደ
ረገችለት ማለቱ ነው። እርሷ ጌታዬ
ስትለው እርሱ ደግሞ እመቤቴ ይል
ነበርና። ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ
አያይዞ «ባሎች ሆይ÷ ደካማ ፍጥረት
ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል
ኑሩ።» ሲል ተናግሯል። 1ጴጥ.3÷7።
ይህም ብንይዝ እናጠቃቸ ዋለን ብንሰ
ነዝር እናደቅቃቸዋለን ብላችሁ ሚስቶ
ቻችሁን አትናቁ ማለት ነው።

«የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ÷
የሴትም ራስ ወንድ÷ የክርስቶስም ራስ
እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ እወ
ድዳለሁ።» ተብሎም ተጽፏል። 1ቆሮ.
11÷3። ሐዋርያው የሴትም ራስ ወን
ድ ሲል ምን ለማለት ፈልጐ ነው?
በዚህ የመጽሐፍ ክፍል ራስ የሚለው
ቃል የሚያመለክተው መገኛ መሆንን
ነው። ይህም የክርስቶስም ራስ እግዚ
አብሔር ባለው ይታወቃል። በዚህኛው
አነጋገር እግዚአብሔር የተባለ አብ
ነው። አብ ለክርስቶስ ራስ መባሉም
በሥልጣን፣ በአገዛዝ ወይም በሕልውና
ስለሚበልጠው አይደለም። እንደዚህ
እንዳንል «እኔና አብ አንድ ነን»፣
«ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው።» ሲል
ጌታችን ከአብ ጋር በትክክልነት ያለ
ልዑለ ባሕርይ መሆኑን አስረድቶናል።
ዮሐ.10÷30፣ 16÷15። ነገር ግን
ወልድ የአብ ልጁ ነው። ማቴ.3÷17፣
17÷5። ቅድመ ዓለም ያለ እናት
አብን አክሎ አብን መስሎ ተወልዷ
ልና። በዚህም ልደቱ መቅደም መቀ
ዳደም የለበትም። ወልድ (ክርስቶስ)
ከአብ ተወልዷል (ተገኝቷል) ወይም
አብ ወልድን ወልዷል ለማለት የክር
ስቶስም ራስ እግዚአብሔር ነው ተብ
ሏል። እንደዚሁም ሴት ከአዳም ጐን
ተገኝታለችና ከአዳም መገኘቷን ለማጠ
የቅ የሴት ራስ ወንድ ነው በማለት
ሐዋርያው ተናግሯል። ወልድ ከአብ
በመወለዱ እንዳላነሰ ሁሉ ሴትም
ከአዳም ጐን በመገኘቷ አታንስም
ሲል ነው።

ወንዶች በዚህ እንዳይመኩ
ሐዋርያው በዚያው ምዕራፍ እንዲህ
ሲል ተናግሯል። «በጌታ ዘንድ ሴት
ያለ ወንድ ወንድም ያለ ሴት አይ
ሆንም። ሴት ከወንድ እንደሆነች እን
ዲሁም ወንድ ደግሞ በሴት ነውና፣
ሁሉም ከእግዚአብሔር ነው።» በማ
ለት አስተምሯል። 1ቆሮ.11÷11–12።
ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን ምዕራፍ
በተረጐመበት ድርሳኑ «የቀደመችው
ሴት ከወንድ በመገኘቷ የወንዶች
ትምክህት እንዲጠፋ እመቤታችን
ቅድስት ድንግል ማርያም የሚበልጠ
ውን አምላክ ያለዘርዐ ብእሲ ወለ
ደች።» ብሏል። ከዚህም የምንረዳው
በቤተክርስቲያን ትምህርት ወንዶች
ከሴቶች እኩል መሆናቸውን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ወንዶ
ች ሁሉ ለሴቶችም የሚገባቸውን ቦታ
ሰጥቷቸዋል። ለወንዶች ከተሰጠው ጸጋ
ለሴቶች የቀረባቸው ምንም የለም።
ይህም እኩልነታቸውን ያንጸባርቃል።
ቤተክርስቲያንም ያለ ሴቶች አልተመ
ሠረተችም። ከመጀመሪያዎቹ መቶ
ሃያ የሃይማኖት ቤተሰቦች መካከል
ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ነበሩ፤
ሥራ.1÷14–15።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ
በነቢይነት የሚታወቁት በአብዛኛው
ወንዶች ቢሆኑም የሴት ነቢያትም
ነበሩ፤ ነብይነት ከእግዚአብሔር የሚሰ
ጥ ጸጋ ሲሆን ኃላፊነቱ ከባድ ነው።
በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ
የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝብ የሕዝ
ብን ጩኸት ደግሞ ወደ እግዚአ
ብሔር ያደርሳል። ስለ መጻየትም ይና
ገራል። ሕዝቡንም ይመራል። ይህ ኃላ
ፊነት ለእነ ሙሴና ኤልያስ እንደተ
ሰጠ ሁሉ ለሴቶችም አልቀረባቸውም።
እንደ ዲቦራና ሐናን የመሳሰሉ አንስት
ነቢያት ነበሩና። መሳ.4÷4። ሉቃ2
÷36።

ከነገሥታትም መካከል በፈሪሀ
እግዚአብሔር የታነጸች ንግሥተ ሳባ
ትጠቀሳለች። 1ነገ.10÷1። እምነትን
ከንግሥና ጋር አስተባብራ በመያዝ የሰ
ሎሞንን ጥበብ ለማየት ሠራዊቷን አስ
ከትላ ብዙ ሺህ ኪሎሜትሮችን አቋ
ርጣ በወቅቱ ገናና ከነበረው ንጉሥ
ሰሎሞን ጋር መሳ ለመሳ (እኩል በእ

ኩል) ለመነጋገር የበቃች ታላቅ ሰው ናት። ጌታችንም ስለ እምነቷ አመስግኗታል። ማቴ.12÷42። ሴት ስለሆነች መምራትና ማስተዳደር አትችልም አልተባለም።

ከሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ በማዕረገ ቅድስና የሚጠራቸው በርካታ ሴቶች ይገኛሉ። እንዲያውም ለፍጥረታት ከተሰጠው ጸጋ የሚበልጥ ጸጋ የተጐናጸፈች ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት። መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን በመሆኗ ከእርሷ የሚተካከል ቅድስና ንጽሕና ያለው ፍጡር አይገኝም። ከእመቤታችን ባሻገር እነ ሣራ፣ ርብቃ ራሔል፣ ሐና እመሳሙኤል፣ ሩት፣ አስቴር፣ ኤልሳቤጥ፣ ማርያም እንተ ኀፍረት፣ ሰሎሜ... ወዘተ ይጠቀሳሉ። ከሰማዕታት መካከልም ቢሆን እንደ አርሴማ ቅድስት ኢየሉጣ የመሳሰሉ ሴቶች አሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ወንዶች ቅዱሳን ሁሉ የአንስትንም ገድል አካትቶ ይገኛል። በየመጽሐፉ ከተወሱት የቅዱሳት አንስት ተጋድሎ ሌላ እነ መጽሐፈ አስቴር፣ መጽሐፈ ሩት፣ መጽሐፈ ዮዲትና መጽሐፈ ሶስናን መመልከቱ ይበቃል። ከጀግኖችም መካከል ኃይለኛውን መሪ ሆሎፎርኒስን የገደለችው ዮዲት ትጠራለች። ከዘማርያንም መካከል ከበሮዋን ይዛ «እግዚአብሔር ተዋጊ ነው ስሙም እግዚአብሔር ነው እያለች» የዘመረችው ማርያም እኅተ ሙሴ አለች። ዘጸ.15÷20።

በዘመነ ሐዲስ ተቀዳሚና ዋነኛ አገልግሎት ሆኖ የተሰጠው የማስተማር ሥራ ነው። በዚህም ዘርፍ ሴቶች ቀጥተኛ ተሳታፊዎች እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። ከሁሉም በላይ ከሰው ልጆች መካከል የመጀመሪያው የትንሣኤ ሰባኪዎች ሆነው ከጌታችን የተላኩት አንስት ናቸው። ማቴ.28÷9። ይህም በእምነታቸው የተደረገላቸው እግዚአብሔር የሰጣቸው ጸጋ ነው።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንም ይህንን መሠረት አድርጋ ለሴቶች የሚገባ ቦታ ሰጥታቸዋለች። በክህነትም ቢሆን ዲያቆናዊት የምትባል ሴት አለች። እንደዚሁም ዐቃቢት የምትባል አለች በቤተክርስቲያን አገልግሎት የዲያቆናዊቷ ድርሻ በቅዳሴም ሆነ በሌሎች ጊዜያት የሚመጡትን ሴቶች በየማዕረጋቸው ታቀማለች። ሴቶች ጉዳይ ለማስፈጸም ወደ ካህናት ሲመጡ ታቀርባለች። እንደዚሁም ዲያቆናዊቷ ማይ (ውኃ) ትቀዳለች፣ የግብር ስንዴ ትሰይማለች ለዲያቆኑም ታስረክባለች። በምናኔው ዓለምም የቅድስት ክርስቶስ ሰምራ ተከታዮች በርካታ መናንያንና መነኮሳይያት አሉ። ለብቻቸውም የሴቶች ገዳም ተገድሞላቸው የቅድስና ኑሯቸውን ሲያከናውኑ እንደነበረ ሁሉ አሁንም ይፈጽሙታል።

ከዚህም ባሻገር ጉባኤ መሥርተው ወንበር ዘርግተው የሚያስተምሩ አንስት ሊቃውንት አሉ። በተለይም እጅግ ከባድ የሆነውን የቅኔን ትምህርት የሚያስተምሩ አንስት በቤተክርስቲያን ይገኛሉ። ከጥቂት ዓመታት በፊት በሞት የተለዩት እማሆይ ገላነሽ በዚህ ሙያ ስማቸው ከገነነው ጥቂት ሊቃውንት መካከል አንዷ ናቸው። ከእርሳቸውም በፊት ሌሎች መምህራን የነበሩ ሲሆን ዛሬም ተከታዮቻቸው በየአብያተ ክርስቲያናቱ አሉ። ለምሳሌ:- በአዲስ አበባ በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም አንዲት የቅኔ መምህርት ሲኖሩ፣ በተመሳሳይ ሙያ በአክሱም ጽዮንም ሁለት መምህራን አሉ። በሌ ሎች ቦታዎች የቤተ ክርስቲያንን ችግር ችግራቸው አድርገው ጉባኤ ዘርግተው የሚያስተምሩ አንስት ይኖራሉ። እምነ ወለተ ጴጥሮስ ወንጌልን ተዘዋውሮ በማስተማር የታወቀች ቅድስት እናታችን ናት።

ሴቶች አስተምረዋል ከተባለ ቅዱስ ጳውሎስ ሴቶች በጉባኤ ፊት ዝም ይበሉ ለምን አለ? 1ቆሮ.14÷ 34–35፣ 1ጢሞ.2÷11–12።

ቅዱስ ጳውሎስ አንዳንድ ሕግጋትን ከሰዎቹና ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ አውጥቷል። ለምሳሌ:- «ኤጲስ ቆጶስ (ጳጳስ) የማይነቀፍ÷ የአንዲት ሚስት ባል እንዲህ ሊሆን ይገባዋል።» ብሏል። 1ጢሞ.3÷2። ከዚህም በዚያ ወቅት ያገቡ ሰዎች ሌሎችን መስፈርቶች እስካሟሉ ድረስ ጳጳስ መሆን ይችሉ እንደነበር እናያለን። ነገር ግን ከጊዜ በኋላ ኤጲስ ቆጶሳት በሥርዓተ ምንኵስና በድንግልና ከሚኖሩት መካከል ቁምስና ካገኙ በኋላ እንዲሾሙ ተደንግጓል።

በተጨማሪም «ከወንድሞች ወገን ያላመነች ሚስት ያለችው ቢኖር እርሷም ከእርሱ ጋር ልትቀመጥ ብትስማማ÷ አይተዋት፤ ያላመነ ባል ያላት ሚስትም ብትኖር ይህ ከእርሷ ጋር ሊቀመጥ ቢስማማ አትተወው።» በማለት ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ትእዛዝ አውጥቷል። 1ቆሮ 7÷12–13። ይህም በወቅቱ የነበሩትን ሰዎች ሁኔታ ያገናዘበ ነው። ነገር ግን ይህ ትእዛዝ በዚያ ወቅት ተፈጥሮ ለነበረው ሁኔታ ሲባል የወጣ እንጂ እስከዛሬ የሚሠራበት አይደለም። በወቅቱ ክርስትና እንደ አዲስ ለአሕዛብ ይሰበክ የነበረ መሆኑ ከባልና ከሚስት አንደኛቸው ቀድመው ክርስትናን የሚቀበሉበት ሁኔታ ነበረ። በዚህ ጊዜ የቆሮንቶስ ሰዎች ይወስዱት የነበረው እርምጃ ፈጣን ሆነ። ይህም ባል ከሚስቱ ቀድሞ ካመነ ሚስቱን ይፈታታል፣ ሚስትም ቀድማ ካመነች ባሏን ትፈታ ጀመር። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ አብረው ለመኖር እስከፈቀዱ ድረስ ሚስት ወይም ባል አላመኑም ብላችሁ አትፍቱ። ምክንያቱም ያላመነው ወገን ባመነው ሥነ ምግባር ተመርቶ ክርስትናን ሊቀበል ይችላልና በማለት መልእክቱን አስተላልፏል።


ይህ መልእክት ግን ዛሬ ተፈጻሚነት የለውም። ምክንያቱም ያመነ ወንድ ያመነች ሴት የማግባት ዕድሉ አለውና። ዛሬ ባልና ሚስት ከክርስትና እምነት ውጪ ያሉ ቢሆኑና ከሁለቱ አንዱ ክርስትናን ቢቀበል ያመነው ወገን ያላመነውን ማስመከር ይገባዋል። በዚህ ወቅት ያመነው ወገን አምናለሁ ካለ መፍታት ይቀራል አላምንም ካለ ግን መለየት ይገባል።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ በወቅቱ ቅዱስ ጳውሎስ ሴቶች አያስተምሩ ብሎ ደንግጓል። ይህም ለጊዜው ሴቶች ለማስተማር በሚነሡበት ወቅት ብዙ ችግሮች በመከሠታቸው ነው። ብዙ ወንዶች በሴቶች ተሰናከሉ፣ ከዚያም ባሻገር ሴቶች በማስተማር ሰበብ ትዳራቸውን እየተው ከአገር አገር መዘዋወር ጀመሩ። ይህንንም ለማስቀረት ቅዱስ ጳውሎስ ወቅታዊ የሆነ መፍትሔ «ሴቶች አያስተምሩ» በማለት ተናገረ። እንጂ እንዲያስተምሩ አልተፈቀደም ለማለት አይደለም።

በእርግጥ ከተፈጥሯዊ ሁኔታ አንፃር ዛሬም ቢሆን ሴቶች እንደ ቅድሚያ አማራጭ ያስተምሩ ማለት ይከብዳል። ሐዋርያዊ ተልእኮ ብዙ ውጣውረድና ፈተና የበዛበት ነው። አንዲት ሴት ምንም እንኳን ይህንን ፈተና በእግዚአብሔር አጋዥነት ለመወጣት የምትችል ቢሆንም ፈተናዋ ግን ከወንዱ ይልቅ የበለጠ ይሆናል፡ ሴትነቷን የሚፈታተን ችግር ያጋጥማታል። በመድረክ ላይ ስትቆምም ሰማዕያኑ ሌላ ነገር ወደማሰብ ያዘነብላሉ። ይህንን የመሳሰሉ ችግሮችን ለማስወገድ እንደ ሕግ ወይም ሥርዓት ሳይሆን አማራጭ እስካልጠፋ ድረስ ሴት ባታስተምር ይመረጣል።

**ሴቶች ለምን ሥልጣነ ክህነት አይቀበሉም ?**

/ይቀጥላል/



# ምዕራፍ



አዘጋጅ ደምሴ ነጋሽ

## ከጥንት ደብዳቤዎች

«በእኛ ዘንድ የጌታችንን እናት ለማየት የሚሹ ብዙ ሴቶች አሉ። ዘወትርም ወደ አንተ ለመምጣት፣ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን በታቀፈችባቸው እጆቿ መዳሰስ እንዲሁም ከእርሷ መማርን ይናፍቃሉ። እመቤታችን የአምላክ እናት እንደሆነች፣ ንጽሕት፣ ቅድስትና ዘላለማዊት ድንግል እንደሆነች በማመን ከፍ ከፍ እናደርጋታለን። በመከራና በመሳደድ ደስተኛ እንደሆነች፣ በማጣትና በችግር እንደማታዝን፣ በሚነሳሱባትም ላይ እንደማትቆጣ ብቻ ሳይሆን መልካም እንደምታደርግላቸውም በእኛ ዘንድ የታመነ ነው። እመቤታችን ለድሆች የምትራራና በሁሉ እንደምትራዳቸው፣ በደስታም ጊዜ በዝግታ የምትኖር መሆኗን እናውቃለን። ነገር ግን እምነቷን /ሃይማኖቷን የሚጻረሩትን አጥብቃ ትቃወማቸዋለች።

እመቤታችን ለሚያምን ሁሉ የመልካም ሥራ መሪ የጽናት፣ የትዕግሥትና የትሕትና መምህርት ናት። ከሁሉ አብልጣ ትኅትንን ትወዳለች፤ እርሷም ለሁሉ ትኁት ናትና። የአይሁድ ሕግ አዋቂዎችና ፈሪሳውያን በተሳለቁባት ጊዜ በትኅትና መቀበሏ የሚገርም ነው፤ የምናምናቸው ሰዎች በጌታችን እናት በማርያም ንጽሕና የተነጣ የሰው ባሕርይ የመላእክትን ባሕርይ እንደመሰለ ነግረውናልና። በዚህ ሁሉ የተነጣ በልባችን ያለው እመቤታችንን የማየትና ድምጿን የመስማት ፍላጎት ልንናገር ከምንችለው በላይ ሆኗል።»

«የሚቻለኝ ቢሆን ወደ ኢየሩሳሌም ልመጣና በዚያ የተሰበሰቡትን ክርስቲያኖች (አማንያን) ላያቸው እስባለሁ። ይልቁንም የጌታችንን እናት ለማየት እናፍቃለሁ። ብዙዎች እርሷን ያዩ ክብርት መሆኗን ከዚህም ጋር ትኁትና በእርጋታ የምትናገር፣ ደስ የምታሰኝ እንደሆነች ነግረውናል። ይህም በፈጠረብን መደነቅ ሁላችንም ልናያት እንናፍቃለን። ግን ሰማያዊውን አምላክ በሆዷ የያዘችውን፣ በድንግልናም የወለደችውን ቅድስት ለማየት የማይሻ ማን ይኖራል?»

ቅዱስ አግናጥዮስ ለወንጌላዊው ዮሐንስ ከጻፈለት ደብዳቤዎች የተወሰደ።
(ምንጭ:- THE ASSUMPTION OF OUR MOST HOLY LADY, THE MOTHER OF GOD AND-VIRGIN MARY 1990)

## ሁለተኛው ማነው?

(በመጽሐፍ ቅዱስ)

1. ረጅም ዘመን በመኖር አንደኛው ሰው ማቱሳላ ነው። የኖረውም 969 ዓመት ነው። ሁለተኛው ማነው?
2. የመጀመሪያው የእሥራኤል ንጉሥ ሳኦል ነው። ሁለተኛው ማነው? (ጥቆማ:- ዳዊት አይደለም)
3. በሐዲስ ኪዳን የመጀመሪያው ሰማዕት እስጢፋኖስ ነው። ሁለተኛው ማነው?
4. የያዕቆብ የመጀመሪያ ልጅ ሮቤል ነው። ሁለተኛው ማነው?
5. በመጽሐፍ ቅዱስ ስማቸው ከተጠቀሱት ሴቶች ሔዋን የመጀመሪያዋ ሴት ናት። ሁለተኛዋ ማን ናት? (ጥቆማ:- የቃየል ሚስት ስም አልተጠቀሰም)

## አስብ

- ኃጢአት በሠራህ ጊዜ የምትሞትበትን ቀን
- በጠገብክበት ወራት የተራብክበትን ዘመን
- በተሾምክበት ጊዜ የተሻርክበትን ዕለት
- ጤነኛ ስትሆን የታመምክበትን ቀን
- ባለጸጋ ስትሆን የችግርህን ጊዜ
- በደስታህ ዕለት ያዘንክባቸውን ወራት
- እግዚአብሔር ከፍ ሲያደርግህ አፈር መሆንህን አስብ። ይህን ስታስብ ከትዕቢትና ከጥፋት ትድናለህ።

ሙሉነሽ
/ከአዲስ አበባ/

## የተሰወረችዋ ምንጭ

ከአቁማዳው ውኃ
... ነጥፎብሽ
ትሸሺበት ጥጋት
... አጥተሽ
የበረሃው ምንጭ
...ተሰውሮብሽ
በአውላላ በረሃ አየሁሽ።
በምድረ በዳው ፈተና
ሕፃንሽ ቢያዝ በቀጠና
በሞት ሲነጠቅ ሳታይው
በቁጥቋጦ ሥር አኖርሽው
ወልደሽው ሳስ ጣልሽው።
... በሲቃ ዕንባ ውስጥ ቆዘምሽ
ተስፋሽን ለበረሃው ገበርሽ
እንዳይቀር:- ዕንባሽ ፈሶ ተስፋሽ ተኖ
እንዲመራሽ መልአኩን ላከው ፈጥኖ።
ቃሉ መራሽ ወደ ምንጩ
ተቀጠፈ የጥማት ልምጩ።
የተሰወረብሽ ምንጭ መታየቱ
በቃለ መልአኩ
አብነታችን ነውና ተስፋሽ መሰምሰሙ
ንገሪን ስለ መልአኩ።
አጋር ሆይ ንገሪያቸው ስለ መልአኩ።

ሰሎሞን ወ/መድኅን
/ከልደታ/

## አንድ ሲባዛ በአሥር

*የአገሩም ሰዎች ዘመዶቹም ገንዘቡን ሲበትን አይተው ተሰብስበው መጥተው ይህን ያህል ገንዘብ በአንድ ጊዜ ለምን ታጠፋለህ አሉት። አባታችን ተክለሃይማኖትም የማጠፋ አይደለም አሥር እጅ ይሆንልኝ ዘንድ አበዛለሁ እንጂ አላቸው።*

ገድለ ተክለ ሃይማኖት ምዕ. 28

## የሁለተኛው ማን ነው?

### መልሶች

1. ያሬድ
2. ኢያቡስቴ
3. ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ (ወልደ ዘብዴዎስ)
4. ስምዖን
5. የላሜሕ ሚስት ዓዳ (ዘፍ.4÷19)

ሦስተኛው ማን ነው?
መጽሐፍ ቅዱስዎን ያገላብጡ

## ኢየሱስ ክርስቶስ መልአክ ነውን?

**ጥያቄ** 1. በገላትያ 4÷14 ላይ «ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር መልአክ አዎን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተቀበላችሁን» ይላል:: ምን ማለቱ እንደሆነ አልገባኝ ምና አብ ራሩልኝ:: ኢየሱስ ክርስቶስ መልአክ ነው ለማለት ፈልጐ ነው:: ይህን የተናገረው ብለው የተከራከሩኝ አሉና::

*መምህር አንተነህ ብርሃኑ*
*ከኤፍራታ*

<u>መልስ</u> ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከጻ ፋቸው 14 መልእክታት ውስጥ ለገላ ትያ ሰዎች የጻፈው አንዱ ነው:: ይህ ንን መልእክት በሮም ታስሮ በነበረበት ጊዜ እንደጻፈው ይነገራል:: በመጀመ ሪያ ጊዜ በገላትያ ተገኝቶ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ አምላክነት ያስተማረና ወንጌልን የሰበከ ቅዱስ ጳው ሎስ ነው:: ነገር ግን የገላትያ ሰዎች እርሱ እንዳስተማራቸው ጸንተው አልተ ገኙም:: በሐሰተኛ መምህራን ትምህርት ተወስደው ከጽናታቸው ወደ ኋላ ብለው ነበር «ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር መልአክ አዎን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተቀበላችሁን» አላቸው:: የዚህን አነ ጋገር መልእክት በሚገባ ልንረዳው ይገባናል:: ይህንንም ለመረዳት መል አክ የሚለውን ትርጉም ማወቅ ያስፈ ልጋል:: መልአክ ቃሉ የግእዝ ሲሆን ትርጉሙ መልእክተኛ፣ አለቃ ማለት ነው:: ቃሉ ለሰውም ለመላእክትም በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶ እናገኘዋለን:: በገላ.4÷14 ላይ «ነገር ግን እንደ እግዚ አብሔር መልአክ አዎን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተቀበላችሁኝ ማለቱ እኔን እንደ እግዚአብሔር መልእክተኛ አድር ጋችሁ ተቀብላችሁኝ አልነበረም ወይ? ለማለት ነው:: ይህንንም ሲገልጥ «አዎ ን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ብሏል::» ነገሩን እንዲረዱት የገለጠበት መንገድ ነበር:: ድንግል ማርያም ቅዱስ ገብር ኤል ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን ዐውቃ እንደተቀበለችው ምእመናንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ አብ ከባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ እነ ርሱን ለማዳን የተላከ አምላክ ወልደ አምላክ ብለው እንዳመኑበት እንደ ተቀበሉት እናንተም እኔን የእርሱ መልእተኛ መሆኔን ዐውቃችሁ ተቀብ ላችሁኝ አልነበረም ለማለት ነው:: ምክ ንያቱም እኔን የእግዚአብሔር መልእ ክተኛ (መልአክ) አድርጋችሁ ከተቀበላ ችሁኝ ለምን በሐሰተኛ መምህራን ትወሰዳላችሁ? ትታለላላችሁ? ቀድሞ በመልካም የተመላለሳች ሁበትን ሕይ ወት አስቡ ሊላቸው ፈልጐ ነው::ጠ ያቂያችን እንደተከራከሩዎት ዓይነት ሰዎች ይህንን አነጋገር ኢየሱስ ክርስቶስ መልአክ መሆኑን (እንደ ቅዱስ ገብ ርኤል) ለመግለጥ ነው በማለት ክህደት የሚናገሩ አይጠፉም:: ይህ ዓይነት አመለካከት የልቡና ፍልስፍና እንጂ ከእግዚአብሔር ቃል የተገኘ አይደ ለም:: ኢየሱስ ክርስቶስ የመላእክት ፈጣሪ እንጂ መልአክ አይደለም:: ኢየ ሱስ ክርስቶስ ሁሉን በፈቃዱ የሚገዛ የሚሳነው ነገር የሌለ የባሕርይ አምላክ ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ የከበረ እንጂ መልአክ አይደለም::

በዚህ በገላትያ መልእክት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ቦታዎች መልአክ የሚለው ቃል እንደ አገባቡ የተለያየ ትርጉም እንዳዘለ ለመረዳት እንዲቻል ለጠያቂያችንም መልአክ የሚለው ቃል ትርጉም አንድ ብቻ እንዳልሆነ ለማሳ የት ተጨማሪ ቦታዎችን አንሥተን እን መልከት::

መልአክ ማለት መልእክ ተኛ ነው ከሚለው ተጨማሪ አለቃ ማለትም እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን:: ለዚህም ለመነሻ ያህል ዮሐ.3÷1 ላይ ያለውን የግእዝና የአማርኛ አገላለጽ እንመልከት:: «ወሀሎ አሐዱ ብእሲ እምፈሪሳ ያን ዘስሙ ኒቆዲሞስ መል አኮሙ ለአይሁድ» የሚለው በአማርኛ ሲገለጥ «ከፈሪሳውያን ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበር» ይላል:: መልአክ ማለት አለቃ ማለት ስለሆነ ትርጉሙን ተክ ቶታል:: እዚህ ላይ ማስተዋል የሚ ያስፈልገን የቃላቱን ትርጉም ለመ ረዳት ግእዝ ቋንቋ ማወቅ ያለውን ጠ ቀሜታ ነው::

ቅዱስ ዮሐንስ ባየው ራእይ ላይ እግዚአብሔር አምላክ ሲነግረው «በቀኝ እጄ ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብ ትና የሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ምስጢ ር ይህ ነው:: ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አቢያተ ክርስቲያናት መላእክት ና ቸው:: ሰባቱም መቅረዞች ሰባቱ አብ ያተ ቤተክርስቲያናት ናቸው ብሎ ታል (ራእይ. 1÷20):: ከዚህ በተጨማሪ ራእይ 2÷1, 2÷8, 2÷12, 2÷18, 3÷1,7,4 ላይ መልአክ የሚለውን ቃል የሚያ መለክ ተው የቤተክርስቲያን አለቃ አስተዳዳሪ ማለት ነው:: ዛሬም ቢሆን በቤተክርስቲያን አለቅነት /አስተ ዳዳሪነት/ ያሉት አባቶች መልአክ ተብለው ይጠራሉ:: ምሳሌ መልአከ ገነት፣ መልአከ ታቦርመልአክ የሚለ ውን ቃል ትርጉም መረዳት ካልቻልን ከተጠቀሰው ገላ.4÷14 ተጨማሪ መልእ ክታቸውን ለመረዳት የሚያስቸግሩን ቦታዎች አሉ:: ምሳሌ ቆላ.2÷ 16–18 «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረ ድባችሁ:: እነዚህ ሊመጡ ላሉ ነገሮች ጥላ ናቸውና አካሉ ግን ክርስቶስ ነው:: ትኅትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወ ደደ ባለው ያለፈቃድ እየገባ በሥጋዊ አእምሮም በከንቱ እየታበየ ማንም አይ ፍረድባችሁ» ይላል::

እዚህ ላይ ቅዱስ ጳውሎስ ማስ ተላለፍ የፈለገው መልእክት እንደሚ ከተለው ይብራራል:: የቆላስ ይስ ሰዎችን ያስተማረው የቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙር ኤጳፍርስ ነው:: በተማ ሩበትም ትምህርት ፀን ተው በመገኘት አርአያ ነበሩ:: በሐ ሰተኛ መምህራን ምክንያት ወደ ክርስትና የመጡትን ጫና ያደርጉባቸው ስለነበርና ጥምቀት ያለ ግርዘት፣ ወንጌል ያለ ኦሪት አያድ ንም ይሏቸው ስለነበር እነዚህ ሰዎች በትዕ ቢት እየቀረቡ እንዳያስጨን ቋቸው እነርሱም የቀረ ነገር ያለ እንዳ ይመስላቸው ለማሳሰብ ነው:: በእር ግጥም ደጋግ አባቶችን በማን ሣት ለሃ ይማኖት ቀናዒነት ያላቸው በመምሰል እግዚአብሔር ለአባቶ ቻችን የሰጠው እንዴት ይቀራል በማለት በግብዝነት ቀርበው ይናገሩ ስለነበር ለመውቀስ ሲል የአለቆቻ ቸውንና የአባቶቻቸውን ሕይወት ለማንሣት «የመላእክትን አም ልኮ» ብሎ ተናገረው:: የአባቶቻቸ ውንና የአለቆቻቸውን (የመላእክትን) አምልኮ የወደዱ፣ በእነርሱ መንገድ የተ ጓዙ መስለው ስለሚቀርቡ፤ ነገር ግን የክርስትና ሕይወት ትርጉሙ ባልገ ባቸው ሰዎች እንዳትናወጹ ለማለት ነው:: ለምሳሌ ያህል እግ ዚአብሔር ለአብርሃም ግርዘትን ሲሰጥ አብርሃም የግርዘት ቃልኪዳን ምን እንደሆነ እንደ ተረዳው እነርሱ ሳይረዱ የአብ ርሃም ዘር ነን በማለት ብቻ የአብርሃምን ሃይ ማኖት የተከተሉ በመምሰል ለምን ግርዘት ይቀራል? ለምን በጥምቀ ትስ ይተካል? ይሉ ነበርና:: ስለዚህ በዚህ ቦታ መላእክት ማለት አለቃ ማለት ነው::

## የትኛው ኃጢአት ነው?

***ጥያቄ 2*** ሰለስቱ ምዕት (318ቱ ሊቃውንት) ኃጢአት በሚሰረይባት አንዲት ጥምቀት እናምናለን ብለ ዋል:: ስመሆኑ የሚያስተሰርየው የትኛ ውን ኃጢአት ነው? በተለይ ደግ ሞ ስህጻናት የዘር ኃጢአት ነው ቢሉ በክርስቶስ ተደምስሶ የለም ወይ?

*ማለደ ዋስይሁን/ደ/ብርሃን*
*ቅ/ሥ/ስ/ት/ቤት/*

<u>***መልስ***</u> የአርዮስን የክህደት ትምህ ርት ለማውገዝ በ325 ዓ.ም አካባቢ ኒ ቂያ በተባለች ቦታ የተሰበሰቡት 318ቱ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን «ኃጢአት በሚሰረይባት በአንዲት ጥምቀት እና ምናለን» በማለት የሃይማኖት መሰረት

የሆነውን ገልፀዋል:: ይህንን የሊቃውንቱን አቋም ለመረዳት ዘመኑንም መመርመር ያስፈልጋል:: ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም የማይደገም የቤተክርስቲያን ምስጢር ነው:: አንባቢያችን እንደገለጡት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ ተቀብሎ ሞታችንን ሞቶ ከቀደመ በደልና ኃጢአት ነጻ እንጻ ወጣን እናምናለን:: ይህንንም ስንል አዳምና ሔዋን በፈፀሙት በደል ለሁሉም ሰው ደርሶ የነበረው የውርስ ኃጢአት ማንም ተጠያቂ እንዳይሆን ሁሉንም የሰው ዘር ነጻ አውጥቷል:: እዚህ ላይ ታዲያ መጠመቅ ለምን እንደሚያስፈልግና በጥምቀት የሚገኝ ስርየተ ኃጢአት ስለመኖሩ ልንገነዘብ ያስፈልገናል::

ጥምቀት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰረተ በካህናት አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈፀም ምስጢር ሲሆን፣ ዳግመኛ በመወለድ የጸጋ ልጅነትን የምናገኝበት ብቸኛ መንገድ ነው:: ጌታችንም ሲያስተምር እንደተናገረው «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ዮሐ.3÷4:: ልጅነትን ካላገኙ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት ስለማይቻል ጥምቀት የምንድንበት መንገድ ነው:: ቅድስት ቤተክርስቲያን ባስቀመጠችው ሥርዓት መሰረት ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀን፣ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ የመንፈስ ቅዱስ ልጅነትን ለማግኘት ሊጠመቁ ይገባቸዋል:: «ሕጻናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው» ተብሏልና:: በአሁኑ ጊዜ ክርስቲያን ምእመናን በሙሉ የሚመሩት በዚህ የቤተክርስቲያን ሕግ ስለሆነ ጥምቀት ለሕጻናቱ ልጅነትን እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል እንጂ ስርየት የሚያስፈልገው በሕጻናቱ የተፈጸመ ኃጢአት ስለሌለ ሕጻናቱ ስርየተ-ኃጢአት በጥምቀት አገኙ አንልም የቀደመው የውርስ ኃጢአት ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ የማዳን ሥራ ቀርቷልና:: ነገር ግን 318ቱ ሊቃውንት ይህንን አቋም በሚ ያስተላልፉበት ሰዓት ብዙዎቹ ካደጉ በኋላ ከአረማዊነት ወደ ክርስትና ከአይሁድነት ወደ ክርስትና ይመጡ ስለነ በረምንም እንኳ ጥምቀት ልጅነትን የሚያገኙበትን መንገድ ቢሆን በተጨማሪም ካደጉ ካወቁ በኋላ ለሠሩት ኃጢአት ስርየት የመስጠት የመደምሰስ ኃይል ጥምቀት እንዳላትም ለመናገር የጠቀሱት ነው:: አባቶቻችን ሐዋርያት በሚያ ስተምሩበት ጊዜ ምንም እንኳን የውርስ ኃጢአት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቢቀርም ካደጉ ካወቁ በኋላ ስለ ሠሩት ኃጢአት ስርየት እንዲያገኙ መጠመቅ እንዳለባቸው ለእስራኤላውያን ተናግረዋል::

«ንስሃ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ»ሐዋ.2÷38::

ሳውል ክርስቲያኖችን ከማሳደድ ግብሩ አምላካችን በቸርነቱ ሲመልሰው ወደ ሐናንያ የተላከበት ምክንያት በጥምቀት ልጅነትንና ስርየተ-ኃጢያትን እንዲያገኝ ነበር:: ምክንያቱም ካደገ በኋላ የሠራው ኃጢአት ነበርና፣ «አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ»ሐዋ.22÷17::

አንድ ጊዜ ተጠምቆ ልጅነትን ካገኘ በኋላ ሰው ኃጢአት ቢሠራ ስርየት የሚያገኘው ንስሐ በመግባት እንደሆነ ልናስተውለው ይገባናል:: ስለዚህ ጥምቀት ልጅነትን በ40 ቀን በ80 ቀን ለሚጠመቁ፣ ልጅነትንና ስርየተ-ኃጢአትን ደግሞ ካደጉ በኋላ ካወቁ ለሚጠመቁ ትሰጣለች ብለን እናምናለን::

## ረቡዕና ዓርብ የፍስክ... ?

*ጥያቄ3.* ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ በዓል በኋላ ያሉትን 50 ቀናት አይጾምም ቀኖናም (ንስሐም) አይሰጥም ይባላል ምክንያቱ አልገባኝምና አብራሩልኝ? (በተለይ ረቡዕና አርብ የፍስግ ምግብ መብላት እየከበደኝ ነው?)

*ዲ. ሰውነት ታዬ*
*ሰሜን ሸዋ*

*መልስ* በእርግጥም በቤተክርስቲያን ቀኖና መሰረት በበዓለ ኃምሳ አይጾምም:: ንስሐም አይሰጥም (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 19÷739) በሌሎች ጊዜያት የምናስባቸው ቀናት ረቡዕና ዐርብን ጭምር አይጾምም:: ቀኖና ስንል ሥርዓት፣ ፍርድ ቅጣት ማለታችን ሲሆን፣ የቤተክርስቲያን ቀኖና ማለት ደግሞ ቤተክርስቲያን የምትመራበት ሥርዓት አባቶቻችን ካህናት በእግዚአብሔር ቸርነት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ያስቀመጡት ሥርዓት ስለሆነ ይህንን ሥርዓት መተላለፍ ሥልጣነ ክህነትን አለማክበር በመሆኑ ውግዘት የሚያመጣ ነው::

በእነዚህ 50 ቀናት የማይጾምበት ንስሐ የማይገባበት ምክንያት ስለትንሣኤ በዓል ክብር ሲባል ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ (በሞቱ ሞታችንን አጥፍቷልና) ከዚያ በኋላ ያሉት 50 ቀናት የእርሱ ትንሣኤ የሚነገርባቸው ቀናት ስለሆኑ ቤተክርስቲያን ለ50 ቀናት በቅዳሴ ሰዓት የምታነበው ምንባብ፣ የምትሰብከው ምስባክ አንድ መሆኑ እንደ እለተ እሑድ (ትንሣኤው ቀን) ሌሎቹ ቀናት የሚከበሩ በመሆናቸው ነው:: በአምላካቸው መከራ መቀበል አዝነው የነበሩት ሐዋርያት በትንሣኤው ፍጹም ደስታን እንዳገኙ ሁሉ፣ ዛሬም ያለነው ክርስቲያኖች መከራውን አስበን የጾሙን ወራት የምናሳልፈው ትንሣኤውን አስበን በፍጹም ደስታ ደስ እንሰኛለን:: ይህ ትንሣኤ ለእኛ አርነት መውጣታችንን የምናስብበት ቀን ነውና:: ስለዚህ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተደረገልን የማዳን ሥራ ትንሣኤያችንን በእርሱ ትንሣኤ አይተናልና በእነዚህ ቀናት ለእኛ ትልቅ ክብር ያገኘንበትን አስበን ለቀናቱ ክብር ሰጥተን በማክበራችን የምናገኘው በረከት ትልቅ ነው::

በዚህን ጊዜ ረቡዕና ዐርብንም ቢሆን አንጾምም:: ምክንያቱም በእነዚህ ቀናት በሌላ ጊዜ የምንጾመው መከራውን ለማሰብ፣ እንጂ ቀናቱ በራሳቸው የተለዩ ስለሆኑ አይደለም:: በእነዚህ 50 ቀናት ደግሞ መከራ አልፎ ደስታ ስለተተካ ሞት ድል ተነስቶ ትንሣኤን ስላየን በእነዚህ ቀናትም ጭምር ትንሣኤውን ስለምናስብ ነው::

ንስሐም በእነዚህ ቀናት አይሰጥም:: ምክንያቱም በዓሉን ከምናከብርበት ምክንያት ጋር አብሮ ስለማይሄድ ነው:: ትንሣኤን ስናከብር ነጻነታችንንም ማሰባችን ነው፣ ከሰይጣን ባርነት ተላቀን በእግዚአብሔር ቤት መኖራችንን የምንዘክርበት ጊዜ ነው:: በኋላም በፍጻሜ ዓለም ከአምላካችን ጋር በፍጹም ደስታ እንደምንኖር የምናስብበት ጊዜ ነው:: /ራዕይ.7÷13-17/:: ንስሐ ማለት ደግሞ የሠሩትን ኃጢአት ማሰቢያ ጊዜ ነው:: በእነዚህ ቀናት እኛ የራሳችንን ኃጢአት አስበን በኀዘን መገኘት የማይገባን የትንሣኤው ክብርም ስለሚበልጥብን ነው:: እንዲሁም እኛ በመጾማችን ከምናገኘው ጸጋና ክብር ይልቅ በትንሣኤው ያገኘነው ይበልጣልና ነው:: እዚህ ላይ መጾምና ማዘን በ50 ቀናት ውስጥ አይፈጸምም አልን እንጂ ሥርዓት ወጥተን ከኃጢአት ሥራ ጋር እንተባበራለን ማለታችን አይደለም:: ጾምና ንስሐ ስለሌለ የፈለግነውን ሁሉ ማድረግ እንችላለን ማለታችንም አይደለም:: እንደውም የበለጠ ትንሣኤያችንን በማሰብ ከኃጢአት ሥራ ሁሉ ፈጽመን የምንርቅበት ጊዜ ነው:: ከዕለተ ምጽዓት በኋላ ያለውን ሕይወታችንን የምናስብበት፣ ኀዘን ከእኛ ርቆ በፍጹም ደስታ የምንገኝበት በመሆኑ በእነዚህ ጊዜያት ከመቼውም የበለጠ ኃጢአት በእኛ ላይ ቦታ ሊኖረው አይገባም::

# እናስተዋውቃችሁ

## አባ ዮሐንስ

/ዘደብረ ቢዘን/

በመንፈሳዊ ህይወታቸው የጠነከሩ በሃይማኖታቸው የጸኑ፣ የተቸገረውን በመደገፍ፣ በትህትናቸው፣ በደግነታቸውና በመልካም ምግባራቸው በአካባቢያቸው የታወቁና የተከበሩ እጅግ ባለጠጐች ነበሩ:: እኒህ ቅዱሳን ባልና ሚስት ገብረ ክርስቶስና አክሮስያ ይባላሉ:: በኤርትራ ውስጥ በአካለ ጉዛይ አውራጃ በደቀመሐሪ ከተማ ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ በምትገኘው ልዩ ስምዋ ዓዲ ኢሕስአ በመባል በምትታወቀው ቀበሌ ይኖሩ ነበር::

እኒህ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያልተለያቸው ቅዱሳን ኑሮአቸው የተሟላ መልካም ምግባራቸውም የታወቀ ቢሆንም ልጅ አልነበራቸውም:: ይኸንኑ ችግራቸውንም ለእግዚአብሔር ከማሳሰብ አላቋረጡም:: በዚህ መሠረት በጾምና በጸሎት ተወስነው ወደ እግዚአብሔር ሲያመለክቱና በቅን ልቡና ሲያገለግሉ ቆዩ::

«ቅሩብ እግዚአብሔር ለየዋሃነ ልብ» ብሎ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት እንደተናገረው ያቀረቡትን ጸሎት ሰምቶ ልመናቸውን ተቀብሎና ኃዘናቸውን ተመልክቶ ዕንባቸውን ከዓይናቸው አበሰላቸው:: የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ሆኖ መልካም ልጅ ወለዱ::

ይህ ደግ ልጅ ከአቡነ ፊሊጶስ ቀጥሎ የደብረ ቢዘንን ገዳም ሲያስተዳድር የነበረው ታላቅ ጻድቅ አቡነ ዮሐንስ ነው::

አቡነ ዮሐንስ በተወለደ በአርባ ቀኑ ጥምቀተ ክርስትናን ለማሥነሣትና የሥላሴን ልጅነት ለማስጠት እናትና አባት ወደ ቤተክርስቲያን ወሰዱት:: በዚህን ጊዜ ዘካርያስና ቅድስት ኤልሳቤጥ ልጅ አጥተው ኖረው ከሸመገሉ በኋላ ያገኙትን ልጅ ዮሐንስ ብለው እንደሰየሙት ሁሉ ገብረ ክርስቶስና አክሮስያ ያገኙትንም ልጅ ካህናቱ ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ዮሐንስ ብለው ሰየሙት::

ዮሐንስ ማለት ፍሥሐ ወሐሴት ፍቅር ወሰላም ማለት ነውና::

ጻድቁ አቡነ ዮሐንስ ከሚታወቁባቸው ታላላቅ ሥራዎች አንዱ ሕፃን ሳሉ ዐርብና ረቡዕ እንዲሁም ሌሎች አጽዋማት በሚሆኑበት ወቅት ከዘጠኝ ሰዓት በፊት በጭራሽ የእናታቸውን ጡት አለመጥባታቸው ነው:: የሕፃኑ ዮሐንስ እናት



አክሮስያ ግን በልጃቸው ጡት አለመጥባት እጅግ እየተጨነቁ ያዝኑና ያለቅሱ ነበር:: ማዘናቸውና ማልቀሳቸውም ልጄ ሕመም ቢያገኘው ነው እንጂ ያለ አንዳች ምክንያት አልጠባም ባላለኝ በሚል ሐሳብ ነበር::

አቡነ ዮሐንስ ግን ከዘጠኝ ሰዓት በፊት የእናታቸውን ጡት አለመጥባታቸው ስለ ክብረ ጾም ነበር እንጂ የሕመም አልነበረም::

አቡነ ዮሐንስ በዕድሜያቸው እያደጉ በአካላቸውም እየጠነከሩ ትንሽ ከፍ ካሉ በኋላ የወላጆቻቸውን በጐች በመጠበቅ እረኝነት ጀመሩ:: በጐቻቸውን ይዘው ከእረኞች ጋር በሚውሉበት አካባቢ ማይ በለስ የሚባል ወንዝ አለ:: አቡነ ዮሐንስ በጎቻቸውን ውኃ ለማጠጣት ወደዚያው በሚሄዱበት ጊዜ እረኞቹ በውኃ እየተራጩ ሲጫወቱ እሳቸው ግን ለብቻቸው ለየት ብለው ሲሰግዱና ጸሎታቸውን ለማድረስ ቆመው ይውሉ ነበር::

እረኞቹም ሥራቸውንና አካሄዳቸውን እየተመለከቱ «ለምን ከእኛ ጋር አትጫወትም? እስከመቼ ድረስ ብቻህን ትኖራለህ?» ይሉዋቸው ነበር::

አቡነ ዮሐንስም «አነ እከውን መነኮስ እኔ መነኩሴ እሆናለሁ:: ይህ ዓለምም እንደሆነ የታየው ሲሄድ ያልታየውም ሲመጣ ይኖራል እንጂ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የኖረ ሰው አናገኝም:: እኔም ብሆን ይህንን በማበየቴ ምንኩስናን መርጬአለሁ::» እያሉ በዘዴ ያስተምሩ እንደነበር ገድላቸው ያስረዳል::

በመጨረሻው ግን ወላጆቻቸውን ሳይሰናበቱ ወደ ደብረ ቢዘን ገዳም ለመሄድ አሰቡ:: አሰበውም አልቀሩ ለማንም ሳይናገሩ ከማንም ጋር ሳይማከሩ ወደ አሰቡት ገዳም መንገዳቸውን ቀጠሉ::

አቡነ ዮሐንስ ከቤታቸው ሲጠፉ በመንደሩም ተፈልገው ሲታጡ ወደ ደብረ ቢዘን ለመሄድ ሃሳብ እንደነበራቸው ዘመዶቻቸው ሁሉ ያውቁ ነበርና «ወደ ገዳም ሄዶ ነው::» በማለት ዘመዶቻቸው ተከተሏቸው:: ከገዳሙ ሣይገቡም ከመንገድ ደረሱባቸው::

አቡነ ዮሐንስ አሻግረው አይተው ዘመዶቻቸው መሆናቸውን ከተረዱ በኋላ «አቤቱ ጌታዬ ሆይ ከዓይና ቸው ሠውረኝ:: ይዘው እንዳይመ ልሱኝም አንተ ጠብቀኝ::» ሲሉ ጸ ሎት አደረጉ:: ጸሎታቸውን እንደ ጨረሱም ዘመዶቻቸው እርሳቸው ካሉበት ቦታ ሲደርሱ ተሰወሩባቸ ውና አልፈዋቸው ሄዱ:: ከገዳሙ ውስጥም ገብተው አቡነ ዮሐንስ እን ደሌሉ ካረጋገጡ በኋላ ወደ አገሩ /ወደ ገጽ 20 ይዞራል/

# ከደብረ ብርሃን ሥላሴ እስከ ሕዝብናኝ ቤተመንግሥት

የዚህ ቦታ ምሥጢር ምሥጢረ ምጽአት ነው፡፡ ሰው አላወቀውም፡፡
አባ ዘውገ ማርያም የገደሙ አበምኔት

ዲ.ዳንኤል ክብረት ና
ሲ/ር ትዕግሥት ከበደ

/ክፍል 2/

እንደምን ሰነበታችሁ?

አሁን ወደ ደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ፡፡ ረገረገርም ዛፎቹ፣ ጥንታዊው አጥር፡፡ ጸጥ ረጭ ያለው መንደር፡፡

እነሆ ዜና ማርቆስ፡፡

በአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የተገደመ ጥንታዊና ታሪካዊ ገዳም፣ አባታችን አቡነ ዜና ማርቆስ ከቆሙ ሳይቀመጡ 40 ዓመት የጸለዩበት ታላቅ ገዳም፡፡

ከታላቁ ተራራ ሥር ይገኛል፡፡ ዛፎቹም ረገረገርምና ወፋፍራሞች ናቸዉ፡፡ ከአዕዋፍ ዝማሬና ከተራራው መንደር ከሚመጣው የከብቶች ጩኸት በየቋጥኙ ተቀምጠ ዜማውንና የቃል ጥናቱን ከሚያንቆረቁረው የቆሎ ተማሪ ድምፅ በስተቀር ሌላ አይሰማበትም፡፡ ጸጥ ረጭ ያለ ሕይወት በደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ገዳም፡፡

ቤተክርስቲያኑን ያሠሩት አጼ ኃይለሥላሴ ናቸው፡፡ የመርከብ ቅርጽ ያለው በጥርብ ድንጋይ የተሠራ የአዲስ አበባውን ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን የመሰለ ሕንፃ ቤተክርስቲያን ነው፡፡

ቤተክርስቲያኑ ሙሉ ጥገና ተደርጎለት ስለማያውቅ አልፎ አልፎ ያፈሳል፡፡ የወለሉ ቅዝቃዜ ለጉድ ነው፡፡ ለሳንቲካ ከተነጠፉት ጥቂት ምንጣፎች በቀር ዓይን የሚያርፈው ወለሉ ላይ ነው፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ያንን የመሰለ ሕንፃ ቤተክርስቲያን በጥንታውያን ሥዕሎች አለመሞላቱን ማርጻታችን ነው፡፡

አጥሩ የድንጋይ ካብ ነው፡፡ አጥሩን ያየ ሰው ግን አጥሩ በሕዝቡ ላይ ያደረው ፈሪሃ እግዚአብሔር መሆኑን ይረዳል፡፡ ጥንት አጥሩ እዚህ ላይ ነበር ለማለት ካልሆነ በቀር የተከመረው ድንጋይ ወይ ወደ ፊት አለያም ወደ ኋላ እንደ ሦስተኛ ክፍል ተማሪ በሰልፍ ተቀምጧል፡፡ ወጭ ገቢውም ከበሩ ይልቅ የሚጠቀመው በሰልፈኛው ድንጋይ ላይ በመንጠልጠል ነው፡፡

የአዛውንቶቹ ዛፎች ግርማ ሞገስ ግን «ባለህበት ቁም!» በማለት አጥሩን ያስጠብቃል፡፡

**ዕድሜያቸው 100 ነው፡፡ በዚህ ቦታ 40 ዓመት ተቀምጠዋል፡፡ እማሆይ ሐረገ ወይን ፤፤ ከአልጋ አይወርዱም፡፡ አባ ዘውገ ብቅ ሲሉ ግን «አልጋ ላይ ሆኜ መስቀል አልሳለምም» በማለት መሬት ካልወረድኩ ብለው በመከራ ነው ያስቀረናቸው፡፡ ወይ የሃይማኖት ጽናት?**

ስለ አዛውንቶቹ ዛፎችና አቋቋማቸው ስናነሳ የቋጥኝ ድንጋዮችንም በማከል የሰማነውንና የታሪኩን እውነትነት በዓይናችን ዐይተን እንድናረጋግጥ ያደረገንን አንድ ታሪክ እናካፍላችሁ፡፡

አቡነ ተክለ ሃይማኖትና አቡነ ዜና ማርቆስ በሥጋም ይዛመዳሉ ፡፡ሁለቱ ቅዱሳን አባቶች በዚች ቦታ ተቀምጠው ሲጸልዩና እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ቆይተው አቡነ ተ/ሃይማኖት ወደ ደብረ ሊባኖስ ለመሄድ ይነሳሉ፡፡ ምንም እንኳን አቡነ ዜና ማርቆስ «ወንድሜ ሆይ እኔን ብቻዬን ትተኸኝ ትሄዳለህን?» ቢሏቸውም በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም እንደሚገባ ተስማምተው አቡነ ተክለ ሃይማኖት አቡነ ዜና ማርቆስን ተሰናብተው መንገድ ሲጀምሩ የገዳሙ አፀደ የነበሩት ዛፎችና የድንጋይ ቋጥኞች ተከትለዋቸው መሄድ ይጀምራሉ ፡፡ በዚህ ጊዜ አቡነ ተክለሃይማኖት ወደ ወንድሜ ተመለሱ እንጂ እኔን አትከተሉኝ በማለት ይገዝቷቸዋል፡፡ ቋጥኞቹና ዛፎቹም በያሉበት ቆመዋል፡፡ዛሬም ቢሆን ንጉሡን የሚያጅብ ሠራዊት መስለው ከገዳሙ በስተሰሜን ይታያሉ፡፡

ወደ ተራራው ግርጌ ስንጠጋ ጥንታዊቱን የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን አገኘናት፡፡

ጣራዋ ግማሹ ዐለት ግማሹ ቆርቆሮ ነው፡፡ ሕንፃ ቤተክርስቲያኑ የቅርብ ዘመን ቢሆንም ትክሏ ግን የጥንት ነው፡፡ አባታችን ዜና ማርቆስ ተጋድሏቸውን የፈጸሙት ከዚህ ቦታ ነው፡፡

በሩ ተከፈተ

ከመቅደሱ ጀርባ ከዐለቱ ሥር ፈዋሹ ጠበል ጠብ ጠብ ይላል፡፡ ብፁዕ አባታችን ዜና ማርቆስ በዓለ ጥምቀትን በዓመት በዓመት ወደ ሀገረ እሥራኤል እየተሻገሩ ያከብሩ ነበር፡፡ ታዲያ አባታችን ውኃውን ከዮርዳኖስ በንሥር

አምጥተው በዚያ ቦታ አፍስሰው ባርከዋታል። ገድላቸው ያመጡትን ውኃ ከልሙጥ ዐለት ላይ አፍስሰው ፀበሏን እንዳፈለቁ ይተርክልናል። ከዓመት እስከ ዓመት ጠብ ጠብ በማለት ብቻ በምትፈሰው በዚች ጠበል አባታችን 8,000 ሕዝብ እንዳጠመቁ ገድላቸው ይመሰክራል። አባታችን በዚህ የተጠመቀ ጥምቀቱ በዮሐንስ እጅ እንደሆነ ይቆጠርለታል የሚል ቃል ኪዳን ተሰጥቷቸዋል።

የቅዱስ አባታችን ዐጽም ያረፈውም በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው።በሩ፡ተዘጋ።ፊት ለፊት እንደ አክርማ የተሠነጠቀ ገደል።

ብፁዕ አባታችን አቡነ ዜና ማርቆስና አቡነ ተክለሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደዚህች ገዳም መጡ። በተራራው ላይ ጸሎት እያደረሱ ሳለ በአካባቢው የሚገኙት አረማውያን ርስታችንን ሊቀሙ ነው ብለው ስለፈሩ ጦራቸውን ሰብቀው ሠይፋቸውን ታጥቀው ነቅለው ወጡ።

ቅዱሳን አባቶቻችን ዐለቱን ባረኩት። ከሁለት ተሠነጠቀና ከዐላውያን ከአረማውያን ሠወራቸው። ውስጥ ለውስጥ ወደ 30 ደቂቃ ያህል ያስኬዳል። አጣብቂኙ።

አንድ ጊዜ አንድ የአካባቢው «ጉልበታም» ሰው ገድሎ ከበዓል አክባሪዎች ጋር ተቀላቀለ። ሰላማዊ ለመምሰል። ምእመናኑ ወደ አጣብቂኙ በዕልልታ በዝማሬ ሲመጡ ተከትሎ መጣ ። «ሰው መሳይ በሸንጎ» ሆነና አጣብቂኝ ውስጥ ገባ። ደግሞ የድፍረቱ ድፍረት ከነመግረያው። መሐል አጣብቂኙ ላይ ሲደርሱ ሰውየውን ትቶ መግረያውን ያዘው። ላበት በላበት። ጭንቀት በጭንቀት። ወደኋት ያምልጥ። ከፊትም ከኋላም የሰው «መንጋ» አለ። ታወቀበት። ተያዘ። ተናዘዘ። እንዲህ ነው ተአምሩ አሉን አባ ዘውገ ማርያም-አበምኔቱ።

ወደ ገዳማውያኑ ኑሮ ስንዝልቅ።

አብዛኛዎቹ በዕድሜ ደካማዎች ናቸው። ረኸርም ሰፊ መኖርያ አዳራሽ አላቸው። ከአጠገቡ መስቀል ቤቱ ይገኛል። እንደ ቤቱን ጉሥ ጉብ ብሎ። ሴት አይገባም አሉን አባ። የብፁዕ አባታችን ገድልና የባረኩበት መስቀል የሚገኘው እዚህ ነው። ገድላቸው ዘወትር ይነበባል- ሰሚው ጥቂት ነው እንጂ።

ሳፊው ቤት ተከፋፍሏል ለየመነኮሳቱ። በቀን አንድ ጊዜ ድርጎ ይሰጣቸዋል። ከተገኘ። ከ110 ዓመት በታች ባለዕድሜ አታገኙም። ለብፁዕ አባታችን አባ ዜና ማርቆስ ከተሰጣቸው ቃል ኪዳን መካከል አንዱ በበአትህ የኖረውን ዕድሜ ሳይጠግብ አልወስደውም የሚል በመሆኑ ከ120-140 ዓመት መኖር ለዚያ ገዳም መናንያን ብርቅ አይደለም።

አባ ዘውገና አባ ሠይፉ እየመሩን ሲ/ር ትዕግሥትና ዲ/ዳን ኤል እየተከተልን። ዘለቅን። ወደ ሴቶቹ መኖርያ። ግብር ቤቱ ሰፊ ነው። ዳሩ ግን «ጠብ ሲል ስደ ፍን...ጠብ ሲል ስደፍን... ይኼ ነገር ቆርቆሮ ነው ስሌን» ያለችው ሴትዮ ያላየችውን ቆርቆሮ ለብሷል።

መነኮሳይያቱ ከሚለፉ የሚነፋውን እህል ጣራ ላይ ቢያደርጉት ምርትና ግርዱን ራሱ ሳይለየው አይቀርም የቆርቆሮው ወንፊት።

ጾፍ እንደ ጉርፍ እየወረደባቸው ሰማይ ሰማዩን በየቀዳዳው እያዩ ይለፋሉ መነኮሳይያቱ።

ከግብር ቤቱ አለፍ ስንል የመነኮሳይያቱ በኣት ይገኛል። ከተሠራ ከ10 ዓመት በላይ ያለፈው በጽዳቱ ግን ከቦሌ ቤቶች የሚበልጠው የመነኮሳይያቱ ቤት ወጣት፣ ባለሙያና ጠንካራ እናቶች ተጠልለውበታል። ጥቂት ሥልጠናና መግረያ ቢሰጣቸው ገዳሙን ቀጥ አድርገው ይይዙት ነበር።

ተአምር እንንገራችሁ።

ዕድሜያቸው 100 ነው። በዚህ ቦታ 40 ዓመት ተቀምጠዋል። እማሆይ ሐረገ ወይን ። ከአልጋ አይወርዱም። አባ ዘውገ ብቅ ሲሉ ግን «አልጋ ላይ ሆኜ መስቀል አልሳለምም» በማለት መሬት ካልወረድኩ ብለው በመከራ ነው ያስቀረናቸው ወይ የሃይማኖት ጽናት?

የአምስቱን አዕማደ ምሥጢር ትርጓሜ በቃላቸው ሲተነትኑት ለሰማ «አውነት ሃይማኖቴን ተምሬያለሁ?» ያሰኛል።

«እኔ የርሳቸውን ዕድሜ ሳህል ስሜንም ማስታወሴን እንጃ!» አለች ሲ/ር ትዕግሥት-እውነትም። ያ ቢያስደንቀንም በዚህ ዕድሜያቸው በርሃብ አለንጋ እየተገረፉ ወደ ሥጋ ሞት በማዝገም ላይ መሆናቸው አሳዝኖናል።

እንሰናበት፣ ግን ከዚያ በፊት ምንም እንኳን ጠንከር ባለ ሁኔታ ባይሆንም እስከ አሁን ስንለ ው የቆየነውን መልእክት እናስተላልፍ። በጻድቁ ገድል ላይ ተጽፎ እንደሚገኘው መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጢአት በቀራንዮ ያፈሰሰውን ደም ሲረጭ በዚህች ታላቅና «ብዙ ቅዱሳን በሚ ወጡባት» ቦታ ጨመር አድርጐ እንዲረጭ ታዝዞ የረጨባት ቦታ እንደመሆኗ ዛሬ ድረስ ጸሎታቸው ከኢትዮጵያ አልፎ ለዓለም የሚተርፉ ቅዱሳንን ይዛለች። ነገር ግን አበምኔቱ በመግቢያችን ላይ እንዳሉት ምእመናን የቦታውን ታላቅነት ተረድተው የበረከቱ ተካፋዮች የሆኑ አይመስለንም። ብዙ ቅዱሳን ተሰውረው ያሉበት ይህ ታላቅ ቦታ ታላቅ ፈተና ላይ ወድቋል። በጃንሆይ ዘመን የተሠራው ሕንፃ ቤተክርስቲያን ጣራው ወንፊት ሆኗል፣ መነኮሳቱ በረሃብ አለንጋ እየተገረፉ ነው። በዚያው ላይ በኣታቸው በመፈራረሱ ርሃብ ያደከመው ሰውነታቸውን በእንቅልፍ ማሳረፍ የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ምላሻችን ምን ይሆን?

ወደ ፊት የአብነት ት/ቤቱንና የተራራውን ከተማ እናስጎበኛችኋለን።

*ደህና ሁኑልን።*

# አባ ዮሐንስ...

*ከገጽ 18 የዞረ*

ቸው ተመለሱ። አቡነ ዮሐንስም ያለአንዳች ችግር ደብረ ቢዘን ገዳም ገቡ።

የገዳሙ አስተዳዳሪ የነበሩት አቡነ ፊልጶስ የአቡነ ዮሐንስ ወደ ገዳሙ መምጣት በመንፈስ ቅዱስ ተገልፆላቸው ነበር። በክብር ተቀብለው ሲያስተናግዷቸው ከሰነበቱ በኋላ በወጣትነት ለጥቂት ቀናት ሲያገለግሉ ቆዩ።

ይሁን እንጂ አቡነ ፊልጶስ ሽምግለው ስለነበርና የአቡነ ዮሐንስም ደግነት በገዳሙ እየታወቀ ይልቁ ንም ከአቡነ ፊልጶስ በኋላ የገዳሙ አስተዳዳሪ አበምኔት አቡነ ዮሐንስ መሆናቸውን ስለተገነዘቡ በእጃቸው አመንኩሰው ገዳሙን እንዲያስተ ዳድሩ አበምኔት አድርገው ሾሙዋ ቸው።

ሲሾሙዋቸውም የገዳሙን መነኮሳት ሁሉ ሰብስበው «ዘተአዘዘ ለአባ ዮሐንስ ተአዘዞ ለመንፈስ ቅዱስ ወዘዓበዩ ለአባ ዮሐንስ ዓበዩ ለመንፈስ ቅዱስ ለአባ ዮሐንስ የታዘዘ ለመንፈስ ቅዱስ የታዘዘ ነው። ለአባ ዮሐንስ ያልታዘዘ ለመንፈስ ቅዱስ እንዳልታዘዘ ነው።» በማለት አባታዊ መመሪያ ሰጥተው እሳቸው በሰማንያ አራት ዓመት ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

አቡነ ዮሐንስም ከአቡነ ፊልጶስ በኋላ አበምኔት ሆነው ሶስት ሺ መነኮሳት ላይ ተሹመው ሳሉ ብዙ አስደናቂ ሥራዎችን ይሠሩ ነበር።

*ምንጭ ትንሣኤ ቁጥር 98*
*ኅዳር - ታኅሣሥ 1978 ዓ.ም.*

# ከሰይጣን ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ

*ዲ.ዳንኤል ክብረት*

*እንደምን ሰነበታችሁ? ክርስቲያን ለቀጠሮ ትልቅ ቦታን ይሰጣል:: «በዚህ ቀን እንገናኛለን» ወይም «በዚህ ቀን እንዲህ እናደርጋለን» ካለ በያዘው ቀጠሮ ይገናኛል ወይም ያለውን ያደርጋል::: ሰው ነውና ምናልባት እንኳን ባለው ቀን ባይገኝ ወይም ባያደርግና ሌላ ሁለተኛ ቀን ቢቀጥር በዚያ ቀን ያለውን ማድረግ አለበት:: እኛም በገባነው ቃል መሠረት ከ «ሰይጣን ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ» በተለያዩ ምክንያቶች ባለፈው እትም ባናቀርብም በዚህኛው እትም እነሆ ብለናል::*



<u>ጥያቄ</u> *እጅግ በጣም የምትወደው እና ዘወትር የምታንጐራጉረው ዘፈንህ ምን ድን ነው?*
<u>ሰይጣን</u> «አንድ ነገር ሲያምር ያየሁት እንደሆን
ያንን ካላጠፋሁ ከቶ ምንም ቢሆን
ዕንቅልፍ አይወስደኝም ዕረፍት አላገኝም::
ቅን ነገር አይቼ እኔ አያስችለኝም»
የሚለው ነው::

<u>ጥይቄ</u> *ሰዎች ጥቁር ቀንድ ያለህ ፣ ጭራ ንህ ደም የለበሰ፣ጥፍሮችህ ረጅም ነህ ይሉሃል:: በእውነት ጥቁር ነህ?*

*ወንድም ይብዛ ጸጋዬ /መቱ/*

<u>ሰይጣን</u> ማን ነው ያለው ? ጨለማ መገለጫዬ ነው:: ልክ በጨለማ የሚጓዝ ሰው መንገዱን እንደሳተ በእኔ የሚ ሚራ ሰው መንገዱን ይስታል:: በጨ ለማ የሚሄድ ሰው ገደል እንደገባ በእኔ የሚሚራ ም ገደል መሽቀንጠሩ አይቀሬ ነው:: በግብሬ ለሚጭራ ት ከሆነ «ጨ ለማ» የሚለው ይስማማኛል» «በላኤ ሰብ» ብሎ በግብር እንዲጠሩት ትንሽ ትንሽምኮ ትርጓሜ ይነካካኛል:: /ከት አለ :: በእሳተ ገሞራ የሚንፈቀፈቅ ንፍ ሮ ይመስላል::

ከዚህ በተረፈ ጆ! መልኬ እንደ አየሩ ጠባይ ነው:: «ተመሳሰል» በሚለው ጠንካራ መመርያ ተመስሎ ወደ «ጠላት» ወረዳ በመግባት ማጥ ቃት ነው:: እናንተኮ ትገርሙ ኛላችሁ ሁል ጊዜ ጠቁሬ አንደምመጣ ስለም ታስቡ ነው ተቆነጃጅቼ፣ተኳኩዬ ስመጣ የምሸውዳችሁ::

ሶምሶንን ለዚያ ያበቃሁት በቆ ንጆዋ ደሊላ ተመስየ አይደለም:: ጠብ ቁ ሰይጤ ጠቁሮ ይመጣ መስሏችኋ ል::

<u>ጥያቄ</u> *እኛ ሰዎች ተሳስተን ገሃነም ብንገባ ምን ትጠቀማለህ? ለምን አትተወንም?*

*ወለተ ዮሐንስ አ/አ*

<u>ሰይጣን</u> ተባለ እንዴ ? ገሀነም ብቻ ዬን ልሰ ቋይልሽ:: በሲዖል/ገሃነም ብቻን መቀመጥ እንዴት እንደሚያስጠላ ባየ ሽ:: ከዚሁ አሠለጥናችሁና በኋላ አብ ረን እንኖራ ታለን:: ሥልጠና መስጠ ትኮ ነው:: መንግሥተ ሰማያትን ስት ወርሱ እጄን አጠጥፌ እንዳልቀመጥማ የሰይጣንነት አንጀቴ አያስችለውም::

<u>ጥይቄ</u> *አንዳንድ ሰዎች ወዳንተ እስኪመጡ ኃጢአት እስኪሠሩ መከራ ታሳያቸውና የምትፈልገውን ካሠራ ሃቸው በኋላ ርግፍ አድርገህ ትተዋቸ ዋለህ ይባላል:: ለምንድን ነው?*

*የኔነሽ /ጋምቤላ/*

<u>ሰይጣን</u> ሞኝሽን ፈልጊ፤ ከተማረከ ወታ ደር ጋር ሲዋጋ ያየሽው ሠራዊት አለ? በቁጥጥሬ ሥር እስከማውላችሁ አባብላ ለሁ፣እፈትናለሁ፣እምቢ ካላችሁ አስቃ ያለሁ:: በእጄ ከገባችሁ በኋላ ግን ወደ ሌላው ተረኛ አመራ ለሁ::

እስቲ በቤታችሁ አይጥና ድ መት ካሉ ልብ ብለሽ እይልኝ:: ድ መቷ አይጧን እስክትይዝ መከራ ዋን ታያለች:: ከያዘቻት በኋላ ዓይኗን ታወጣና እንደ ኳስ ትጫወትባታለች:: የኔም እንዲሁ ነው:: በሱስ እስክትጠ መጂ ያልሺውን ሁሉ እያቀረብኩ አባ ብልሻለሁ አንዴ ከተጠመድሽ በኋላ ቁራጭ ሲጋራ ፣ቅንጣቢ ጫት፣ጭላጭ መጠጥ አታገኚም ከተማረከ ጋር ማን ይዋጋል::

<u>ጥያቄ</u> *አንተ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን ስትመሰክር ትሰማለህ፤ ታዲያ መናፍቃ አማላጅ ነው እንዲሉ ለምን ታደርጋለህ?*

*መላኩ ንጉሤ /ኢተያ/*

<u>ሰይጣን</u> «አጋንንት ያምናሉ ይንቀጠቀጣሉ» ያለውን አላነበብክም? አውቃለሁ:: አምናለሁ:: በማመኔ ግን አልጠቀምበትም:: እነርሱ ግን አምላክ ወልደ አምላክ ብለው ካመኑ መጽደቃቸው ነው:: ይቺን ፍራ :: ስለማውቀውማ ነው አምነው እንዳይድኑ የማደርጋቸው:: ጐበዝ! ሐሳባችሁ ሁሉ እኔን በገሃነም ብቻዬን ለመተው ነው እንዴ! ለኔም እዘኑልኝ እንጂ:: አሁን ሰው ጠበል ቢጠመቅ፣ንስሐ ቢገባ፣ቢቆርብ ፣ገዳም ቢሳለም እንደሚድን አጥቼው መሰለህ? ግን ስለማውቀውማ ነው ንቅ ንቅ እንዳትሉ መከራ ዬን የማየው:: ቆይ አንተ ጠላትህ በሌለበት ቦታ ጥይት ብትተኩስ ከኪሣራ ውጭ ምን ታመጣለህ:: አየህ የት መተኰስ እንዳለብኝ ዐው ቃለሁ::

<u>ጥያቄ</u> *ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ከእግዚአብሔር ጋር ላስታርቅህ ስትልህ ለምን እምቢ አልክ?*
<u>ሰይጣን</u> ብልጦ እዚያ ሄጄ ባርያ ሆኜ በፈቃድ እግዚአብሔር ልሟራ ሞኝህን ፈልግ የራሴ ግዛት፣የራሴ ባሮች፣የራሴ መንግሥት ያለኝ ነኝኮ:: ይሄንን ባልፈልግ «ድሮስ ምን ከሰማይ ወደዚህ አመጣኝ» እና እኔ «አጠፋሁ» ብዬ ይቅርታ ልጠይቅ? ይሄማ ድፍረት ነው:: ይሄን የሰይጣንነት ኅሊናዬ አይቀበለውም::
<u>ጥያቄ</u> *አንዳንድ ሰዎች አንድ ስህተት ሲሠሩ «ሰይጣን ነው» ይሉሃል፤ በእውነት ሁሉንም የምታሳስተው አንተነህ?*

*ሐና ስሜ /ሞያሌ/*

**ሰይጣን** ጥሩ ጥያቄ ነው:: ጨማምሬ እስኪ እንዲህ ያለ ጥያቄ:: በርግጥ ሰው ደግ ሲሠራ ማየት የሰይጣንነት ልቤን አያስችለውም:: ወደ ሰው የምንቀርበው ግን ሲፈቅድ ነው:: አንድ አሽከሬ የነገረኝን ልንገርሽ አንድ ጊዜ በአንድ መንገድ የነበሩ የበቁአባት ጭፍሮቼን ሁሉ ከሰው ልቡና አስወጥተው ያባርሯቸዋል:: ጭፍሮቼም ወደኒህ አባት ተገዝተው ምን እንሁን? ብለው ጮሁ:: «ካልጠሯችሁ ካልፈለጓችሁ አትምጡባቸው» አሏቸው:: ከዚህ በኋላ በየቤቱ እየዞሩ ፈላጊ ሲያስሱ ኖሩ፡ አንድ ቀን ከአንድ ሰው ቤት ፊት ለፊት ተሠልፈው ቆመው እያለ ባልና ሚስት ሲጨቃጨቁ ሰሙ «ቆዩ ቆዩ» አለ መሪው:: ከዚያ በኋላ ባልየው «ይህች ሰይጣን የሆነች ሴት» ሲል «በሉ ተጠራን እንግባ አሉና ገብተው ተቈጣጠሩት::

አየሽ ሳይጠሩን አንመጣም:: ግን ዙሪያችሁን እንደሚያገሣ አንበሳ እንዞራለን:: አጋጣሚ ስናገኝ እንገባለን:: መቼም አንቺ ሴትዮ ምሥጢሬን ሁሉ ልታዘከዝኪኝ ነው:: ለነገሩ የአምላካችሁን ቃል ያልሰማችሁ ሰዎች የኔን ቃል ትሰማላችሁ ብዬ አልገምትም:: ተናገርኩም አልተናገርኩም ያው ነው:: ሦስት ስትራቴጂዎች አሉን:: እነዚህ ስትራቴጂዎች ለብዙ ዘመናት ተሞክረው ውጤት ያመጡ ናቸው::

የመጀመሪያው «ቁስቆሳ» ይባላል:: ዙሪያውን እየዞርን ምክንያት መፈለግ ነው:: ለምሳሌ ለአንድ ሰው በገፍ ምግብ ታቀርብለታለህ:: አሁን ይኼ ለእናንተ ኃጢአት አይመስላችሁም:: ከዚያ የጥጋብ ስሜት ትለቅህ:: ቀጥለህ ውጣ ውጣ ትለዋለህ:: ጠጋ ትልና «ይኼንን የተቋጠረ ነገር ሿብ ታደርገው አይሻልም አንድ ሁለቷን ውሰድበት» ብለህ ሹክ ትለዋለህ:: ዘሎ ጥልቅ ይልልሃል:: ከዚያ በመጠጥ ኃይል ትገዛና ዝሙት ታሠራዋለህ:: ይኼ «ቁስቆሳ» ይባላል::

ዳዊትን በዝሙት ለመጣል በኦርዮን ሚስት ገላ መታጠብ ነው ቁስቆሳውን የጀመርነው:: ሔዋንን ለመጣል በዕፀ በለስ ውበት ነው የጠነሠስነው::

ይኼ በየመጠጥ ቤቱ የምታየው ቦግ እልም ብልጭ ድርግም የሚለው መብራት፣የሲጋራ የአልኮል ማስታወቂያ የቁስቆሳ ስታራቴጂ አካል ናቸው::

ሁለተኛው «ማስፋት» ይባላል:: ሰውየው አንድ ነገር ሲጀምርልህ ታሰፋዋለህ:: አንድ መለኪያ ከያዘ «ካሜት» እንዲያወርድ ማድረግ ቀላል ነው፤ አንድ ቅንጣቢ ጫት ከቀመሰ ዙርባ እንዲገዛ ማድረግ ይቻላል:: እንደ ቀልድ ንትርክ ከተጀመረ፤ ወደ ጦርነት ታሳድገዋለህ:: «ልሸውደው» ተብሎ የተጀመረ ልማድ አድጎ ስርቆት ቢሆን አይግረምህ:: የዚህ ስትራቴጂ «የዛሬን» የምትል አዝማች አለችው:: ዋናው ለአንድ ቀን፣የዛሬን ብለህ ጀምርልን የቀረውን እናሰፋልሃለን::

ሦስተኛው «ባለህበት ሂድ» የሚባል የወታደሮችን ስፖርት የመሰለ ዘዴ ነው:: ይኼ የሚያገለግለው ከእጃችን ላመለጠ ሰው ነው:: «ቢያንስ ማደግ የለበትም» ባለበት ይርገጥ ነው፤ ለርሱ የሄደ ሊመስለው ይችላል ግን ባለበት ነው የሚሄደው:: ቢቻል እንዳያስቀድስ አርገው ካልቻልክ አስቀድሶ እንዳይቆርብ ጥረት አድርግ፣ቢቻል እንዳይማር አድርገው ካልተቻለ ተምሮ እንዳይሠራበት አዚም ጣልበት:: ከቻልክ በጐ ሥራ እንዳይሠራ የተቻለው ሁሉ ይደረግ:: ካልሆነ «ከንቱ ውዳሴ» የሚባል መርፌ ተወግቶ በሠራው ሥራ እንዳይጸድቅበት አድርገው:: ቢቻል በተክሊል እንዳያገባ አድርገው ካልተቻለ በተክሊል ካገባበት ቀን በኋላ ስለ ቁርባን እንዳያስብ ልቡን ድፈነው የሚሉት ከዚህ ስትራቴጂ መመሪያዎች የሚጠቀሱ ናቸው::

**ጥያቄ** *ካጋጠሙህ ነገሮች ሁሉ በጣም ያስደነቀህን ወይም ያሳቀህን ንገረኝ*

*ኃይሌ ሥዩም /ድሬዳዋ/*

**ሰይጣን** አንድ ጊዜ በአንድ ገዳም ውስጥ አንድ ሰው እመነኩሳለሁ ብሎ ይገባል:: አበምኔቱ ጠንካራ ሰው ናቸው:: አንድ በአት ለብቻው ይሰጡትና ጸልይ ይሉታል:: ሰውየው ለካ በስሜታዊነት ነው ልመንኩስ ብሎ የተነሣው እንጂ ከእኛ የቀማመሳት እርሾ ገና አልለቀቀችውም:: ዕንቁላል ያምረዋል:: ወጥቶ እንዳያስጠብስ ከጸሎት ሰዓት በቀር ከበአቱ መውጣት አልቻለም:: እንዳይችለው አላስቻለውም:: አንድ ቀን ከበአቱ አጠገብ ዘወር ዘወር ሲል የገዳሙ ዶሮዎች ከጣሉት ዕንቁላል አንዱን ያገኛል:: ሰው ሳያየው ደብቆ ይገባና ያስቀምጣታል:: የገዳሙ መነኰሳት ለማኅበር ጸሎት ሲሄዱ ይቀርና ዕንቁላሉን መጥበስ ይጀምራል:: አበምኔቱም ከቁጥር ሰው መጉደሉን ያያሉ ::ወደ ወጣኒው በአት ሲመጡ አጅሬ ለካ ጧፍ አብርቶ በጧፍ እሳት እንቁላል ይጠብሳል:: እኔ በመስኮት ገርሞኝ አየዋለሁ:: አበምኔቱም ደንቋቸው «ምነው ምን ነካህ?» ይሉታል:: ሰይጣን አሳስቶኝ ነው አይላቸውም? መሰለህ:: እኔ ይገርምሃል ይቺን ዘዴ ያለዚያ ቀን አይቻት አላውቅም::ዕድሜ ልኬን ሲገርመኝ ይኖራል::

**ጥያቄ** *እኔ ምንያህል ጊዜ የምኖር ይመስልሃል?*

*ጌታቸው /ከአ/አ/*

**ሰይጣን** ይኸን ጥያቄ እኔ ካለሁበት ደረጃ አንጻር ባልመልሰው ደስ ይለኝ ነበር:: ነገር ግን ልጅ ጌታቸው ኑሮ የምትለው ለመሆኑ ምኑን ነው:: ከኔ ጋር አብረህ የምትውለውን ከሆነ በርግጥ በኔ የትርጓሜ ሊቃውንት ኑሮ ይባላል:: ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል» ትሉ የለ እናንተ ሰዎች:: በኔ የትርጓሜ ሊቃውንት «ኑሮ» የሚለው ቃል ሲተረጐም አንድም ጭልጥ ብሎ ኃጢአት ውስጥ ተዘፍቆ ቢቻል ከኔ በላይ ባይቻል እንደኔ ያለ ሰይጣንነት ባሕሪ ተላብሶ «ሑር ወመሐር» ብዬ አሰናብቼው በየመጠጥ ቤቱ፣በየጫት ተራው፣በየአመንዝራው ቤት፣በየመንደሩ በየሀገሩ ነገር የሚቆሰቁስ፣የግፍ ጢስ የሚያጤስ የሚያጋጭ የሚያፋጭ ለባሕርዬ ደግነት፣ ለምግባሩ በጎነት፣ ለዓለማው መንግሥተ ሰማያት፣ ለገንዘቡ ምጽዋት የማይታየው ማለት ነው:: አንድም እነ «ሜ ጌታ» አደፍርስ፣እነ «ጉትት ጌታ» አቴራ ምስ በጻፉት ትርጓሜ እንደተገለጠው ከመብላት ከመጠጣት ፣ከመተኛት ከመነሣት፣ከመሄድ ከመምጣት በቀር ሌላ ቁም ነገር የሌለው ማለት ነው::

አንተ በዚህ የኑሮ ትርጓሜ የምትኖረውን ከጠየቅኸኝ በዚህ ምድር ቢበዛ 40 /ጠንከር ካልክ/ በሚቀጥለው ደግሞ ተደጋግፈን ከወደድኩህም እግሬን ጫን አድርጌብህ እስከወዲያኛው እንኖራለን:: ከዚህ ሌላ ከሆነ የምትጠይቀኝ ለኔ መኖር ስለማልለው የምትጠይቅበት ቦታ ሄደህ ጠይቅ::

**ጥያቄ** *ከጸሎት ሁሉ የምትጠላው ምንድን ነው::*

ወ/ሮ አልማዝ ሥዕሉ /አ.አ/

**ሰይጣን** ከልብ ከተጸለየ የምወደው ጸሎት የለኝም:: አሁን እርስዎ የሚወዱት ሰይጣን አለዎት!

**ጥያቄ** *በሕይወትህ የተደሰትክበትና የተከፋህበትን ጊዜ ብትነግረኝ*

ጤና ወርቅ አዋሽ /ፈረንሳይ ለጋሲዮን/

ሰይጣን የተደሰትኩት አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስ በልተው ከገነት ሲባረሩ ነው:: ያኔ ድል ያለ ፓርቲ ሲዖል ውስጥ ተዘጋጅቶ ነበር::

የተከፋሁት ለምን አነሣሽብኝ ይኸንን ባታነሺብኝ ጥሩ ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ሲያድነውና 5500 ዘመን የያዝኩትን ምርኮ ጥርግርግ አድርጎ ገነት ሲያስገባብኝ ነው እጅግ ያዘንኩት :: የዚያን ጊዜውን አታንሺው::

**ጥያቄ** *ስንጸልይ ለምን ትፈታተነናለህ?*

**ሰይጣን** ይኼማ እኛ እንምታህ አንተ እጅህን አጣምረህ ተደብደብ የማለት ያህል ነው::

**ጥያቄ** የወደፊት ዓላማህ ምንድን ነው?

*ዲ. መለሰ ማሞ/ቆንደልቲ/*

/ይቀጥላል/

# መንፈሳዊነት ነፃ ለመሆን ከመፈለግ ጋር ሲከራከር

## አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ መሆንን ነጻነት ከማጣት ጋር የሚያነጻጽሩት ስምንድን ነው?

*(አሉላ ሰይፈ ገብርኤል)*

ከሥራ ጓደኛዬ ጋር ጥሩ ቅርርብ አለን:: በአዘቦት በአንዲት ክፍል ቢሮአችን ውስጥ ከዓመት እስከ ዓመት አብረን ከመዝለቃችን ባሻገር ቀን ሲያገጣጥመን ሻይ ቡና እንገባበዛለን፤ ምሣ አብረን እንበላለን:: የመስክ ሥራ /field/ ሲኖርም ዕጣ ፈንታችን እያዳበለን አብረን እንወጣለን:: ከአገር አገር እንዞራለን:: የማንገናኝባት አንዲት ሥፍራ ብትኖር ቤተክርስቲያን ናት:: ይህ የሥራ ጓደኛዬ ቤተክርስቲያን መሄድ አይፈልግም:: ለምን አትሄድም ለሚለው ጥያቄዬ «ነፃነት ማጣት አልፈልግም::» ነው መልሱ::

የሥራ ጓደኛዬ አስተያየት ብዙ ቀን በልቤ ሲብሰለሰል ቆይቷል:: ምን ማለቱ መሆኑን የጠየኩት ግን ዘግይቼ ነው:: ነፃነት የሚያሳጣው ምኑ ነው? መጸሙ፣ መጸለዩ፣ ንስሐ መግባቱ፣ ቤተክርስቲያን ማገልገሉ፣በአጠቃላይ ኃጢአትን መተዉ ነውን? ጓደኛዬን ጠየኩት:: መቼም መልስ አያጣም:: «መብላት፣ መጠጣት፣ መደሰት፣ መልበስ እፈልጋለሁ:: ይህንን አድርግ ያንን አታድርግ መባል ይከብደኛል:: ሕግ ያስጠላኛል:: መንፈሳዊነት ደግሞ በሺህ ምንተ ሺህ ሕጎች መታጠር ነው:: ስለዚህ ለጊዜውም ቢሆን አልፈልገውም» አለኝና ቁጭ:: በጊዜው፣ ያቅሜን ያህል መልስ ለመስጠት ሞክሬያለሁ:: ርዕሰ ነገሩ ግን በዚያ አልቀረም:: መጻሕፍትን እንዳገላብጥ፣ ሰዎችን እንድጠይቅ፣ እንድወያይ፣ ይህችንም አጠር ያለች ጽሑፍ እንዳዘጋጅ አድርጐኛል:: «በእውነት ክርስትና ነፃነት ያሳጣል? ካልሆነ ሰዎች እንደዚህ እንዲያስቡ የሚያደርጋቸው ምንድነው?»

መቼም ሰዎች ነፃነታቸውን ላለማስነካት አሻፈረኝ ማለታቸው ትክክል ይመስለኛል:: ለነፃነቱ የማይሞት ማን አለና? ግን «ነፃነት» የሚለው ቃልም ቢሆን ድንበር ወሰን ተበጅቶለት «ይህንን ማለት ነው» ሊባል ይገባል:: ምክንያቱም ነፃነት በየዘርፉ፣ በየዓለሙ የየራሱ ዓይነትና መልክ ሊኖረው ይችላል:: ባጭር ቃል ግን «ከባርነት መውጣት፣ አርነት ማግኘት» ነው ልንለው እንችላለን:: በዚህች አነስተኛ ብያኔም (definition) ቢሆን ብዙ ጥያቄ ማንሣት ይቻላል:: «ባርነት» ራሱ ምንድነው? አንድ ሰው ባሪያ ሆኖ በባርነት ቀንበር የሚያዘው ምን ሲሆን ነው? «ነፃ ወጣ፣ አርነት አገኘ» የሚባለውስ ምን ሲያገኝ ነው? ሁሉን ለጊዜው ተወት አድርገን ከመንፈሳዊው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ብቻ የተገናኘውን የ«ነፃነት» ትርጉም እናንሣ::

አዳም ዕፀ በለስን አድምቶ በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ፣ በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነም ተፈርዶበት፣ የፀጋ ልጅነቱን አጥቶ፣ ባሕርይው ጐስቁሎ ለ5,500 ዘመን ከምድረ ፋይድ የተጣለባቸው ወራት የባርነት ዘመኖች ነበሩ:: «አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ፣ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ» የሚለው የዕዳ ደብዳቤ እስከጠፋበት ዘመን ድረስ የሰው ልጅ የዲያብሎስ ባሪያ ሆኖ ኖሯል:: ጌታችን «በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በሥጋው ያፈርስ ሰላምን ያደርግ ዘንድ፣ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ» ወደዚህች ምድር እስኪመጣ:: በዚህም ርቀው ለነበሩት «ሰላምን፣ ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምሥራች ብሎ ሰበከ:: በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ» መግባትን አደለን /ኤፌ 2÷14–18/:: ለዚህም ነው ሐዋርያው «በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን::» ያለው /ገላ 5÷1/::

> አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ለጽድቅም ለኃጢአትም «ባሪያ» ሊሆን አይችልም:: ለሁለቱም ሳይሆኑ መኖር የሚባል ነገርም የለም:: ምርጫው ሁለት ነው:: የኃጢአት ባሪያ ሆኖ ራስን ከጽድቅ ባርነት አርነት ማውጣት ወይም ለጽድቅ ባሪያ ሆኖ ራስን ከኃጢአት ባርነት ነፃ ማውጣት::

የክርስትና ሕይወት የነፃነት ሕይወት ነው:: ለምንም ነገር ባሪያ አለመሆን:: ባርነቱ ለፍቅር ብቻ ነው:: ሌሎች የክርስቲያን «ጌቶች» የሚሆኑት በፍቅር ስለሚታዘዝ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ «ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት፣ ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያ እንደሆናችሁ አታውቁምን? ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ» እንዲል /ሮሜ 6÷16/::

የክርስትና ትምህርት ራሱም እግዚአብሔር አምላክን «አባት» ብሎ መጥራት እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነት መንፈስ መቀበል አይደለም:: ምእመናንም የሐዋርያውን ቃል ቃላቸው፤ እንደ በቱን እንደበታቸው አድርገው «በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛል» የሚሉት ለዚህ ነው /ሮሜ 8÷2/:: ከባርነት ሁሉ የሚበልጠው ለሥጋ ፈቃድ፣ ለሰይጣን ፍላጎት መገዛት ነው:: ትልቁ ነጻነትም ከዚህ ፈቃድ ራስን መከላከል፣ ለሥጋ ፈቃድ አልገዛም ማለት፤ ሐዋርያው እንደ ተናገረው ብልቶችን ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጎ ማቅረብ ነው:: መጽ

ሐፍ «የኃጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁ» ይላል /ሮሜ 6÷20/::

አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ለጽድቅም ለኃጢአትም «ባሪያ» ሊሆን አይችልም:: ለሁለቱም ሳይሆኑ መኖር የሚባል ነገርም የለም:: ምርጫው ሁለት ነው:: የኃጢአት ባሪያ ሆኖ ራስን ከጽድቅ ባርነት አርነት ማውጣት ወይም ለጽድቅ ባሪያ ሆኖ ራስን ከኃጢአት ባርነት ነፃ ማውጣት:: «ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና» /2ጴጥ 2÷19/:: ለኃጢአት የሚገዛ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው:: «የዚህ ነገር መጨረሻ ደግሞ ሞት ነው:: ለጽድቅ የሚገዛ ደግሞ የቅድስና ባሪያ ነው:: መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው» /ሮሜ6÷22/::

ጥያቄው ለጽድቅ ወይም ለኃጢአት የመሸነፍ፣ እጅ የመስጠት ጉዳይ ነው:: ሐዋርያው እንደተናገረው ከፍ ብሎም እንደተጠቀሰው የሰው ልጅ ለተሸነፈበት ለማንኛውም ነገር ባርያ ይሆናል:: ለጽድቅ መሸነፍ ገነት መንግሥተ ሰማያትን ያስገኛል:: ለኃጢአት መሸነፍ ግን ትርፉ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወደ ሞላበት ሥፍራ መወርወር ነው:: ለዚህ የሚያደርሰን ደግሞ በዚህ ምድር እያለን የምንሸ ነፍበት ወይም የምንሸነፍለት «ነገር» ምንነት ነው::

ይህ ቃል ሁልጊዜ የሚያስታውሰኝ ጎረቤታችንን ነው:: አንዷት መለኪያ በጠዋት ካልቀመሱ እጃቸው ይንቀጠቀጣል:: ጠራራ ፀሐይም ቢሆን ብርድ ከሆዳቸው ገብቶ ይንጣቸዋል:: እንኳን ሥራ ሊሠሩ፣ ሊጾሙም ሆነ ሊያስቀድሱ ሰውም በአግባቡ ሰላም ለማለት ቢያንስ «አንዷት መለኪያ» መውሰድ አለባቸው:: በሲጋራ፣ በጫት፣ በሐሺሽ፣ በመጠጥ ሱስ ተይዘው የነዚህ ነገሮች «ባሪያዎች» የሆኑ ብዙ ሰዎች ዐውቃለሁ:: የነዚህ ሰዎች ገዢዎች ኅሊናዎቻቸው አይደሉም:: ዕፆቹና መጠጦቹ እንጂ:: መብልና መጠጥም ቢሆን «ሱስ» ከመሆን ደርሶ፣ ለመጾም ለመጸለይ እንቅፋት ሊሆኑ አይገባም:: መብል መጠጥ እያሸነፋቸው፣ «ሃይማኖተኛ» መሆንንም እያማራቸው በመካከል ሲዋዥቁ «ወደ ሆድ የሚገባ አያ ረክስም» በምትለው ያለቦታዋ ለጾም በተጠቀሰች ጥቅስ ወደነ እንቶኔ አዳራሽ የገቡ ብዙ ሰዎች ዐውቃለሁ::

ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጌታችን የተናገረው ቃል ለጾም ይሁን አይሁን መጠየቅ፣ መመርመር፣ መማር ቦታ የላቸው:: ጥቅሱ ከሥጋቸው ድካም ጋር የሚስማማ፣ ላለመጾማቸው «ምክንያት» ስለሚሰጥ ጥርግ ይላሉ:: በመጠኑ ከነርሱ የተሻሉቱም ምክንያት አያጡም:: «ጨጓራቸውን ያማቸዋል፣ በድሃ አገር መኖርም ራሱ ጾም ነው::» ለነርሱ «አለመጾም» ወይም «ጹሙ!» ተብሎ አለመገደድ «ነፃነት» ነው::

የሥራ ባልደረባዬ በመጠኑም ቢሆን የዚህኛው የሁለተኛው ክፍል «ባልደረባ» ነው:: መጾም የሚባል ነገር አይፈልግም:: ጠዋት ተነሥቶ ከእህል ካልተገናኘ ያመዋል:: ሁለት ወር ሁዳዴ ከሥጋና ከቅቤ ተለያይቶ መክረም ለርሱ በትንሽ ወፍ ጀርባ ተቀምጦ ጨረቃ ለመድረስ እንደመሞከር ነው:: መቼም «ጓደኛው» ነኝና አንድ ጊዜ መጾም ጀምሮ የሆነውን ነገር ነግሮኝ ሲደንቀኝ ከርሟል:: ሁዳዴ ነው:: መጾም ጀመረ:: ደግሞ «ፍየል ይመስል ቅጠላ ቅጠል መብላት፣ እህል በእህል መመገብ» ሰለቸው:: ከዛም «እባካችሁ ሳላውቅ የበላሁ እንዲመስለኝ በጎመኑ መካከል ሥጋ ጣል ጣል አድርጉበት» ብሎ እርፍ:: ጾሙም በዚያው ፍርስ:: እና አሁንም ለመጾም ሲያስብ ትዝ የሚለው ያ ታሪክ ነው:: የሥጋ ነገር አይሆንለትም::

ችሁ:: ሰውየው የወንድሜ ባልንጀራ ናቸው:: በወንድሜ የተነሣ ቤተሰብ ሆነናል:: እጠይቃቸዋለሁ – ይጠይቁኛል:: አንድቀን በጨዋታ – በጨዋታ ስለ መንፈሳዊ ነገር ተነሣና የዐቅሜን ያህል ላስረዳቸው ሞከርሁ:: ነገር ግን እኔ ከምጠቅሰው የመጽሐፍ ቃል ይልቅ «ከቤተክርስቲያን ደጃፍ» የማይጠፋው የጎረቤታቸው ሕይወት ትልቅ ሥፍራ ነበረው::

ይህ ጎረቤታቸው ከሰው አይገጥምም:: የሰው ነገር አይጥመውም:: ጠዋት ወጣ – ሥራውን ማታ ገባ ካልጋው ነው:: በቃ ኑሮ ለርሱ ይኸው ነው:: የሰፈር ዕድር አያውቀው፣ የጎረቤት ለቅሶ አይደርስ፣ ሬዲዮ አያዳምጥ፣ ቴሌቪዥን አይመለከት፣ ጋዜጣም ሆነ መጽሔት አያነብ፣ የራሱ ዓለም ፈጥሮ ይኖራል:: እንዲያውም አንድ ቀን ሥራ አለመኖሩ በሬዲዮ ተነግሮ ሳይሰማ ቀርቶ መሥሪያ ቤቱ ደርሶ መመለሱን ያስታውሳሉ:: ለርሳቸው መንፈሳዊነት «ይህ» ነው:: እንዲህ ዓይነት ኑሮ ደግሞ አይጥማቸውም:: ከሩቁ ይሸሹታል:: እኔ የምነግራቸው ከዚህ የተለየ ነበረ:: እስኪያጣጥሙት ግን ብዙ ጊዜ ፈጅቶባቸዋል:: በርግጥ አሁን ጥሩ የቤተክርስቲያን ሰው በመሆናቸው ደስ ይለኛል::

ከዚህ ሁሉ እንፃር ስገመግመው ክርስትና ሳይሆን ሰዎች «ክርስትና» ብለው የሚይዙት የየራሳቸው አስተሳሰብ «ነፃነታቸውን» የሚገፍፋቸው እንደሚመስላቸው

## የክርስትና ሕይወት የነፃነት ሕይወት ነው:: ስምንም ነገር ባሪያ አለመሆን:: ባርነቱ ለፍቅር ብቻ ነው:: ሌሎች የክርስቲያን «ጌቶች» የሚሆኑት በ ፍቅር ስለሚታዘዝ ነው::

እኔማ «አንተ የሥጋ ባሪያ» እያልኩ እቀልድበታለሁ::

ሌሎቹና መንፈሳዊነትን ነፃነት ከማጣት ጋር የሚያዋድዱት ደግሞ በሚያውቋቸው የ«ቤተክርስቲያን ሰዎች» እየመዘኑት ነው:: ወደ ቤተክርስቲያን የሚመላለሱ አንዳንድ ሰዎች ሕይወት ከሩቁ ያሸሻቸዋል:: አንድ ምሳሌ ልንገራ

ለመረዳት ችያለሁ:: ለእናንተስ፣በተለይ ደግሞ ለወጣቶች፣ ክርስትና እንዴት ነው? በነፃነት የምትኖሩበት የቅድስና ሕይወት ወይስ ቀንበሩ የከበደ የባርነት ኑሮ? እስተያየታችሁን ለዓምዱ አዘጋጅ ላኩና እንወያይበት?

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ቦታህ የት ነው?

/በደምሴ ነጋሽ/

የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በነበርኩ ጊዜ ካስተማሩኝ መምህራኖቼ መካከል አንዱን እስከዛሬ የማስታውሳቸው ደጋግመው በሚያቀርቡት ጥያቄ ነው:: ከስማቸው በላይ ትዝ የሚለኝም ይኸው የተለመደ ጥያቄያቸው ነው:: ሁልጊዜም «ሁላችሁም በየቦታችሁ ናችሁ? ሰው ቦታ ላይ እንዳትቀመጡ» ሳይሉ ቢሞቱ ማስተማር አይጀምሩም:: «ቦታህ/ሽ/ የት ነው?» ለእያንዳንዳችን የሚቀርብልን የዘወትር ጥያቄ ነበር:: መምህሬ «ለሕፃናት የትምህርት መጀመሪያ ቦታቸውን ማወቅ ነው» የሚል አመለካከት ነበራቸው:: ይሁን እንጂ እኔን የገባኝ አሁን ካደ ግሁ ዘግይቶ ነው – አወይ መዘግየት! እውነትም «ቦታ»ን ማወቅ ትልቅ ነገር ነበር:: ነውም:: ታዲያ ያለወትሮዬ ይህ ጥያቄ ትዝ እያለ ሲያስቸግረኝ «ክለሳ ያስፈልገዋል» አልኩና ጊዜ ሰጥቼ አሰላ ስለው ገባሁ::

እኔና «ጥያቄው» ቀጭ ብለን ስናወጋ ቆየንና ትርጉሙ (የጥያቄው) ከክፍል ውስጥ የተርታ ጥያቄ ከፍ ብሎ አገኘሁት:: እናም በዚህ በኋለኛው (አሁን በገባኝ ልበለው?) ፍቺ ከአን ባብያን ጋር ብንነጋገር ብለን (እኔና ጥያቄው) እነሆ ከፊታችሁ «ቆመናል»:: በዚህ ውይይታችን የማቀርበው ሃሳብ «ፍጹም ነው» ብዬ አልናገርም:: ፍሬ እንደማይጠፋው ግን አልጠራጠርም ለማገኘውም እስኪ በሐሳብ አብረን እና ዝግም::

«ቦታህ/ሽ የት ነው?» የሚለው ጥያቄ (ቢያንስ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ) የመኖሪያ ወይም የመሥሪያ ቤት አድራሻ ቢሰጥ የሚመለስ የዋዛ ጥያቄ አይ ደለም:: የክፍል ውስጥ የወንበር ተርታ ጥያቄም አልሆነም:: ጥያቄው በደፈናው የኃላፊነት፣ የክብርና የተቀባይነት ጥያቄ ነው:: ከዚህም አልፎ የእ ምነት ጥያቄ ነው:: ይህን የምለው ግን ሁለቱም ትርጉሞች በአንድ የሚሠ ምሩበት ሁኔታ መኖሩን ባለመዘንጋት ነው::

ውድ አንባቢ እርስዎ ለራስዎ የሰጡት ቦታ የቱ ነው? በቤተሰብዎ ውስጥ ያለዎት ቦታ ምንድነው /የት ነው? በት/ቤት፣ በሥራ ቦታ፣ በጓደኞችዎና በኅብረተሰቡ ዘንድ ቦታዎ የት ነው? በቤተክርስቲያን ያለዎት ቦታ ምንድነው? እነዚህን ጥያቄዎች እንደ ክርስቲያንነትዎ ለመመለስ ይሞክሩ:: እስኪ ንባብዎን እዚህ ይግቱና ለጥቂት ቂቃዎች ያስቡ «ቦታዬ የት ነው?» ብለው ራስዎን ይጠይቁ::

እርስዎ ጥያቄዎቹን እስኪመልሱ እኔ ስለ «ቦታ» አንድ ሌላ ጥያቄ ልመልስ:: «ቦታ» የሚሰጠው ማነው? ይህን ጥያቄ በተስማማንበት ትርጉም ባላነሣው ኖሮ ቀለብ አድርጋችሁ «ቀበሌ፣ ክልል፣ ማዘጋጀ ቤት...» ትሉኝ ነበር «ቦታ» የማይፈልግ ማን አለ? «ቦታ» ለማግኘት ደግሞ ሰጪውን ማወቅ፣ ምናልባትም ማመልከቻ ማስገባት፣ አስፈላጊውን ክፍያ መፈጸም ይገባል::

ሰው ለራሱ «ቦታ» ይሰጣል:: ሌሎች (ቤተሰብ ጓደኛ ኅብረተሰብ) «ቦታ» ይሰጡታል:: እግዚአብሔር «ቦታ» ይሰጠዋል:: ከመጨረሻው ልነሣና ወደ መጀመሪያው ላቅና:: እግዚአብሔር «ቦታ» ይሰጣል:: ከሁሉ አስቀድሞ ፈጣሬ ዓለማት እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከፍ ጥረታቱ ሁሉ አክብሮ አልቆ ፈጠረው:: የሁሉ አዛዥ ናዛዥ አደረገው:: የማክበሩ ብዛት በእጁ ሠርቶ፣ ሕያው አሳቢ ተመራማሪ አድርጎ በአርአያው በአምሳሉ ፈጠረው:: የሰው ልጅ እንዲህ የከበረ «ቦታ» የተሰጠው ነው:: የሰው ልጅ በእግዚአብሔር በፈጣሪው ዘንድ ትልቅ «ቦታ» (ክብር፣ ፍቅር፣ ሙውደድ) ስለተሰጠው ትእዛዝ ተላልፎ ቢወድቅ አምላኩ ሊያድነው ወደ ከሰማያት ወረደ:: መከራ ተቀበለለት፣ የሰውን ልጅ ከወደቀበት አነሣው:: በጥፋቱ ያጣውን «ቦታ» ሊመልስለት ካሣ ሆነው:: «ፈቀደ እግዚእ ያግእዞ ለአዳም ኅዙነ ወትኩዘ ልብ፤ ወያግብእ ኀበ ዘትካት መንበሩ» እንዲል::

«ወደ ቀደመ ቦታ ው ወደ ቀደመ ክብሩ ይመልሰው ዘንድ ወደደ፤ ክብር ቢሉ ልጅነት፣ ቦታ ቢሉ ገነት ፍጡር ከሆነ ያለቦታ መኖር አይቻለውምና» ይለዋል ሊቁ:: *(ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ)*

የሰው ልጅ ከአምላኩ የተሰጠው «ቦታ» እንዲህ የከበረ ነው:: ከልጅነት ከወራሽነት የበለጠ «ቦታ» የት ይገኛል? አዳምን 5,500 ዘመን ያስለቀሰው ይህን «ቦታውን» ማጣቱ ነው:: የእሱ «ቦታ» የልጅነት ጸጋው፣ ከእግዚአብሔር ጋር መኖሩ ነው:: እነዚህ ካሉለት ሁሉ አለው:: ይህ «ቦታው» ከተጠበቀ ገነት የእሱ ናት:: እናም በኦርቶዶክሳዊነት – በጥምቀታችን ያገኘነው ልጅነት በእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠን ትልቁ «ቦታ» መሆኑን አንድ በሉልኝ:: እንደ አዳም ሁሉ ልጅነታችንን ከጠበቅን ከትዕዛዝ ካልወጣን፣ ብንበድልም ተጸጽተን ከተመለስን የምንኖርባትን መንግሥተ ሰማያት እናገኛለን:: «ቦታ» ከቦታ ሲገጥም እዩልኝ::

ሰው በመሆናችን ማሰብ መመራመር ተሰጥቶናል:: በእዚህ ላይ ኦርቶዶክሳውያን በመሆናችን የእግዚአብሔርን ልጅነት በጥምቀታችን አግኝተናል:: የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን ለዘላለም በደስታ በመንግሥተ ሰማያት መኖር ተሰጥቶናል:: በእግዚአብሔር ዘንድ ያለን «ቦታ» አይገርምም? ቅዱስ ጳውሎስ «ስለማይናገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን» ያለው ይህን ዘላለማዊውን «ቦታ»ም ቢያስብ እንጂ የዕለት ውሎ አዳሩን ብቻ አስቦ መቼ ነው? ታዲያ በእግዚአብሔር ዘንድ እንዲህ ያለ «ቦታ» እን ደተሰጠው የማያውቅ ሰው አልተጎዳም ትላላችሁ? አንድ ወጣት በቅርቡ ኑሮ እንዳሰበው አልሆን ስላለውና ፈተናውን ማለፍ ስላቃተው «ኢትዮጵያ ውስጥ ሰው ሆኜ ከምፈጠር አውስትራሊያ ፈረስ ሆኜ ብፈጠር ይሻለኝ ነበር» ሲል ሰምቼው «ቦታህ የት ነው?» ብዬ ልጠይቀው ፈልጌ ነበር፡ እንደማይመልሰው ገምቼ እያዘንኩ ተውኩት:: ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ እንኳን ከፈረሱ እንደ ሚበልጥ መረዳት አልቻለም:: ክቡር በሆነ ፈጣሪው አምሳል መፈጠሩን፣ ፈረስ ለእርሱ (ለሰው ልጅ) አገልግሎት የተፈጠረ መሆኑን አላስተዋለም:: «ቦታ»ን (ክብርን) አለማወቅ ምንኛ ያሳዝናል በሉ? ቅዱስ ዳዊት የሰውን ልጅ ከክብሩ መዋረድ ሲገልጽ «ክቡር ሰው እንደ እንስሳት ሆነ...» ማለቱስ ለዚህ አይደል? የአው ስትራሊያ ፈረስ «ጋላቢ ነው» ስለሚባል፣ በፈረሱ ፋሚ ኑሮውን ሊሞላ መከጀሉ አሳዘነኝ:: ፈረስ ሆኖ እንደ ሰው ማሰብ የሚቻል መስሎትም ይሆናል:: አወይ «ቦታን» አለማወቅ?! «ቦታህ/ሽ የት ነው?» ይሉ ነበር መም ህሬ:: ልጅነቱን ጠብቆ እግዚአብሔርን እያሰበ፣ ትዕዛዙን እየፈጸመ፣ ስለበደሉ እየተጸጸተ ንሥሐ እየገባ፣ በምክረ ካህን ጸንቶ በሥጋ ወደሙ ተወስኖ የሚኖር በእግዚአብሔር ዘንድ ትክክለኛ «ቦታውን» ➔

ይዟል:: በንስሐ የማይኖር፣ ከሥጋ ወደሙ ፪ሩ ቀ፣ ከ ቋ እግዚአብሔር የተለየ አንድ ደረጃ ከቦታው ወርዷል:: በዝሙት፣ በስካር፣ በስርቆት በሐሜት የሚኖር ደግሞ... ቀጥሎበት:: መንፈሳዊነት ማለት አንድም ይህን «ቦታ» በሚገባ መጠበቅ ማለት ነው:: የዛሬ ጊዜ «ቦታ» ካልተጠቀሙበት ለሌላ ለሚሆኑ በት እንደሚሰጥ ሁሉ «መንፈሳዊ ቦታችንም» ካልሆኑ ንበትና ካልጠበቅነው ለሌላ ይሰጣል:: ለዚህ መቼም ምሳሌ አልጠቅስም ታውቁታላችሁና::

እግዚአብሔር ልጆቹ የሚሰጠው ሌላው «ቦታ» እርሱንና ሕዝቡን እንድናገለግልበት የሚሰጠን ጸጋ (ሥጦታ) ነው:: እንግዳ የመቀበል፣ የማስታረቅ፣ የመምከር፣ የማስተማር፣ የመጻፍ፣ የመዘመር፣ የመማር፣ የጸሎት፣... የመሳሰሉት ሥጦታዎች እርሰን እንዘሩ ባቸው ዘንድ የተሰጡን «ቦታዎች» ናቸው:: የሰንበት ት/ቤትና የሰበካ ጉባኤ አባል ሆነን በም ንችለው ሁሉ ቤተክርስቲያንን ማገልገል ተተክለን እንጸድቅበት ዘንድ የተሰጠን «ቦታ» ነው:: እንደፊ ቋሩ በትዳር ወይም በምንኩስና መኖር አብርሃምን ወይም እንጦንስን እንመስልባቸው ዘንድ የተሰጡን «ቦታ»ዎቻችን ናቸው:: «ቦታህ/ሽ የት ነው?» ይሉ ነበር መምህሬ::

ስለ «ቦታ» ሲነሣ መቼም ቤተ ክርስቲያን «ቦታቸው» ሳትሆን የሞቱ ዕለት ከቤተክርስቲያን ቅጽር መቀበሪያ ቦታ ይሰጠን የሚሉትን ሰዎች ሳናስ ታውሳቸው አናልፍም:: ባያውቁት እንጂ ለእኛ ለምናምን የቤተክርስቲያን ቅጽሯ መንፈሳዊ «ቦታችን» ነው:: ቤተ ክርስቲያን «ቦታችን» መሆኗን ከጥምቀታችን ጀምረን እስከ ሞታችን ድረስ በቅጽሯ በመገኘት እናረጋግጣለን:: ደግሞም'ኮ ቤተክርስቲን አምሳለ መንግሥተ ሰማያት ናት፣ ስለዚህም የመንግሥተ ሰማያት ዜጋ መሆናችንን የምና ጠይቀው ከልደት እስከ ሞት ቤተክርስቲያንን ቅጽሯ ችን ማረፊያችን በማድረግ ነው::

ቅን ፈሪ ጅ እግዚአብሔር በስጣቸው ጸጋ በሚገባ ያልሠሩትንና ያልተመለሱትን ጸጋቸውን ይነሣቸዋል:: ቅዱሱ መጽሐፍ ስለነ ዓሊ በብሉይ፣ ስለታማኞቹ አገልጋዮች በሐዲሱ የሚዘክረንም ይህንኑ ነው::

ለመሆኑ እርስዎ በቤተክርስቲያን ቦታዎ የት ነው? የደፈኑት ቀዳዳ፣ የጠረጉት አቧራ ፣ ፪ሩ ገፉት ምንጣፍ አለ? ውድ አንባቢ ቤተክርስቲያንን የምታውቅዎት እንዴት ነው? መኖርዎን አረጋግጠው «ቦታ» ተሰጥቶዎታል? በሰዓታቱ፣ በቅዳሴው፣ በትምህርቱ፣ በልማቱ የሚሳተፉ ከሆነ የሰንበት ት/ቤት እና/ ወይም የሰበካ ጉባኤ አባል ከሆኑና ግዴታዎን የሚወጡ ከሆነ «ቦታ» አለዎት:: ቦታዎን ፍጹም ለማድረግ ይበርቱ:: እስከ አሁን «ቦታ» ከሌለዎትም ለወደፊቱ ያስቡበት:: ምን አስጨነቀዎት በቤተክርስቲያን «ቦታ» ማግኘት አድካሚ አይደለ? ጉቦ ክፈሉ አይባሉበት:: ይልቅ ይሽቀዳደሙ! እንዴት ያለ የዳበረ የንስሐ፣ የአገልግሎት.... «ቦታ» አለ መሰለዎት?

ይህን ነጥብ የማጠ ቃለው በእግዚአብሔር ቤትም ሆነ በሕዝቡ (በኅብረተሰብ) መካከል ራሳቸውን ያለ ቦታቸው የሚያስቀምጡ፣ በትዕቢት ራሳቸውን ከፍ ከፍ የሚያደር ጉትን እግዚአብሔር «ዝቅ» እንደሚያደርጋቸው አስታውሼ ነው:: በቤተክርስቲያን አገልግሎት ራስዎን ከሌሎች የተሻሉ፣ ጻድቅና ብቁ፣ ከሌሎች የበለጠ ተቆርቋሪ አድርገው ይገምታሉ? የሌሎች አገልጋዮችንና ኦርቶዶክሳውያንን (የሚያውቋቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ) ስሕተት እየመዘኑ እነርሱን ለማናናቅና ፪ሩ ስዎን «ቦታ» ከፍ ለማድረግ አይሞ ክሩም? «በልባቸው አሳብ የሚኮሩ ትዕቢተኞችን አዋረዳቸው» የሚለው ኃይለ ቃል ያለው የት ነበረ?

እግዚአብሔር «ቦታ» እንደሚሰጥ ከተግባባን ከዚሁ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለውን ሌላ ጉዳይ እንጃ:: ሰው ራሱ «ቦታ» ይሰጣል:: ሰው ፪ሩ ሱን «ቦታ» «ይመርጣል» «ይወስናል»:: ሰው ፪ሩ ሱን «ቦታ» የመምረጥና የመወሰን ሙሉ ነጻነት አለው:: ይህ ራሱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠን ትልቅ «ቦታ» አንዱ ገጽ ነው:: እግዚአብሔር አዳምን በገነት አኖረው ከገነት የመውጣት ነጻነቱ ግን የተጠበቀ ነው:: «ቦታ»ውን መምረጥ ይችላል:: በሃይማኖት ረገድ እኛም «ቦታችንን» የመምረጥ ነጻነት አለን:: መንግሥተ ሰማያትን ወይም ገሃነምን በመኖሪያነት «ቦታችን» የማድረግ መብት አለን:: ይሁን እንጂ ለመረ ጥነው «ቦታ» (ለመንግሥተ ሰማያት) የሚስማማ ግብር ሊኖረንም የግድ ነው:: መቼም ጽጌረዳ ያለቦታዋ በረሃ መሃል ሄዳ ካልጸደቁ አትልም:: ቦታዋን መቼ አጣችውና? የበረሃው ቁጥቋጦም «ደጋ ላይ ካልበቀ ልኩ» አይልም ምን ቁርጥ አድ ርጎት?

**እልፎ እልፎ እንደሚታየው ግን ከቤታቸው ውጪ ብርሃን በቤተሰባቸው መካከል ግን ዕንቅብ የተደፋባቸው መቅረዞች የሚሆኑ እሱ:: («እሰን» ልበል ይሆን?)**

በክርስቲያንነታችን የሚኖረን ሰብዕና እንዲሁም ሌሎች ግላዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ለራሳችን «ቦታ» እንድንሰጥ ያደርጉናል–ይረዱናል:: ለምሳሌ በቤተሰባችን ወይም በጓደኞቻችን ዘንድ ለራሳችን የምንሰጠው ቦታ የት ነው? ለራሳችን የምንሰጠው «ቦታ» ማለት በቤተሰባችን፣ በጓደኞቻችንም ሆነ በኅብረተሰቡ ዘንድ (በማኅበራዊ ሕይወት) የምንጫወተው ሚና፣ የምንካፈለው ኃላፊነትና ግዴታ፣ የምንሰጠውና የሚሰጠን አክብሮት ማለት ነው – በግርድፉ::

ሩቅ ሂዱና ሳጥናኤልን አስታውሱት:: እግዚአብሔር መላእክቱን ከፈጠረ በኋላ ተሰወረባቸው:: ሳጥናኤልም ቅ ሩብ እግዚአብሔር አሐዜ መንጦላዕት ነበርና ወደ ላይ ቢመለከት ዓይኑ ያርፍበት ነገር አጣ:: «ከእኔ በላይ ማንም የለም ማለት ነው?» ብሎ ራሱን ጠየቀ:: ወደታች ተመለከተ ነገደ መላእክት በየቦታቸው ነበሩ፡ ከበላዩ የሚያየው ነገር ስለሌለ የሚያየውም የሌለ መሰለው:: ስለዚህም «እኔ ፈጣሪ ነኝ» ብሎ ለራሱ «ቦታ» ሰጠ:: በዚህ የተነሣ የደረሰበትን መቼም ታውቁታላችሁ እዚህ አልተርከውም:: «አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፣ እንዴት ከሰ ማይ ወደቅህ! አሕዛብን ያዋረድህ አንተ ሆይ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቆ ረጥህ! አንተም በልብህ:– ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፣ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፣ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ በልዑልም እመስላለሁ አልህ:: ነገር ግን ወደ ጉድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ» ተብሏል:: (ኢሳ. 14÷12– 16) እንግዲህ በእግዚአብሔር ቤት ስንኖር የእኛ ያልሆነውን «ቦታ» እንዳንይዝ ይገባል:: በቤተክርስቲያን የተለያዩ አገልግሎቶች ውስጥ አንዳንድ ድክመቶችን ብናይ በትሕትና በመቅረብ «ይሄ እንዲህ ቢሆን አይሻልም ወይ?» በማለት እንጂ ለራሳችን የአራሚና የተቺ ቦታ ሰጥተን ከታች ሆነን ከላይ ያሉትን አባቶች ለማዘዝ ለራሳችን «ቦታ» ከሰጠን ወዴት እንደምናመራ መገመት አይቸግርም:: ➡

ጠንቀቅ ነው ኀበዝ። «ቦታ»ን ማጣት
ይሏል ይኼ ነው።
በቤተሰብ ውስጥ ያለዎት
«ቦታ» የት ነው? በቤተሰብዎ ቤተ
ሰባዊ ጉዳዮች ላይ ምን ያህል ይሳ
ተፋሉ? ቤተሰብ ስል ወላጆችን፣ ወን
ድም እኅት ዘመድ አዝማድ እንዲሁም
አብሮዎት የሚኖር ሌላ ሰው ማለቴ
ነው።

ክርስቲያን እንደመሆናችን
ለሌሎች ብርሃን ሆነን መታየት እንዳ
ለብን ይታወ ቃል። ብርሃንነታችን
መጀመር ያለበት ደግሞ ከቤታችን
ነው። አልፎ አልፎ እንደሚታየው ግን
ከቤታቸው ውጪ ብርሃን በቤተሰባ
ቸው መካከል ግን ዕንቅብ የተደፋባ
ቸው መቅረዞች የሚሆኑ አሉ።
(«አለን» ልበል ይሆን?) ግን ለምን?

እናንተዬ መንፈንሳዊ መሆን
ሲጀምሩ ከቤተሰባቸው ጋር በተለያዩ
ምክንያቶች መ ቃቃር የሚጀምሩኮ
ጥቂት አይደሉም። ለዚህ የሚዳርገን
ዋናው ችግር ቤተሰቦቻችን በቅጽበት
እኛ በምንፈልገው መንፈሳዊ መንገድ
እንዲጓዙ መፈለጋችን ይመስለኛል።
በባዕድ አምልኮ የተያዙ ቤተሰቦች
ያሉት ወጣት ተምሮ የመጣ ዕለት
«ካልተዋችሁ» ቢል የተማረውን በጥ
በብና በፈሊጥ ሳያስተምር፣ ሳይመክር
ሳያስመክር ፍላጎቱ ተግባራዊ እን
ዲሆንና ቤተሰቦቹ ከባዕድ አምልኮ ተላ
ቀው ንስሐ እንዲገቡ ቢያዝ ማን ይሰ
ማዋል? ይህቺን ፈሊጥ አጥተዋት በፍ
ቅር ከሚኖሩበት ቤተሰብ የተ[illegible]
በየአካባቢያችን አይጠፉም። ከቤተሰባ
ችን ውስጥ ያለንን «ቦታ» ከምናጣባ
ቸው ምክንያቶች አንዱን ለምሳሌ
ያህል አነሣሁት እንጂ ብዙ መጥቀስ
ይቻላል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክና
ጥቅስ ውጪ እንዲሁም እነሱ «መን
ፈሳዊ» ከሚሉት ነገር ሌላ ማወራ ት
ኀጢአት የሚመስላቸውና ከቤተሰባ
ቸው ጋር የማይጫወቱ፣ ራ ሳቸውን
በኀጢአተኞች መካከል የሚኖር ጻድ
ቃን አድርገው የሚቆጥ ሩ ስመ «መን
ፈሳውያን» ዐው ቃለሁ። እነዚህ ሰዎቹ
«መንፈሳዊ ነታቸውን» እንደ ምክን
ያት ያቀርባሉ። በመሠረቱ ግን መንፈ
ሳዊነት እንኳን ከቤተሰብ ከጠላት ጋር
ፍቅርን የሚመሠርት ነው። እውነት
ተናገር ካላችሁኝ እነዚህ ወገኖቼ በቤ
ተሰባቸው ውስጥ ያላቸውን «ቦታ»
አስበውት የሚያውቁ አይመስለኝም።
የሚያስቡት ደግሞ «መንፈሳዊ» ስለ
ሆኑ ብቻ የቤቱ አዛዥ መሆን ስለሚፈ
ልጉ፣ አምነው ካስጠመቋቸው ወላጆ
ቻቸው በላይ «ክርስ ቲያኖች ነን»
የሚል ቦታ ለራ ሳቸው ሰጥተው የተቀ
መጡ ናቸው። በእርግጥ ከዕውቀት
ማነስ የሚደረግ ስሕተት ሲመለከቱ
በትሕትና ማስረዳት መምከር ይገባል፤
ግን... ምን አመጣው?

ሌሎቹ ደግሞ በግል ሥራ ቸ
ውና በቤተክርስቲያን አገልግሎት ወይ
ም በግል ሥራ ቸው ብቻ ከመጠን
በላይ ከመወጠራ ቸው የተነሣ ጊዜ
ስለሚያጡ ከቤተሰባቸው ጋር ሳይ
ተያዩ ሳምንታት ይቆጠራ ሉ። ግን-ግን
የቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚጀም
ረው ከቤተሰብ መሆኑ ለምን ይዘነ
ጋል? ከቤተሰቤ ጋር ሆኜ የዘመመ
አጥራ ችንን ባቀና፣ ያፈሰሰ ጣሪያችንን
ብደፍን፣ የውኃ መውረጃ ቦይ ብቆፍር
መንፈሳዊነቴ ይጎድፍ ይሆን? ከቶስ
«እናትና አባትህን አክብር» የሚለ
ውን ትእዛዝ የት እንፈጽመው ይሆን?
አደራ ችሁን ቤተክ ርስቲያንን አታገል
ግሉ ማለቴ አይደለም። በሥራ ቦታ
ችንም በትጋት አንሥራ እያልኩ
አይደለም። ብዙ ጊዜ የሚፈጅ፣
ወይም አስቸኳይ የሆነ ሥራ ገጥሞን
ይሆናል። ግን ከቤተሰዎቻችን ጋር
የምንጫወትበት፣ ዘመድ የምንጠይ
ቅበት፣ ሥራ የምናግዝበት ጊዜ ሊኖ
ረን ይገባል ነው የምለው። መንፈሳዊነ
ታችንም ሆነ ሥራ ችን ከቤተሰብ
የሚለየን (ቢያንስ በሃሳብ) አይሁን
ለማለት ነው የፈለኩት። ለነገሩ አንዳ
ንድ ጊዜ ሰዎችን ከቤተሰብ የሚያ
ር ቃቸው፣ «ቦታቸውን» የሚያስተዋ
ቸው የተለያየ ምክንያት ይኖራ ል።
ስለዚህ ምክንያቱን በግልጽ መነጋገር
የሚያስፈልግበት ሁኔታ እንዳለ መዘ
ንጋት የለበትም። ሲሆን «ለምንድነው
ለቤተሰቤ ጊዜ ያጣሁት?» ብሎ ራ ስን
መጠየቅ ደግ ነው። ቦታውን ለመጠ
በቅ ያስችላል። «ቦታህ የት ነው?»
ይሉ ነበር መምህሬ።

በቤተሰብ ውስጥ ስላለን
«ቦታ» ሳነሣ ከሥራ ዎና ከቤተክርስ
ቲያን አገልግሎቷ ጋር ጊዜዋን መድባ
አንድ ቀን ከእናትና ከአባቷ፣ ሌላውን
ከወንድምና ከእኅቶቿ ደግሞ ሌላውን
ከቤተሰብ ሁሉ ጋር ሆና የምታሳልፍ፣
ጓደኛዬ አርአያነቷ ዘወትር አይዘነ
ጋኝም። ሌላው ቢቀር ምክንያት ታሳ
ጣኛለች። አንዱ ወዳጄ ደግሞ በየ
ሣምንቱ እሑድ ከቤተሰቦቹ ጋር ጠ
ዋት ቅዳሴ አስቀድሰው ቀኑን በየፊና
ቸው ይውላሉ። ማታ ደግሞ አብረው
ራ ት ይበላሉ፤ ሲጫወቱ ያመሻሉ።
የጨዋታቸውን ጣዕም አትጠይቁኝ።
አስደሳችና አሳዛኝ ገጠመኞች ይነሣሉ፣
የቤተሰቡ አባላት የወደፊት ሕይወት
እንደ አስፈላጊነቱ መነጋገሪያ ይሆ
ናል፣ ዕቅድ ይወጣል፣ ለእገሌ ቤተክ
ርስቲያን እንዲህ እናድርግ፣... ምኑ
ቅጡ። ደስታና ትምህርት በዚያ አሉ።
እናትና አባቱም ሆኑ ሌላው ቤተሰብ
እሑድ እንዴት እንደሚናፍ ቃቸው
ለመጻፍ ቃት ያጥ ሩኛል። የዚህ
ወዳጄ «ቦታ» በቤተሰቡ ውስጥ የት
እንደሆነ ለመገመት የምትቸገሩ አይ
መስለኝም። ምን የእሱ ብቻ የቤተ
ሰቡ አባላት ሁሉ እንጂ። ይፋቁራ ሉ፣
ይደማመጣሉ፣ ይተሳሰባሉ፤ ይግባባሉ።
በ ቃ ይኸው ነው።

ውድ አንባቢዬ በቤተሰብዎ
ውስጥ የእርስዎ «ቦታ» የት ነው?
ሁሉን በፍቅር ዓይን ይመለከታሉ?
ለቤተሰብዎ የሚሆን ጊዜ አለዎት?
መንፈሳዊ ስለሆኑ ብቻ አይፈሩም?
የቤተሰብዎን አባላት ጥ ቃቅን ስሕ
ተት እየፈለጉ በማጋነን አይቆጡም?
ወላጆችዎ፣ ወንድም እኅቶችዎና መላ
ው የቤተሰቡ አባላት ወደ ቤተክር
ስቲያን የማይመጡ ከሆነ ይህን
ለማድረግ ምን ጥረት አድርገዋል?
ሙከራ ዎ በመካከላችሁ መራ ራ ቅን አል
ፈጠረም? ጥያቄ ሞልቷል ግን ይብ
ቃኝ። እነዚህንና ተያያዥ ጥያቄዎች
በሚገባ ያስቡባቸውና በቤተሰብዎ
ውስጥ ያለዎትን «ቦታ» ይወቁት።
«ቦታህ/ሽ የት ነው?» ይሉ ነበር
መምህሬ።

እስከ አሁን «መንፈሳዊ» ስለ
ሆኑ በቤተሰባቸው ዘንድ ቁጡ፣ የሚ
ፈ ሩ ስለሚሆኑት አነሣሁ እንጂ በተቃ
ራኒው ራ ሳቸውን ከቤተሰቡ አባላት
የሚያገሉ ግዴለሽ የሚሆኑ በዚህም
የተነሣ የቤተሰብ ፍቅር የሚያጡ፣ ሃሳ
ባቸው የማይሰማላቸው፣ ራ ሳቸውን
ዝቅተኛና ብቸኛ አድርገው የሚያ
ዩም አሉ። እንዳለመታደል ሆኖ እነ
ዚህ ሰዎች ይህን ችግር «መንፈሳዊ»
በመሆናቸው የሚቀበሉት መከራ
አድርገው ያስቡታል። ይህ ግን ፈጽሞ
ስሕተት ነው። በቤተሰባችን ውስጥ ከዕ
ድሜያችንና ከችሎታችን አንጻር ሊኖ
ረን የሚገባ ፍቅር፣ ክብር፣ ኃላፊነት፣
ግዴታ አለ። «ቦታችንን» ፈልገን
ማግኘት መወሰን የእኛ ሥራ ነው።
እግዚአብሔርን ያህል አባት፣ መንግ
ሥተ ሰማያትን ያህል ተስፋ ያለው
ሰው ምን ሲደረግ ራ ሱን ብቸኛና የተ
ናቀ አድርጎ ያስባል?

ወንድሜ ምክሬን ሰምቶ መን
ፈሳዊ ላይሆን ይችል ይሆናል። ቤተ
ሰቤም እንደዚያው። መንፈሳዊ ቢሆኑ
ምንኛ ጥ ሩ በነበረ። ባይሆኑም ግን
ቤተሰባዊው ፍቅርና መተሳሰብ መና
ጋት ያለበት አይመስለኝም። ከእኛ
የሚያዩት ፍቅር ከጊዜ ብዛት ሊመል
ሳቸው እንደሚችል አምናለሁ።

እንዲህ ሆነ፦ ከቤተሰቡ አባላት
አንዱ (ሦስተኛ ልጅ) መንፈሳዊ ሆነ።
ቤተሰቡ በሙሉ ኦርቶዶክሳዊ ቢሆንም
የቤተክርስቲያናቸውን ሥርዓት ዐው
ቀው በዚያ መመላለስ እጅግም አያሳስ
ባቸውም። ያ ልጅ ሊያስተምር ተነሣ
«ደግሞ አንተ» እየተባለ አፉን እን

ወደ ገጽ32 ዞሯል

## ራሴን ባጠፋ እኮነናለሁ?

ጥያቄ:- የእኔ ችግር ለየት ያለ ነው:: የዘመኑ በሽታ (ዘIV) ተሸካሚ ነኝ:: በሽታውም ከያዘኝ ወደ ሰባት ዓመት የሆነኝ ይመስለኛል:: ነገር ግን ምንም ዓይነት መረበሽና ጭንቀት የለብኝም:: ምክንያቱም ክርስቲያን እንደመሆኔ መጠን የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ አደር ጋለሁ:: ንስሐ ገብቼ ቅዱስ ቁርባንም ተቀብዬአለሁ:: ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ አንዳንድ የሚያውቁኝ ሰዎች ሲያገኙኝ «ምነው ከሳህ? ምነው ሰሞኑን ሰውነትህ ቀነሰ?...» ሲሉኝ ቅር ይለኛል:: ከዚህም ሌላ የሚያስፈራኝ ነገር አለ:: ይኸውም በሽታው አመንምኖ ሰውነትን ጨርሶ÷አጥንትን አስቀጥሮ መግደሉ ነው:: እኔም ከዚህ በፊት ተመሳልሼ የጠየኳቸው ሰዎች ስሳሉ በዓይኔ አይቼዋለሁ:: ይህንን ሳስብ ራሴን ባጠፋ ግልግል መሆኑን አስብና እንደገና ደግሞ እኮነን ይሆን? እያልኩ እጨነቃለሁ:: በሌላም በኩል ከዛሬ ነገ እድን ይሆናል እያልኩም ተስፋ አደርጋለሁ:: እባካችሁ የማደርገው ጠፍቶኛልና መንፈሳዊ ምክራችሁን ለግሱኝ::

*ወንድማችሁ /ከለ/ለ/*

መልስ:- ከኤድስ ቫይረስ ጋር የተያያዘ ጥያቄ ከዚህ በፊት 7ኛ ዓመት ቁጥር አንድ እትማችን መመለሳችን ይታወሳል:: ከቻልክ መጽሔቱን አግኝተህ ብታነበው መልካም ነው::

የሆነው ሆኖ ለእንደዚህ ዓይነቱ ችግር አንተ የመጀመሪያው ሰው አይደለህም:: በዓለማችን እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በየቀኑ በቫይረሱ ይለከፋሉ:: ይሁን እንጂ ኤድስ በበሽታነቱ ከሌሎች የተለየ አይደለም:: ከዚህ በፊት በዓለማችን የአንዲት ቀን ዕድሜ የማይሰጡና ከኤድስ የበለጠ ብዙ ሰው የጨረሱ በሽታዎች ተከስተዋል:: ስለዚህ በቫይረሱ በመለከፍህ ብቻ ሁሉም ነገር እንዳበቃና የኑሮ መጨረሻ እንደሆነ ማሰብ የለብህም:: አንተም እንደገለጽከውና በራስህም እንዳየኸው በቫይረሱ ተይዣለሁ ብለህ ካሰብክበት ጊዜ ጀምሮ ለዓመታት ያህል በሰላም ኖረሃል:: ከአንተ ሌላ በቫይረሱ ከተለከፉ ከሁለት አሥርት ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠሩ እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች በዓለማችን ላይ እንዳሉም መዘንጋት የለብህም:: ስለዚህ በቫይረሱ በመያዝህ ብቻ ተስፋ ልትቆርጥና ራሴን ባጠፋስ? እስከ ማለት ልትደርስ አይገባም::

እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገሩ ሁሉ ለበጎ በመሆኑ ንስሐ ገብተህ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙን በመቀበልህ ልትደሰት ያስፈልጋል:: ቅዱስ ቁርባን የነፍስም የሥጋም መድኃኒት ነው:: «... ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደሞቱ አይለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘለዓለም ይኖራል» ብሎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ሰማያዊ ተስፋ ተካፋይ ሆነሃል:: ለዚህ ሰማያዊ ክብር በመብቃትህ እግዚአብሔርን ልታመሰግን ይገባል::

ከዚህም ሌላ በሰው ልጆች አእምሮ ከባድና የማይቻል የሚመስለው፤ የተወሳሰበና የሚያስጨንቀው ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሳነዋል ማለት እንዳልሆነም ማመን ያስፈልጋል:: ሰዎች መድኃኒት ስላላገኙለት ብቻ እግዚአብሔር አያድነውም ማለትም አይደለም:: የአናንያ÷ የአዛርያ÷ የሚሳኤል በእሳት ውስጥ መንሸራሸር የሚቻል አይመስልም:: ዳን.3÷19 36 :: የዳንኤል የተራቡ አናብስት ባሉበት ጉድጓድ ውስጥ ተጥሎ በሕይወት መትረፍም በሰው አእምሮ የሚታሰብ አይመስልም:: ዳን.6÷22:: እግዚአብሔር ግን አደረገው:: እምነት ጽናታቸውን አይቶ ፈጸመው:: ስለዚህ አንድቀን እግዚአብሔር ምን እንደ ሚያደርግልህ አታውቅምና እርሱኑ ተስፋ አድርግ::

ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ከታመንን የማናሸንፈው ነገር አይኖርም:: ሮሜ.8÷38:: ለዚህም በእግዚአብሔር ስም ኤልያስ አክአብን ማሸነፉን፤ ሙሴና አሮን ፈርኦንን ድል መንሣታቸውን አስብ :: ለሚያምን ሁሉ ይቻላልና በእምነትህ ጸንተህ ጠበል እየተጠመቅህ ከቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ሳትለይ ኑር::

በተጨማሪም ከዚህ በፊት ሰዎች በበሽታው ሲሰቃዩ ስለተመለከትክና ሌሎች የሰውነትህን መቀነስ ስለነገሩህ ይህንኑ እያሰብክ መጨነቅ የለብህም:: በሰው የታሰበውና የተነገረው ሁሉ ይሆናል ማለት አይደለም:: እንደአንተ ግምት ቢሆን ኖሮ በቫይረሱ መለከፍህን እንደሰማህ እስከዛሬ በጤና እኖራለሁ ብለህ አስበህ ነበር? ይልቅ በእንደዚህ ዓይነት ነገሮች መጨ ነቅህን ትተህ የምታምነው አምላክ ሁሉን ማድረግ ይችላልና ተስፋህን ሁሉ በእርሱ ላይ አድርግ:: መዝ.12 1÷7–8:: ለጊዜው በሥጋ ባትድንም እንኳን የበለጠውንና እግዚአብሔር የሚሰጥህን ሰማያዊ ዋጋ ክብር ልታስብ ይገባል:: ስለዚህ ምድራዊ በሆነውና÷ በሚታየውና ሰዎች ለሚናገሩት ብቻ ትኩረት መስጠት የለብህም::

ከዚህም አልፎ ሰዎች በቫይረሱ መለከፍህን ዐውቀው ቢያገሉህም ልትጨነቅ አይገባም:: ስለ ቫይረሱ በቂ ግንዛቤ ካለመኖር የተነሣ ብዙ ሰዎች የማይገባ ነገር ሊያደርጉና ሊናገሩ ይችላሉና :: አንተ ከሁሉም በላይ ማሰብ ያለብህ እግዚአብሔር ዘወትር ከአንተ ጋር መሆኑን ብቻ ነው:: የምታመልከው አምላክ ከሰማያት የወረደው÷ መከራ የተቀበለውና የሞተው እኮ ለአንተ ነው:: 1ጴጥ.3÷18:: ይህ እስከሞት ድረስ ያደረሰው ፍቅሩ ስለታመምክ የሚቀንስ ይመስልሃል? ዮሴፍን ወን ድሞቹ በሸጡት ጊዜ አብሮት ወደ ግብጽ የተሰደደው÷ በእስር ቤትም ያልተለየው አምላክ ከአንተ የሚለይ ይመስልሃል? ለምን ይህንን ታላቅ ፍቅሩን አታስብም? ለምንስ ሁል ጊዜ የሚታየውንና ሰዎች የሚሉትን ብቻ ትሰማለህ? በዚያ ላይ አንተ እኮ ንስሐ ገብተህ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የተቀበልክ እውነተኛ የእግዚአብሔር ማደሪያ ነህ::

ይህንን ሁሉ የእግዚአብሔር ፍቅር ዘንግቶ ራስን ለማጥፋት ማሰብ ኃጢአት ነው:: በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትም አንድ ሰው ራሱን ካጠፋ ነፍሱንም ሥጋውንም ገድሏልና ጸሎተ ፍትሃት አይደረግለትም:: ከዚህም ሌላ ራስን ማጥፋት «አትግደል» የሚለውን የእግዚአብሔር ሕግ መጣስ÷ ማደሪያ ➡

መቅደሱን (የሰውን ልጅ ሰውነት) ማፍረስ ነው:: ዘጸ.20÷13፣ ዘዳ.5÷17፤ 1ቆሮ.6÷:: እንዲሁም በእግዚአብሔር ፈቃድና ሥራ ውስጥም መግባት ነው፤ መግደልና ማዳን የእርሱ ሥልጣን ነውና! ራስን ማጥፋት ያለ ማመንም ምልክት ነው:: የሚያምን ሰው ምንም ዓይነት ችግር ቢደርስበት በእግዚአብሔር ታምኖ ይወጣዋል:: ፊልጵ.3÷12:: ስለዚህ በክርስትና ሕይወት የሚኖር ሰው ምንም ዓይነት መከራ ቢደርስበት ተስፋ ቆርጦ ራሱን ማጥፋት የለበትም::

ወንድማችን እንግዲህ ይህንን ሁሉ አስበህ እንደክርስቲያንነትህ በእምነት እግዚአብሔርን ተስፋ ልታደርግ እንጂ ገና ለገና በይሆናልና ሰዎች የሚናገሩትን በመስማት ብቻ ተስፋ ልትቆርጥ አይገባም:: ንስሐ ገብተህ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በመቀበልህ ከሁሉም የበለጠውንና ሰማያዊውን ነገር ይዘሃልና ኑሮህን በተስፋ ልትመራ ያስፈልጋል:: አንተም በቅድሚያ የገለጽከውንና «በቫይረሱ ብለከፍም ምንም ዓይነት መረበሽና ጭንቀት የለብኝም» የሚውን ቃልህን ጠብቀህ ልትረጋጋ ይገባል:: ከዚህም ሌላ ሌሎች ወገኖችህን ማስተማርና፤ ማጽናናት ብትችል የበለጠ ደስተኛ ትሆናለህ፤ ለሌሎችም በመትረፍህም ሰማያዊ ዋጋ ታገኛለህ:: «ስለዚህ ራስን ማጥፋት» የሚለውን ሃሳብ ከአእምሮህ አውጣውና በአዲስ መንፈስ መልካምና እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሥራ ለመሥራት ተነሣ! እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን፤ ድንግልም አትለይህ!

## ስለ ሁለት ነገሮች ተጨንቄአለሁ

*<u>ጥያቄ</u>.2 በአንግድነት አንዲት በሰንበት ት/ቤት የማውቃት ልጅ ቤት ሄጄ አየተ ጫወትን አያለ ድንገት ያላሰብኩትን የትዳር ነገር አነሣችብኝ:: እኔም ተማሪ በመሆኔ ሃሳቤ ወደ ትምህርቴ አንደሆነና ለጊዜው ምንም ሌላ ተጨማሪ ነገር ማሰብ እንደማልፈልግ ገለጽኩላት:: በዚህን ጊዜ በጣም ተቆጣችኝ:: በኋላም እኮ ረፈችኝ:: አሁን ስለሁለት ነገሮች ተጨን ቄአለሁ:: አንደኛው ከዚህች እንተ ጋር መጣላቴ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሳሳሰና ክሳት አልቀርም የሚል ሃሳብ ስለተፈጠረብኝ ነው:: ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ገብቶኛልና ምክራችሁን ስግሡኝ::*

*በቀለ /ለምበ/*

<u>መልስ</u>:- ወንድማችን ለራስህም ሆነ ለሌላ ሰው ሕይወት መጨነቅህ ተገቢ ነው:: ክርስቲያን በየትኛውም መንገድ ይሁን በራሱም ሆነ በሌላ ሰው ላይ ፈተና ሲደርስ ለዚያ ሰው ሊያስብለትና ሊጨነቅለት ያስፈልጋል:: ይሁን እንጂ መሰናከልና ማሰናከል ለሚለው ቃል ትክክለኛውን ግንዛቤ የያዝክ አይመስለንም:: መሰናከል መሆን ማለት አንድ ሰው እያወቀ ወይም በንዝኅላልነት ሌላ ውን ከዓላማውና ከእውነተኛው መንገድ ማደናቀፍ ነው::

ከዚህ አንፃር አንድ ወይም አንዲት ወጣት ሌላውን ለተቀደሰ ትዳር መፈለጋቸው (ማሰባቸው) ማሰናከልም ሊባል አይችልም:: ምክንያቱም ወጣቶች ለዐቅመ አዳምና ለዐቅመ ሔዋን ሲደርሱ አንዱ ሌላውን በትዳር መፈለግና እርስ በርስ መተሳሰብ ያለ ነገር ነውና:: እንዲያውም በዝሙትና ጊዜያዊ ለሆነ ነገር ካልሆነ በቀር በተገቢው ጊዜው ከሆነ ለተቀደሰ ዓላማ ለትዳር መተሳሰብ ሊበረታታ የሚገባው ነገር ነው:: ስለዚህ አንተም በእኅታችን ለትዳር መታሰብህን እንዳሰናከልካት ልትቆጥር አይገባም::

በተጨማሪም አንድ ሰው (ፈላጊው) ለዝሙትና ለማይገባ ነገር ቢያስብ እንኳን ከሌላው ወገን በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ÷ መገፋፋት ለምሳሌ ባለባበስ÷ በአነጋገር ÷በምልክት፣ ወዘተ... እስከሌለ ድረስ አሰናከለችው ወይም አሰናከላት ሊባል አይችልም:: ለጲጥፋራ ሚስት ዝሙት ማሰብ ዮሴፍን መልከ መልካምነቱ በምን ምዓይነት መንገድ ተጠያቂ ሊያደርገው አይችልም:: ስለዚህ ወንድማችን አንተም የማይገናኙትን ነገሮች አገናኝተህ ራስህን ባታስጨንቅ መልካም ነው:: እንደዚህ ስንልህ ግን አታስብላት ማለታችን አይደለም:: በተረፈ አቀራረብህና አኳኋንህ እርሷን እንድታስብህ ወይም ወዶኛል ብላ እንድትገምት አድርጓት ወይም ፍንጭ ሰጥተሃት እንደሆነ ግን ትክክል አይደለህም:: ከሌሎች እኅቶችም ጋር ቢሆን ለትዳር የፈለግሃቸው በሚመስል መልኩ መቅረብ የለብህም::

ከዚህም ሌላ ያኮረፈችበትን ምክንያት ለማወቅ ምንአልባት እርሷ ሃሳቧን በገለጸችልህ ሰዓት በማይገባ መንገድ ማለት ተናደህባት ወይም በቁጣ ተቃውመሃት በድንጋጤ አማትበህባት፣ አዝነህባት፣ እንደሆነም ለመመርመር ሞክር:: በኩራትና በትዕቢት አለያም ከኃጢአት አንፃር ተመልክተህ እንደማይገባ ገልጸህላት ከሆነም ትክክል አይደለም:: ክርስቲያን እንኳን ለተቀደሰ ዓላማ ለትዳር ተጠይቆ ክፉ ነገር ቢናገሩትም በክፉ አይመልስም:: ተቃውሞም ይሁን ድጋፍ ሃሳቡን በፍቅርና በትኅትና ይገልጣል:: እንደዚህ ከሆነ ማሰናከልና መሰናከል ከሚለው ጋር በምንም መንገድ ሊገናኝ አይችልም:: ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ጥያቄ ከማናቸውም በኩል ቢቀርብ ተጠያቂው÷ የጠያቂውን ኅሊና በማይጎዳ መልኩ መልስ ሊሰጥ ያስፈልጋል::

በተረፈ እኅታችንም በዚህ አጋጣሚ እንድታውቂ የሚያስፈልገው ለትዳር ያሰቡት ሁሉ ፈቃደ እግዚአብሔር ነው ወይም የራስ ነው ማለት አይደለም:: አንድ ክርስቲያን አንድ ነገር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆንለት ይፈልግና ይሞክራል:: የተባለው ነገር ቢገኝም ባይገኝም÷ ቢሆንም ባይሆንም ይህ ለእርሱ ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን አምኖ ሊቀበል ያስፈልጋል:: ፈቃደ እግዚአብሔር የግድ ከእኛ ሃሳብና ፍላጎት ጋር የተስማማ ነገር ብቻ መሆን የለበትም:: ስለዚህ እኔ ሴቷ ደፍሬ ሳነጋግረው እንዴት አይቻልም ይለኛል የሚል እልህ ይዞሽ በቁጣ... ልትቆጪ ወይም ልታኮርፊ አይገባም:: ከላይ እንደ ገለጽነው ክርስቲያን ተቃውሞም ቢሆን በዚህ መንገድ መግለጽ የለበትምና :: በተጨማሪም አንቺ ራስሽ በቃል ከማናገርሽ በፊት የእርሱን ስሜት ልትረጂ÷ ፍላጎቱን ልታውቂ ይገባሽ ነበር:: የአንቺንም ፍላጎት በተለያዩ መንገዶች በመግለጽ እንዲዘጋጅ (እንደወደድሽው እንዲያውቅ) ልታደርጊው ብትችይ መልካም ነበር:: ምንም ሳያስበውና ሳይዘጋጅ እንደ ዱብ ዕዳ ስታወርጂበት በድንጋጤ ተገቢ ባልሆነ መንገድ መልሶልሽ ሊሆን ስለሚችል ልትቀየሚው አይገባም::***

# ቤተክርስቲያንን ዕወቁ

## የቅኔ መንገድ

*ከሐዑጊዳ*

ባለፈው እትም ቅኔ ስለ ሚለው መንፈሳዊ ድርሰት ምንነትና የትመጣነት አይተን ስለ ግእዝ ቅኔ አመጣጥ፣ ዓይነቶችና ክፍሎች በመጠኑም ቢሆን አቅር በናል:: ዛሬ ደግሞ «የቅኔ መን ገድ» ስንል ካቆምንበት እንቀጥ ላለን::

የቅኔ መንገድ ማለት የቅኔው አካሄድ፣ መልክ ማለት ነው:: የቅኔዎች ዓይነት ባለፈው እትም ያየናቸው ሲሆን መንገዳ ቸው ግን ብዙና ልዩ ልዩ ዓይ ነት ነው:: ሰምና ወርቅ መንገ ድ፣ ውስጠ ወይራ መንገድ፣ ዝምዝም ወርቅ መንገድ፣ አታ ላይ መንገድ፣ አንጻር መንገድ፣ ሙሻዘር፣ ኅብር፣ ፀዐት መንገድ ወዘተ... እየተባሉ በመቶ የሚቆ ጠሩ መንገዶች አሉ:: በዚህ ጽሑፍ እነዚህን በዝርዝር ለማቅ ረብ አንችልም:: ነገር ግን ከበር ካታዎቹ በቅኔ ሊቃውንት ዘንድ ተወዳጅ ነው የሚባለውን አንዱን ብቻ ለማየት እንሞክራለን::

ሰምና ወርቅ መንገድ አንድ ቅኔ ሁለት ፍችዎችን ይዞ የሚቀመጥበት መንገድ ነው:: እነዚህም የሰምና የወርቅ ፍች ይባላሉ:: የሰም ፍች የሚባለው ቅኔውን ስናዳምጥ ወይም ስናነብ ፊት ለፊት የምናገኘው ትርጉም ነው:: ወርቃዊ ፍች የሚባለው ደግሞ ሰፊፉን (እንጀራውን) ከላ ይ አንስተን ማሩን እንድናገኝ የቅኔውን የሰም ፍች ከላይ አንስ ተን ከስር የምናገኘው ምሥጠ ራዊ ትርጉም (ወርቁ) ነው::

ሰምና ወርቅ በባልና በሚስት ይመሰላሉ:: ባልና ሚስት አንድ ካልሆኑ ልጅ እንደማይገኝ ሁሉ ሰምና ወርቅም በባለሙያው ተቀ ናብረው ካልተዋሐዱ ቅኔው ስሜት አይሰጥም:: እንዲያውም ቅኔ የሚለውን ስም አያገኝም::

በሰምና ወርቅ የቅኔ መን ገድ የቅኔውን የሰምና የወርቅ ፍች አስተባብሮ የሚይዝ ቃል አለ:: ይኸውም ኅብረ ቃል ይባ ላል:: በመሆኑም የአንድን በሰ ምና ወርቅ መንገድ የቀረበ ቅኔ የሰሙንና የወርቁን ፍች ለማው ጣት ሁለቱ ፍችዎች የሚገኙ በትን ቃል (ኅብር) መርምሮ ማወቅ (መያዝ) ይገባል::ኑ እንጂ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላለ

<u>ምሳሌ</u>:- *ካህን ገብርኤል ይመስ ለነ ቀሊለ*
*ጎዕሌሃ ለዖፍ አምጣነ አሀደረ ቃለ*

<u>ፍቹ</u>:- ካህኑ ገብርኤል ቀላል ሰው ይመስለናል:: ምነው ቢሉ በወፏ ላይ ቃልን አሳድሯልና::

ይህ ቅኔ በሰምና ወርቅ መንገድ የቀረበ ነው:: የቅኔው ሰምና ወርቅ ፍቺ በቅኔው ሁለተኛ ስንኝ ባሉ ሁለት ቃላት ላይ ይገኛል:: እነሱም ወፍና ቃል የሚሉት ናቸው:: እነዚህን ኅብረ ቃላት መሠረት አድርገን የቅኔውን ሰምና ወርቅ ፍች ስን መረምር እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን::

የቅኔው ትርጉም በሰሙ ካህኑ ገብርኤል እንዲሁ ሲታይ ቀላል ሰው ይመስላል:: ነገር ግን እሱ በወፏ ላይ ቃልን ያሳደረ በመሆኑ ቀላል አይደለም፤ የሚከ በር የሚወደስ እንጂ የሚል ነው:: ወደ ወርቁ ስንሄድ ደግሞ የቅኔው ኅብረቃላት በምሳሌ የተ ቀመጡ ናቸው:: ይኸውም ወፍ የእመቤታችን፤ ቃል የተባለው ደግሞ እግዚአብሔር ቃል መድ ኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይህን ተገንዝበን ወርቁን ስንመረምር መልአኩ ቅዱስ ገብ ርኤል ንጽሕት በድንግልና ሥር ጉት በቅድስና ወደምትሆን እመ ቤታችን ድንግል ማርያም ዘንድ ቀርቦ ወልደ እግዚአብሔር ከእ ርሷ ሰው እንደሚሆን ባበሠራት ጊዜ ጽንሱ በማኅፀኗ አድሯልና:: ለእሱ ውዳሴያችን ከፍ ቢል እንጂ አያንስም የሚል ይሆናል::

በሰምና ወርቅ የቅኔ መንገድ የሚቀርቡ ቅኔያት በመ ንገዳቸው አንድ ይሁኑ እንጂ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ::

አንዳንድ ጊዜ ሰሙ ደክሞ ወርቁ ብቻ ደምቆ ሲገኝ ወርቃ ወርቅ ቅኔ ይባላል:: አንዳ ንድ ጊዜ ደግሞ ከላይ እንዳየነው ኅብር ነው በማለት ወርቅንም ሰምንም የሚጠቀልልበት ጊዜ አለ:: ሰሙ በሚገባ ሳይለይ የሚ ጠቀልልበትም ጊዜ አለ:: በዚህ ጊዜ ሰም ረገፍ ይባላል:: አንዳ ንድ ጊዜም ጽድቅ (ቀጥተኛ ንግ ግር አይነት) መስሎ ኅብርነት ያለው ወርቃ ወርቅ መስሎ ሰም ነት ያለው መንገድ አለ:: ለምሳሌ «ዕፁብሂ ለሰማዒሁ በቢ ታንያ ዘኮነ:: ንጉሠ ዓለም ሆሣ ዕና በዲበ ዕዋል እስመ ተጽእነ» ይላል:: ይኸ ዓይነቱ መንገድ ኅብርነት አለው፤ ደግሞም ጽድቅ ነው፤ ሰም ረገፍ መስሎም ይታ ያል፤ ጥንታዊ የቅኔ መልክ ይ ኸን የመሰለ ነበር:: ማለት ጽድ ቅነቱን ሳይለቅ ኩሸቱ ሳይበዛ ምስጋናነት ያለው ነበር:: ኅብ ርነት ያለው ዐዋቂም የሚያሰ ኘው እንደዚህ አድርጎ አስተባ ብሮ መቀኘት እንጂ ምሥጢሩን ሰውሮ ቤቱን ብቻ መግጠም እንደ ኅቡዕ ስም መድገም ይመ ስላል:: እንደዚህ ያለውን መን ገድ ለይቶ ቤት ሞልቶ ሲገኝ እገሌ ተቀኘ ይባላል:: ግን እገሌ ቅኔ ዓዋቂ ነው ለመባል እነዚህን መንገዶች ማወቅ ብቻ ሳይሆን በእነዚህ ቅኔዎች ሁልጊዜ መቀ ኘት የእነዚህንም አባባል ለይቶ ማወቅና መዝረፍ ይጠበቅበታል:: ➡

### የቅኔ አመራር ዘረፋ ሥርዓት

በቅዱስ ያሬድ የዜማ ባሕል የመሪና የተመሪ ሥርዓት አለ:: ይኸውም መሪው ከፍ ባለ ድምፅ እያዜመ ሲቀድምለት ተመሪውም መሪውን መስሎ እየተከተለ ያዜማል:: የሚቀርበው ቅኔ ድጓ በሚሆንበት ቀን ማለትም እንደትንሣኤ፣ መፃጉዕና ደብረ ዘይት ባለው ቀን መወድሱ ድጓ ሲሆን መሪው እያዜመ ሲቀድም ተመሪውም እያዜመ ይከተላል:: የቅኔ መሪና ተመሪ ግን እንዲህ አይደለም::

ባለቅኔው ለተመሪው ቀስ ብሎ በሹክሹክታ ሲነግረው ተመሪው ከፍ ባለ ድምፅ ለኹሉ በዜማ ያሰማዋል፣ ይህ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? ቢሉ ለጊዜው ቅኔው ምሥጢር መሆኑን ያስገነዝባል:: ፍጻሜው ግን ባለቅኔው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተመሪው ከሐዋርያት የአንዱ ምሳሌ ስለሆኑ «በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ» (ማቴ.10÷26) ያላቸውን ምሥጢር የሚመለከት ነው::

ቅኔ በአብያተክርስቲያናት፣ በልዩ ልዩ ጉባኤያት፣ በክርክር ቦታዎች ወዘተ... ይዘረፋል:: ታዲያ በእነዚህ ቦታዎች ዘረፋ፣ ነጠቃና ግልበጣ የተባሉ የሊቃውንቱን የአእምሮ ፈጣንነት የሚያመለክቱ ክዋኔዎች ይኖራሉ:: ከሁሉም በፊት ግን የቅኔው ደቀመዝሙር የማስነገር ሥራን ይሠራል::

<u>ማስነገር</u>:- በጥሩ ሁኔታ ቅኔ ያወቀ ደቀመዝሙር ዘረፋ ከመጀመሩ በፊት ጀማሪዎችን ደቀመዛሙርት ያስነግራል:: ይህም ሲባል ደቀ መዛሙርቱ ቆጥረው ያመጡትን ቅኔ ያርማል፣ ይፈታል፣ ሙያውን ያስጠናል ማለት ነው::

<u>ዘረፋ</u>:- ዘረፋ ዜማውን አስተካክሎ ቤቱን ጠብቆ በፍጥነት ቅኔን ማቅረብ ማለት ነው:: ይህ የትምህርት ደረጃ ስሙ በትክክል ከግብሩ ጋር የተያያዘ ነው:: አንድ ወራሪ ወደ አንድ አገር ገብቶ በድንገት ይዘርፋል:: ባለቅኔም ቀድሞ በተሰጠው የቅኔ ቤት የተሰጠውን የቅኔ ዓይነት ወዲያውኑ ይቀኛል:: ባለቅኔውም ዘራፊ ይባላል::

ቅኔን እንዲያስተምር የሚተካው ደቀመዝሙር የሚገመገመው ጥሩ ቅኔ በመቀኘቱ ብቻ ሳይሆን በፍጥነት ዘርፎ በመቀኘቱ ነው:: ከዚህም የተነሣ የሚተካው ደቀመዝሙር ነገ በዚህ ሰዓት ለተማሪዎች ቅኔ ትቀኛለህ አይባልም:: መምህሩ በድንገት ግስ ገሶ ከፈጸመ በኋላ ተተኪውን ደቀመዝሙር ዝረፍላቸው ብሎ ያዝዘዋል:: ያን ሲፈጽም ራሱን ችሎ መምህር ይሆናል::

ይህንን የአባቶችን ቅኔ በመቀኘት ጊዜ ምንም አይነት ቅድመ ዝግጅት አለማድረግ የሚያስረዳ አንድ ታሪክ እናቅርብ:: ይህም በአንድ ወቅት በቅኔ ሊቅነታቸው ታዋቂ በነበሩት በአለቃ ዶሪና በማዕበል ወልደሕይወት መካከል የተደረገውን የቅኔ ዘረፋ ውድድር የሚተርክ ነው:: ስማቸው የተጠቀሰው ሁለቱ የቅኔ ሊቃውንት በአንድ ቦታ ተገናኝተው ባደረጉት የቅኔ ዘረፋ ውድድር የዋሸራው ማዕበል ወልደሕይወት አንድ መቶ ኀምሳ መወድስ፣ የጐንጁ ዶሪ ኀምሳ መወድስ ብቻ ይዘርፋሉ::

በዚህም ምክንያት አለቃ ዶሪ በመወድስ ቅኔያቸው መጨረሻ ላይ

*«ማዕበል ቅኔክ ለእመ ገፍዐኒ*
*ተንተንኩ ለወዲቅ ወእግዚአብሔር አንሥአኒ»*

(የቅኔህ ማዕበል በገፋኝ ጊዜ ልወድቅ ተንገዳገድኩ ነገር ግን እግዚአብሔር አነሣኝ) ብለዋል:: ማዕበል ወልደሕይወትም የዶሪን የቅኔ ርቀት በማስተዋል «ዶሪ የቅኔ ፈጣሪ» ብለው አሞግሰዋቸዋል:: አንዳንድ የቅኔ ቤት ታሪክ የሁለቱ መምህራን ቅኔ በሊቃውንት ተገምግሞ በቅኔ ብዛት ሳይሆን በቅኔያቸው ጥራት ጥልቀትና ምጥቀት አለቃ ዶሪ አሸናፊ ሆነዋል ይላሉ:: ለዚህም ነው «ማዕበል ቅኔክ ለእመ ገፍዐኒ-ተንተንኩ ለወዲቅ ወእግዚአብሔር አንሥአኒ» ያሉት ይባላል::

<u>ነጠቃ</u>:- አንድ ባለቅኔ በሚቀኝበት ጊዜ የባለቅኔውን ሃሳብ በመከታተል ቀጣዩን ምሥጢር ተረድቶ ንባቡን፣ ዜማውን ምሥጢሩንና ቤቱን ጠብቆ ከባለ ቅኔው ቀድሞ መናገር ነው:: ለ ዚህም በብዙ የቅኔ ሊቃውንት ዘንድ ስለነጠቃ ሲወራ የሚዘከር አንድ ማስረጃ እናቅርብ::

በአንድ ወቅት የደብረታቦር በዐል በእሑድ ቀን ውሎ መ/ር ሐዲስ በደብረ ጻላሎ አማኑኤል መወድስ ሲያቀርቡ «*በታቦርሂ አመ ቀነፀ መለኮትከ ፈረስ*» ሲሉ ልጃቸው እመይቴ ገላነሽ «*ኢክህለ ስህበቶ ሙሴ ወኤልያስ*» ብለው እንደነጠቋቸው ይነገራል:: እመይቴ የአባታቸውን ቅኔ ንባቡንም ምሥጢሩንም አስተካክለው ነጥቀዋል:: ያንጊዜም አባታቸው «በልላት» አሉ ይባላል:: አዚምላት ተቀበላት ማለታቸው ነው::

ብዙ ጊዜ መጽሐፋዊ ቅኔ ለዚህ ይዳርጋል:: ማለትም ባለቅኔው የቅኔውን ቤት የሠራው ከመጻሕፍት ባገኘው ታሪክ ከሆነ መጻሕፍቱን ያነበበ ሌላ ሊቅ ቶሎ አሳክቶ ሊነጥቀው ይችላል::

ቅኔ ሕዋሳተ አፍአንና ሕዋሳተ ውስጥን ለሕሊና አስገዝቶ በተወሰነ ቁርጥ ሐሳብ የሚታሰብ ነው:: በዚህ የተነሣም በቅኔ ምሥጢር ልቡ የተነካ ሰው ቅኔ በሚያስብበት ጊዜ በፊቱ የሚደረገውን ነገር እያየ አያይም እየሰማ አይሰማም::

የጐንደሩ የቅኔ ሊቅ ክፍለ ዮሐንስ ተቀምጦ ቅኔ ሲያስብ ልቡ ተመስጦ ንጉሡ ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ባጠገቡ ሲያልፉ ባለማየቱ ሳይነሳላቸው ቀረ:: ርሳቸውም ልቡ በምሥጢር እንደተመሠጠ ዐውቀው ወቄት ወርቅ ከኪሳቸው አውጥተው ቢመቱት ብንን ብሎ ደንግጦ ተነሥቶ «*እስጢፋኖስ እባን እመ ዮንልቁ ወገረኒ ኢያሱ በወርቁ::*» አላቸው ይባላል::

### <u>ማጠቃለያ</u>

ቅኔ በቤተክርስቲያናችን አሉ ከሚባሉ ዕውቀቶች አንዱ ነው:: በመሆኑም አባቶቻችን እነሱ ሙያውን አክብረው ሙያውም እነሱን አክብሯቸው በየጊዜው የተለያዩ ቅኔያትን እየደረሱ አእምሮአቸውን ሲያጐለምሱ መንፈሳቸውን ሲያድሱ፣ በኃጢአት የተጐሳቆለ ሰውነታቸውን ሲወቅሱ ምረረ ገሃነምን ጣዕመ

መንግሥተ ሰማያትን ሲያስታ
ውሱ ሃይማኖታቸውን ሲመሰክሩ
ምሥጢራተ እግዚአብሔርን ሲና
ገሩ ኖረዋል:: እነሱም ብቻ ሳይ
ሆኑ ነገሥታቱም መሳፍንቱም
መኳንንቱም ናቸው:: ይልቁንም
በቅኔ ድልድይነት ካለማወቅ ወደ
ማወቅ ተሸጋግረው፤ የመጻሕፍ
ትን ጥልቅ ምሥጢራቸውን በቅ
ኔ ማይክሮስኮፕነት አጉልተው
ተመልክተው ብሉያትን ከሐዲ
ሳት ሐዲሳትን ከሊቃውንት በማ
ስማማት እያብራሩ ተርጉመው
ጉባኤ ሠርተው ሲያስተምሩ
የኖሩ ሊቃውንት እጅግ ብዙ
ናቸው::

የሊቃውንቱንም ቅኔ አልፈው
አልፈው ከደቀመዛሙር ቶቻቸው
አንዳንዶቹ በቃል አጥንተው
ለሰው ቢያተርፉት እንጂ በመ
ጽሐፍ አይጽፉትም ነበር:: ይል
ቁንም ብሉያትን ከሐዲሳት ሐዲ
ሳትን ከሊቃውንት በማስማ ማት
ተተርጉሞ፤ ጥልቅ ምሥጢር ተሸ
ክሞ ከአንደበታቸው የሚ ፈል
ቀውን የመጻሕፍት ትርጓሜ
ቃል በቃል እየጠየቁ ምሥጢ
ሩን እየተረዱ ያጠኑት ነበር
እንጂ በመጽሐፍ መልክ አያስቀ
ምጡትም ነበር::

በዚህ በኩል ክቡር ብላ
ቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላ ሴና
መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀን
በሬ ሊመሰገኑ ይገባል:: ምክንያ
ቱም እነርሱ ያወቁትን ጽፈው
ለሚመጣው ትውልድ ማቆየት
ግዴታቸው መኾኑን ተገንዝበው
ልዩ ልዩ የኾኑ እንግዳ ድርሰቶች
እየደረሱና የሌሎችን ሊቃውንት
ድርሰትም ሰብስበዋል፤ የታላላቆ
ችንም ሰዎች የሕይወት ታሪክ
መዝግበዋል::

ስለዚህ የቅኔ ድርሠት
ጊዜ ሳይወስነው በየጊዜው ከየ
ሊቁ ልቡና ሲመነጭ ሲፈልቅ
የሚኖር እንደመሆኑ ዛሬም
ያሉት ውሱን ሊቃውንት የሚደ
ርሷቸውንም ሆነ ያለፉ ሊቃው
ንት የደረሷቸውን ቅኔያት በመሰ
ብሰብ በጽሑፍ መልክ መቅረፅ
ይገባል::

በዘመናችን በመንፈሳዊ
መምህራን ዘንድ ያለው ስጋት
የቅኔ ንባብና ምስጢር ለወደፊቱ
ዘመን እየተዘነጋ እየሄደ ነው
የሚል ስለሆነ በከተማ የሚገኘው
ወጣቱ ትውልድ ይህን የአባቶ
ቻችንን ትውፊት ተቀብሎ ቤተ
ክርስቲያኑን ለማገልገል እንዲ
ችል ብየአድባራቱ ከሚገኙ መም
ህራን እግር ስር ቁጭ ብሎ መ
ማር ይጠበቅበታል:: ሥርዓተ
ቤተክርስቲያንን በሚገባ ያልተ
ማረ ወጣት ቤተክርስቲያንን
ሊያገለግል አይችልም:: ዘመና
ችን ኑፋቄ የተስፋፋበት በመሆኑ
የቤተክርስቲያናችንን ቋንቋ በሚ
ገባ ካልተማርን አምላካችንን እን
ደአባቶቻችን ተግተን ካላገለገልን
ወገኖቻችንን ለጥፋት አሳልፈን
እንሰጣለን:: ስለዚህ በተሰጠን
ፀጋ በሚገባ ተጠቅመን ለራሳች
ንም ሆነ ለወገኖቻችን የሚጠቅም
ሥራ ለመሥራት የቤተክርስቲ
ያናችንን ትምህርት ማወቅ ይጠ
በቅብናል::

## ቦታህ የት ነው ?

*ከገጽ 27 የዞረ*

ዲይዝ ተደረገ:: ነገሩ ገባው::
ዘዴውን መቀየር አለበት:: ገበታ
ሲቀርብ «ካልጸለያችሁ» ብሎ
አይከራከርም፣ እነርሱ መብላት
ጀምረው እሱ «አቡነ ዘበሰማ
ያት» ይላል፤ የደረሰበትን ይጎር
ሳል:: ጠዋትም ሆነ ማታ «ካል
ጸለያችሁ»፣ «ቤተክርስቲያን ካል
ሄዳችሁ» አይልም፤ እሱ ግን ያደ
ርግዋል:: በቤተሰብ መካከል
ከሚነሣው ጨዋታ ራሱን አላገለ
ለም፤ በሁሉም ውስጥ ይሳተ
ፋል፣ አስተያየቱን ይሰጣል፣
የተሳሳተ ነገር ሲኖር ምክንያት
አቅርቦ «እንዲህ አይመስለኝም»
ይላል በእርጋታ:: (በማረም–
በመቆጣት አይደለም)

ጊዜ በጊዜ ተዋጠ::
ከታናናሾቹ አንዱን ሊያስጠናው
ሲቀመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቀው
ገባ:: እሱም እንደ አቅሙ ይመ
ልስለት ጀመር:: «ልየው» አለ
ታናሹ ይዞት ሄደ:: ነጠላ አጣ
ፍቶ በመልበሱ የማያፍር አንድ
አጋር አገኘ:: እኅቱ ተከተለች::
ተከ ተለ–ተከ ታተሉ:: አስታ
ውሱ መጀመሪያ ከተሳሳ ተባት
ቀን በስተቀር «ላስተምር» «ታረ
ሙ» ብሎ አልተና ገረም:: ከገ
በታ አይቀርም፣ ቡና ሲፈላ እሱ
እዚያ አለ:: ይስቃል ይጫወ
ታል፣ ታናናሾቹን አቅፎ ይስ
ማል–ያስጠናል፣ ከታላቁ ጋር
አብሮ ይተኛል... በቤተሰብ ግን
ኙነት የተቀየረ ነገር አልነ
በረም:: የዚያ ወጣት ውስጣዊ
ሕይወት ግን ተቀይሮ ነበር::
አስቀድሞ የውጪቱን ውስጥ
አጠራ:: ከዚያ ውጪውን:: በመ
ጨረሻ ቤተሰቡ ሁሉ መሰለው::
ይህ ወጣት ዛሬ በቤተሰቡ ውስጥ
ያለውን «ቦታ» ሁላችንም ብናገ
ኘው ምንኛ በታደልን? «ቦታህ/ሽ
የት ነው?» ይሉ ነበር መም
ህሬ::

እንደ ወላጅ ፣ እንደባል
/ሚስት፣ እንደ ልጅ፣ እንደ ወን
ድም/ እኅት... በቤተሰብዎ
ውስጥ ያለዎት «ቦታ» ምንድ
ነው? በትክክል እየተጠቀሙበት
ነው? ብሉያትንም ሐዲሳትንም
ቢያገላብጡ ብዙ ምሳሌዎች ይገ
ኛሉና እስቲ ይቃኙት:: አንድ
ዐቢይ ነጥብ ላስታ ውስና ይብ
ቃኝ:: የኅብረተሰብ መሠረት
ቤተሰብ ነው:: በቤተሰባቸው
ውስጥ ትክክለኛ «ቦታቸውን ይዘ
ው» በትክክል ያደጉ ልጆች በኅ
ብረተሰቡም ውስጥ ትክክለኛ
«ቦታቸውን» ለማግኘትና የሚሰ
ጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት
አይቸገሩም:: ከታላላቆቹ በላይ
ተጋኖ ያደገ ልጅ መበለጡን
የማያምን (ለመብለጥ መጣር
አይደለም) በማንኛውም መንገድ
የበላይነቱን ማሳየት የሚሻ ጎል
ማሳ ይሆናል፣ ሃሳቡን እንዳ
ይገልጽ ታፍኖ–ሃሳቡ እየተጣ
ጣለ ያደገው ደግሞ ኃላፊነትን
እንደሸሸ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ
ትክክለኛ «ቦታውን» ሳያገኝ እን
ደተሸማቀቀ ያልፋል:: ቤተሰብ
የኅብረተሰብ መሠረት ነው::
ቤተሰብ ውስጥ የተዘራ ኅብረተ
ሰብ ውስጥ ይለቀማል:: እናም
ለልጆቻችንና ለታናናሾቻችን
የምናደርገው ነገር ሁሉ «ቦታቸ
ውን» እንደሚወስን ልብ ይሏል::

እስከ አሁን «ቦታ–ቦታ»
እያልን እግዚአብሔር ስለሚሰጠ
ንና፣ በቤተሰባችን መካከል ስለ
ሚኖረን «ቦታ» በዚህም ታክኮ
ለራሳችን ስለምንሰጠው «ቦታ»
በአለፍ ገዳም አውስተናል::
ሌሎች (ቤተሰብ፣ ጓደኛ ኅብ
ረተሰብ) ስለሚሰጠን ቦታ የምለ
ውን አስከትላለሁ:: ይቆየን!

## ከመጻሕፍቶቻችን

# ፍትሐ ነገሥት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካሉ ጥንታውያን መጻሕፍት መካከል አንዱ ፍትሐ ነገሥት ነው:: ፍትሐ ነገሥት ማለት የነገሥታት ፍርድ ማለት ሲሆን በቀድሞ ዘመን ነገሥታቱ መንፈሳዊ ከመሆናቸው የተነሣ ሥጋዊውንም መንፈሳዊውንም ፍትሕ ይመለከቱ ስለነበር በነገሥታት ስም ተሰይሟል::

ይህ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በ325 ዓ.ም. በኒቂያ የተሰበሰቡ ሊቃውንት የጻፉት ሲሆን ከዚያ በኋላ ግን በተለያየ ዘመን የተነሱ የሕግ ሊቃውንት የተለያየ ሐሳብ እንደጨመሩበት ይነገራል::

ከ565 – 577 የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የነበረ አስቀድሞ በጥብቅና የሥራ ነገር አዋቂ ምሁር ዮሐንስ የሚባል ሰው የሠልስቱ ምዕትንና ሌሎችንም ሕግጋት በአንድነት አገናዝቦ 51 አንቀጽ ያለው በጣም የበሰለ አስተያየትን የያዘ ፍትሐ ነገሥት በጽርዕ ቋንቋ ጽፎ ነበር:: ይህ መጽሐፍ ለተወሰነ ጊዜ ይጠፋና ከጊዜ በኋላ አብርሃም ቀሲስ የተባለ ሰው አግኝቶት አስፋፍቶ እንደጻፈው ይነገራል::

በሌላ በኩል ይህ መጽሐፍ በ318ቱ ሊቃውነት ብቻ ያልተጻፈ ስለመሆኑ በውስጡ ያለውን ታሪክና ሰነድ በመመርኰዝ ማረጋገጥ እንደሚቻልም ታሪክ ጸሐፊዎች ይናገራሉ

ለምሳሌ:- ዮሐንስ አፈወርቅ ቅዱስ ባስልዮስ ጎርጎርዮስ ቴኦሎጎስ ከሠልስቱ ምዕት ከ318ቱ ሊቃውንት በፊት አልነበሩም:: በኋላ እንጂ. ታሪካቸው ግን በፍትሐ ነገሥት ተጽፏል:: የሰርጽቅያ ሲኖዶስ የላኦዶቅያ ሲኖዶስ ከኒቂያ ሲኖዶስ በፊት ሳይሆን በኋላ የተካሄዱ ናቸው:: ግን በዚሁ መጽሐፍ አሉ:: የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት ክርስቶዶሎስ ገብርኤል ኢብነ ቱራይቅ የኋላ ዘመን /የ10ኛው እና የ11ኛው ምዕት ዓመት/ ሊቃነ ጳጳስ ናቸው:: እነርሱም በውስጡ አሉ:: «ጠሰን» የሚለውን ክፍል ብንወስድ በ9ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ በቁስጥንጥንያ ንጉሥ ባስልዮስ ዘመቄዶንያ ቀዳማዊ የታወጀ ሕግ ነው:: ከዚህ አንጻር ከ318ቱ ሊቃውንት በኋላ የነበሩ ሰዎች ውሳኔ ታሪክ... በዚህ መጽሐፍ እያለ መጽሐፉ በ318ቱ ሊቃውንት ብቻ ተጻፈ ማለት አይቻልም የሚለውም አባባል ትክክል ይመስላል::

ስለዚህም ሆነ በሌላ መልኩ ብናየው አብርሃም ቀሲስም አስፋፍቶ ጻፈው ሠልስቱ·ምዕት አረቀቁት መጽሐፉ ጥንታዊ መሆኑ አያጠራጥርም::

ፍትሐ ነገሥት በውስጡ ለሥጋዊውም ሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚጠቅሙ ሕግጋትን ይዟል::

ለምሳሌ:- – ስለ ቤተክርስቲያን /ስለ ሥርዓቷ/ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት፣

– ስለ ክህነት /እንዴት ይሰጣል ለማን ይሰጣል ስንት ማዕረግ አለው

– ስለ ጸሎት የት መጸለይ አለበት መቼ መጸለይ አለበት...

– ስለ ምጽዋት

እነዚህ መንፈሳዊውን ነገር የያዙ ሕግጋት ሲሆኑ በተጨማሪ ለሥጋዊ ኑሮአችን የሚጠቅሙ::

ስለ ብድር ስለ ርስት ስለ ሌብነት ፍርድ ስለ ነገሥታት የተጻፉ /የረቀቁ/ ሕግጋት አሉበት::

በክርስትና ስንኖር ስለሚገጥመን ማንኛውም ችግር መፍትሔ የሚሰጠን ከሕግ ውጪ እንዳንሆን መንገዱን የሚጠቁመን የሕግ መጽሐፍ ነው:: ጌታችን ጸልዩ አለን እንጂ አጠቃላይ የጸሎት ሕግጋትን አላስቀመጠልንም ሌላውንም ጾምን ስግደትን ክህነትን ቁርባንን... በተመለከተ አስፈላጊ መሆኑን አስተማረን እንጂ ዝርዝር በሆነ መልኩ በዚህ ቦታ በዚህ ሰዓት በዚህ ሁኔታ ፈጽሟቸው አላለንም:: ነገር ግን እኔ ከሄድኩ በኋላ በእኔ የሚያምን... እኔ ከማደርገውም በላይ ያደርጋል ባለው መሠረት:: በመንፈስ ቅዱስ የተሾሙ ሊቃውንት ጳጳሳት ሕግን አርቅቀው አስቀመጡልን ስለዚህም ፍትሐ ነገሥት ሊቃውንት አጠቃላይ የሆነውን ሁኔታ በዝርዝር ያረቀቁበት የሕግ መጽሐፍ ነው::

---

## ለ1991 ዓ.ም ተመራቂዎች

ማኅበሩ ያዘጋጀው የ1991 ዓ.ም የምረቃ መጽሔት በአንዳንድ ምክንያቶች ቢዘገይም በአሁኑ ወቀት ዝግጅቱ ተጠናቆ ለምረቃ በመታደል ላይ ይገኛል:: ስለዚህ የ1991 ዓ.ም የግቢ ጉባኤያት ምረቃን ወደማኅበሩ ጽ/ቤት /አዲስ አበባ/ በመምጣት እንድትወስዱ ወይም ደግሞ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ግንኙነት ክፍል አድራሻችሁን በመግለጽ እንዲላክላችሁ ማድረግ የምትችሉ መሆኑን ከታላቅ ደቀርታ ጋር እንገልጻለን::

*የመንፈሳዊ አገልግሎት ግንኙነት ክፍል*

---

እንኳን ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ አሸጋገርዎ እያለ የማኅበረ ቅዱሳን መዝሙርና ስነጽሑፍ ክፍል ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የጠበቀ የትግርኛ መንፈሳዊ ካሴት የዘላችሁ ቀርቧል:: ካሴቱን ከማኅበሩ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣና የሐመር መጽሔት ማከፋፈያ ሱቆች ያገኙታል::

ለማንኛውም ጥያቄዎ

በስልክ ቁጥር 11 48 70

ደውለው ያነጋግሩን::

---

## የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ

| | የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | የሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 ወር እትም | የ12 እትም | የ6 ወር እትም | የ12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 10.00 | 20.00 | 18.70 | 37.40 |
| የክፍለ ሀገር | 10.50 | 21.00 | 19.00 | 38.40 |
| ከኢትዮጵያ ውጭ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዳላር |


ለአቶ መስፍን ተ/ዮሐንስ ተሻለ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ
የባንክ ሂሳብ ቁጥር 75282 አዲስ አበባ ብለው ከላኩ በኋላ
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ማስረጃ
የመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን



እነዚህንና ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳትን በማከፋፈያ ማዕከላችን ያገኟቸዋል፤ ይዘዙን እናዘጋጃለን። ለተክሊል ተጋቢዎችም ካባዎችን እናከራያለን። በተመጣጣኝ ዋጋ ጥሩ ሥራ ለማሠራት ወደ እኛ ይምጡ።

አድራሻ:- ከገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ወደ 6 ኪሎ በሚወስደው መንገድ
ከመቅደላ ሆቴል አጠገብ።

✉ 12 84 60
☎ 80 078





ብራና ማተሚያ ድርጅት ታተመ

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡